ይመጣል። ራሳችንን ከሌላው ጋር ማወዳደር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እን ዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ይሁን እንጂ፥ ራሳቸውን ከሚ ያመሰግኑ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ራሳችንን ለማወዳደር ወይም ራሳ ችንን ለማነጻጸር አንደፍርምና፥ እነርሱ ግን ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር በማመዛዘናቸውና ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር በማወዳደራቸው አስተ ዋዮች አይደሉም"* ይላል (2 ቆሮ. 10፥12)። የእግዚአብሔር ቃል ራሳ ችንን ከሌሎች ከማወዳደር ይልቅ፥ *"ዝትሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቁጠሩ እንጂ መጀ በመለየ ትና በራስ ወዳድነት ወይም ያለ አሌ ማን አለ በሚል ትምክሕት ምንም ነገር አታድርጉ"* በማለት ይመክረናል (ፊልጵ. 2፥3)።

ሁልጊዜ ከማማረርና ከማጉረምረም በስተቀር ከአፋቸው ጨርሶ የምሰጋና ቃል የማይወጣቸው ክርስቲያኖች አሉ። ምንም ያህል ቢኖ ራቸው የሚረኩ አይደሉም። እንደነዚህ ዓይነቶቹ የራሳቸውን ደስታ አጥተው አብረዋቸው ለሚኖሩት ሰዎችም ሲአል ይሆናሉ። በማማረ ርና በማጉረምረም የተሞሉ ሰዎች ምንጊዜም ቢሆን የሚያማርሩበት ወይም የሚያጉረመርሙበት ምክንያት አያጡም። አንድ ጊዜ በአንድ ከተማ ውስጥ በማማረሩ በጣም የታወቀ አንድ ገበሬ ነበር። ከምንጊ ዜውም የበለጠ ገበሬዎች ጥሩ ምርት ያመረቱበት ዓመት ነበር። ከእርሻቸው ያገኙት ፍሬ በጣም ጥሩ ነበር። ድንቾቻቸው በጣም ትልልቅ ነበሩ። የአካባቢው ገበሬዎች "ያ አጉረምራሚ ሰው ለማጉረ ምረም ምንም ዓይነት ምክንያት የማያገኝበት ዘመ" ቢኖር ይሄ ዓመት ነው" በማለት ሄደው "ስለ ዘንድሮ ጥሩ የመከር ጊዜ ምን ትላለህ?" ብለው ጠየቁት። እርሱም "አሳማዎቼን የምመግብበት ትና ንሽ ድንች የት አለ?" በማለት አሁንም ሁኔታውን አጨልሞ መልስ ሰጣቸው። ምክንያት እየፈለጉ የሚያማርሩና የሚያጉረመርሙ ሰዎች ግን ይወዳል? ሁልጊዜ "የማማረርና የማጉረምረም ቃል" የሚያሰሙ ሰዎች በሕይወታቸው እርካታ ያጡ እንደሆኑ ተመልክተናል። እንዲህ ዓይነቶቹ መንግሥት ሰማይም እንኳን ቢሆን፥ ቆረቆረን፣ አልተመቸ ንም እንደሚሉ የታወቀ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ የተማ ረውን ትልቅ ነገር ሲገልጽ *"ስለዚህ ማንኛችንም ሆን ማጣትን ዐው ቃለሁ፥ በማንኛውም ቦታ ሆነ በየትኛውም ጊዜ የመገብንና የመራ ብን፥ የማንንትንና የማጣትን ምስጢር ተምሬአለሁ"* ይላል (ፊልጵ. 4፥11-12)።

ምዕራፍ ፭

ነቃፊ ምላስ

"ሳያስብ በችኮላ ከሚናገር ሰው ይልቅ
አዕምሮ የጎደለው ሰነፍ የተሻለ ተስፋ አለው።"
ምሳ. 29፥20

የክርስትና ሕይወት አንድ ቦታ የሚቆም ሳይሆን፥ ዕድገት ያለበት ሕይወት ነው። እግዚአብሔር የጠራን እንድናድግ ነው። *"ይልቅስ በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እርሱንም በማወቅ እደጉ..."* ይላል (2 ጴጥ. 3፥18)። ዕድገታችንም በግል፥ ከእግዚአብ ሔርን እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ነው። ዕድገታችን ምን ዓይነት እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፥ *"እውነትን በፍቅር እየተናገርን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር እናድጋለን"* (ኤፌ. 4፥15) ይላል። የዕድገታችንም ፈጻሚ መንፈስ ቅዱስ ነው። *"የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ደግነት፣ ቸርነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው..."* ይላል (ገላት. 5፥22-23)። ሲጋዊው የሕይወታችን ዕድገት ግብዂያ አለው። መንፈሳዊው ዕድገታችን ግን እንደ ሥጋ ዊው ዕድገታችን ግብዂያ የለውም። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ባደ

ግን ቁጥር፥ የማደግ ፍላጎታችን ይበልጥ እየጨመረ ይሄዳል። ለዕድገታችን እንቅፋት ከሚሆኑት ምክንያቶች መካከል አንደኛው ነቃፊነት ነው። ምን ያህል ጎዳት በሌሎች ላይ እንደሚያመጣ ባለመረዳት አንዳንዶቻችን "መንቀፍን" እንደ ጥሩ ልማድ አድርገን ይዘነዋል። የታወቀው ዴል ካርነጊ (Dale Carnegie) "መንቀፍ" ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል ሲጽፍ፥ *"ነቀፌታ የሰውን ስሜት ይጎዳል፣ ሰዎችን ዝቅ ያደርጋል፣ ተስፋ መቁረጥን ያደርሳል፣ ጠብን ይጭራል፣ ከሰው ጋር ያለውን ግንኙነት ያበላሻል"* አለ። ገንቢ ያልሆነ ነቀፋ ምን ያህል እንደሚጎዳ የምንረዳው በነቀፋ ውስጥ ስናልፍ ብቻ ነው። "ነቀፌታ" ማለት ምን ማለት ነው? "ነቀፌታ" ምን ማለት እንደሆነ ዊልያም ዳይሽም *(William Diehm)* ሲገልጸው *"ጥሩ ያልሆነ አሰተያየት መስጠት፣ በሌላው ላይ ስህተት መፈለግ፣ መውቀስ፣ መታዘብ፣ መገሰጽ"* ማለት ነው አለ። በአጭሩ "ነቀፌታ" ማለት አንዱ በሌላው ላይ ለመፍረድ ስህተት ፈልጎ ማግኘት ማለት ነው።

የበታችነት መንፈስ የሚያጠቃቸው፣ በኑሮአቸው በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡ፣ ከሰው ሁሉ ተገልለው ለብቻቸው መኖር የሚፈልጉ፣ በቀላሉ የህዘን ስሜት የሚሰማቸው ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በልጅነታቸው በወላጆቻቸው ወይንም በአሳዳጊዎቻቸው እየተነቀፉ ያደጉ ሰዎች እንደሆኑ የሥነ ልቦና ምሁሮች ይገልጻሉ። ጤናማ ያልሆነ ነቀፋ ምን ያህል ጉዳት እንዳለው ያልተረዱ አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው ሲሳሳቱ፥ "እንተ ደደብ ልጅ! ይሄ እንዴት አይገባህም?" ይሉታል። ልጆቻቸውን በአግባቡ የሚያሳድጉ ወላጆች ግን ልጆቻቸው ሲሳሳቱ ነቀፋና ስድብ ውስጥ ሳይገቡ "ይሄን እንዲህ አድርገህ ትሠራዋለህ" ወይም "ይሄ ግለትተ ይሄ ነው" ብለው መመሪያና ትምህርት ይሰጧቸዋል። የነቀፋና የክስ ዋና ምንጭ ሰይጣን ነው። ሰይጣን ክሳሻችን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ራዕይ 12፥10)። በኢዮብ ዘመን የእግዚአብሔር ልጆች በተሰበሰቡበት ወቅት ሰይጣን የቀረበው ለመክሰስ እንደነበረ እናውቃለን (ኢዮብ 1፥6)። ሰይጣን ሌላው ቀርቶ በገነት እግዚአብሔርን ከመውቀስ ወደ ኋላ እንዳላለ እናስታውሳለን (ዘፍ. 3፥4-5)። ሰይጣን የሚጠቀምበትን መሣሪያ (ነቀፋን) መጠቀም ስንጀምር፥ ራሳችንን በጎ ላልሆነ ነገር አጋልጠን መስጠታችን መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። መንቀፍ የሌላውን ስሜት ስለሚጎዳ፥ ሌላውን የበታችነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርግ በመ

ሆኑ ጎጂ እንጂ ጠቃሚ አይደለም። ስለዚህ ነቃፊዎች አንሁን። ሰው በሁለት አቅጣጫ ነቀፌታ ይደርስበታል። ብዙ ጊዜ ሌላውን ስንነቅፍ "የነቀፍኩት ስለምወደው ነው" ብለን ራሳችንን ስለምናሳምን፥ "ነቀፌታ መልካም ነው" እንላለን። ስንነቀፍ ደግሞ ነቀፋው ስለሚቆረቁረን "መንቀፍ ክፉ ነው" እንላለን። ያም ሆነ ይህ ሰው ነቀፋ ከሁለት አቅጣጫ ይደርስበታል። ይኸውም፥ አንደኛ፥ ሰው ራሱን ይነቅፋል። ሁለተኛ፥ በሌሎች ይነቀፋል። ከሁለቱም አቅጣጫ የሚወረወሩት ነቀፋዎች በአግባቡ ካልሆኑ፥ በሰው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርሱ የታወቀ ነው።

1. <u>ሰው፥ ራሱን በራሱ ሲነቅፍ (Self-Criticism)</u>

በደረሰባቸው አንዳንድ የተፈጥሮ ጉዳት ምክንያት የዝቅተኛነት ስሜት የሚሰማቸው ሰዎች አሉ። በሕይወቱ ሁሉም ነገር የተሟላለት ማንም ሰው የለም። አንዳንዱ በአካሉ ላይ ጉድለት ይኖርበታል። ጤናማ አካል ያለው ደግሞ ሌላ ዓይነት ጉድለት በሕይወቱ ይኖረዋል። ሰው ያልተሟላለትን፥ የሌለውን ነገር ባሰበ ቁጥር፥ ስለ ራሱ የሚኖረው ግምትና አስተያየት እየወደቀ ይመጣል። ያንን በማሰብ ፈንታ ግን ያለውን፥ የሆነለትን፥ ማድረግ የሚችለውን ሲያስብ ልቡ በምስጋና የሚሞላ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ራሱም ትክክል የሆነ አስተያየትና ግምት ይኖረዋል። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችም ብንሆን ይወደናል። እግዚአብሔር ከወደደን፥ እኛም ራሳችንን እንድንወድ ይፈልጋል። እንግዲህ እርሱ የፈጠረውን "እኛነታችንን" የምን ጠላ፥ የምንንቅና የምንነቅፍ ከሆንን፥ እግዚአብሔርን መውደድ አንችልም። እግዚአብሔር የወደደውን "እኛነታችንን" እንዴት መጥላት እንችላለን? ራሳችንን ስንነቅፍ፥ የሠራንን እግዚአብሔር መንቀፋችን መሆኑን እንረዳ። "የምስጋና ዓለም" ጌታ እግዚአብሔር ሲሆን፥ "የነቀፌታ ዓለም" ንጉሥ ግን ሰይጣን ነው። የሌሎችን ነቀፌታ ለማስተናገድ ብንፈተንም፥ ራሳችን በራሳችን ላይ የምንሰነዝረውን ነቀፌታ ግን ማስተናገድ ፈጽሞ የለብንም። አንዳንዶች "ራስን መንቀፍ" መንፈሳዊነት መስሎ የሚሰማቸው እንዳሉ እናውቃለን።

ሰዎች ራሳቸውን መንቀፍ ሲጀምሩ የራሳቸው ጠላት ይሆናሉ። ስለራሳቸው የሚሉትን ማመንና መቀበል ሲጀምሩ፥ ከሌላው ሰው ጋር

መጣጣምና መገባበት እያቃታቸው ይመጣል። ራሳቸውን "አልረባም፣ ሞኖር ነኝ፣ ደንቆሮ ነኝ፣ ምንም ዓይነት ችሎታ የሌለኝ ሰው ነኝ" ሲሉ፥ ራሳቸውን ካሉት ሁኔታ ወይንም ደረጃ ውስጥ እንደሚከቱ የታወቀ ነው። "ነን" ብለን የምናስበውን የመሆን ዝንባሌ እንዳለን ግልጽ ይጠቅመናል። "የራስ ኑሮታ" መሆን "የራስ አጥሬ" መሆን ነው። በሕይወታችን ድካም ስናይ፥ ድካማችንን ወደ እግዚአብሔር ይዘን በመቅረብ ከእርሱ ይቅርታን ተቀብለን፥ ራሳችንን ለማሻሻል እንጥራለን። ራሳችንን ስንነቅፍ ግን፥ ራሳችንን ለማሻሻል ጉልበት እያጣን እንሄዳለን። ይህንን ስንል፥ "እንደ እኔ ታላቅ ሰው ግንም የለም" እያልን ስለራሳችን እያጋነንን የትምክህት ቃል እንናገራለን ማለት አይደለም። "ራስን በመንቀፍ" ጉዳት እንዳይደርስብን፥

(1) ድካማችንን ብቻ ሳይሆን ብርታታችንንም እንይ። አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካላደረግን፥ ያደረግናቸውን በጎ ነገሮች ችላ ብለን በድካማችን ላይ የበለጠ ትኩረት ማድረግ ልማድ ሊሆንብን ይችላል። ድካማችን ብቻ ላይ ትኩረት ከሰጠን፥ ራሳችን የራሳችን ጠላት እንሆናለን። ተሸናፊዎች እንዳንሆን፥ የራሳችን ወዳጆች እንሁን። ድካም ብቻ ሳይሆን፥ መልካም ነገርም እንዳለን አንርሳ። ይህን ስንል ስህተታችንን ወይም ድካማችንን አንይ ማለት አይደለም። ለራሳችን ሀቀኞች እንሁን ማለታችን ነው።

(2) ትክክል (በጎ) የሆነ ነገር ስናደርግ፥ በራሳችን ደስ ይበለን። ብዙ ጊዜ ሰው ትክክል ያልሆነ ነገር ሲሠራ ይቀጣል። በጎ ነገር ሲያደርግ ግን ችላ ይባላል እንጂ አይሸለምም። ሁላችንም ባሕሪያችንን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን። ዕድገታችን እንዲቀጥል፥ ስናሻሽል በራሳችን ደስ ሊለን ይገባል።

(3) የሌሎችን መልካም አስተያየት በደስታ እንቀበል። አንዳንድ ሰዎች "ከማም ጥሩ ነው የሠራኸው" ሲባሉ ብዙ ጊዜ የሚሰጡት መልስ "ይሄ፣ ያህል አይደለም" የሚል ነው። ይሄን ሲሉ፥ አስተያየት የሰጠውን ሰው ግምት ልክ አይደለም ማለታቸው እንደሆነ አይረዱትም። የሰዎችን መልካም አስተያየት መቀበል የበለጠ እንድናሻሽል ይረዳናል።

(4) ያለፈውን ረስተን የእግዚአብሔርን ጸጋ እንቀበል። አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት "እኔ የማልረባ ትል ነኝ" እንበል። እኛ የእግዚአብሔር ወዳጆች ነን (የዮሐ. 15፥15)። እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች ነን (ሮሜ 8፥16)። እግዚአብሔር ነቱሩን ሳይሆን ምስጋናን ይወዳል። ስለዚህ ሰዎች ሁልጊዜ ባለማጸረጥ ራሳቸውን ሲነቅፉ ደስ አይለውም። ኃጢአታችንን በጌታ ፊት አቅርበን ከእርሱ ይቅርታን ከተቀበልን በኋላ፥ ላለፈው ድካማችን ራሳችንን አንቀጥቅጠው።

2. <u>በሌላ ሰው መነቀፍ</u>

መነቀፍ፥ መሰደብና መናቅ ምን ያህል ሰውን ሊጎዳ እንደሚችል ለመግለጽ ዊልያም ዲህም (William Diehm) "መንቀፍ" (Criticizing) በሚለው መጽሐፉ መግቢያ ላይ በልጅነቱ ያለፈበትን ከባድ ጊዜ እንዲህ በማለት ይገልጻል።

"የአምስት ዓመት ልጅ ሆኜ በፖሊዮ በሽታ ተመትቼ በሀመም ከመሰቃየቴ ሌላ፥ ሁለቱ እግሮቼ ፍጹም ሽባ በመሆናቸው የምራመደው በምርኩዝ ነበር። አንዳንድ ቀን የጎረቤት ልጆች እየተራሯጡ ካሰ ሲጫወቱ ከቤቴ በራፍ ላይ ቁጭ ብዬ አያቸዋለሁ። አንድ ቀን እንደተለመደው የጎረቤቴ ልጆች ኳስ ሲጫወቱ ምርኩዜን ተደግፌ ሳያቸው፥ በእኔ ሁኔታ እየሳቁ፥ 'ምን ታያለህ አንተ ልጅ? ከዚህ ጥፋ። እኛ ሽባ ልጅ ማየት አንፈልግም' አሉኝ። ይህን ሲሉኝ ዓይናቸው በፅንባ ተሞልተው፥ እነዚያን ሽባ የሆኑትን እግሮቼን እየኮተኮተ፥ ከቤታችን ጓሳ አባቴ ከሰል ከሚያስቀምጥበት ክፍል ውስጥ ገባሁ። ኮተከመረው ከሰል ላይ ቁጭ ብዬ የከሰል መያዣውን ቆርቆሮ በቦክሰ እየመታሁ አለቅስሁ፥ እራገምና 'እንዲህ ነኝ፥ እንዲያ ነኝ' እያልኩ በግውቀው መዋር ሰም ሁሉ አራሴን እጠራ ነበር። ሽባ በመሆኔ ራሴን ጠላሁት። በዚያን ጊዜ በሕይወት መኖርን ጠልቼ ነበር።

ላለቅስና ቆርቆሮ ሰደበድብና ሰራም እናቴ ሰምታ እየ ሮጠች መጣች። ከከሰል ግጠራቀሚያው ክፍል አንገቷን

ገባ አድርጋ ከስተር ባለ ድምጽ፥ 'ዊልያም! በፍጥነት ከዚህ ወጥተህ ወደ ቤት ና' አለችኝ። ምርኩዜን እንደተደገፍኩ ብድግ ብዬ፥ የዕርግማን ቃል ከአፌ በመውጣቱ ቅጣት ይደርስብኛል ብዬ እየፈራሁ 'እሺ እማዬ!' አልኳት። ባለኝ ጉልበትና ጎይል ራሴን እየጎተትኩ እንደምንም ብዬ ወጥ ቤት ከአለው በርጩማ ላይ ሄጄ ተቀመጥኩ። ሰውነቴ ሁሉ በከሰል ተሸፍኖ ነበር። ከሰል በሆነው ፊቴ ላይ ዕንባዬ ፈሰሰ ልዩ የሆነ መልክ ሰጥቶኝ ነበር። እናቴ በዚያን ጊዜ ሳህን እያጠበች፥ የደረቁትን ሳሆኖች መደርደሪያው ላይ ትደረድር ነበር። ሥራዋን እስክትጨርስ ድረስ ምንም ቃል አልተናገረችኝም። ከመፍራቴና ከመጨነቄ የተነሳ ያቺ ጥቂት ጊዜ እንደ ዘላለም ረጅም ሆና ተሰማችኝ። በመጨረሻ ወደ እኔ ዞር ብላ 'እኔና አባትህ በጣም ጥሩ ኑሮ፥ በጣም ጥሩ ቤት እንዲኖርህ አቅማችን የፈቀደውን ሁሉ እያደረግንልህ ነው' አለችኝ። እኔም እየተንሰቀሰቅሁ፥ 'እውነት ነው እማዬ! ቆንጆ ቤት ነው ያለን' አልኳት። 'ከጎረቤት ልጆች መካከል አንዱ ቤትህ አይረባም፥ ቆሻሻ ነው፥ የአሳማ መኖሪያ ይመስላል ቢልህ ምን ትለዋለህ?' ብላ ጠየቀችኝ። እኔም የእኛ ቤት የማይረባ፥ ቆሻሻና ያሳማ መኖሪያ ይመስላል' እንዲለኝ አልፈቅድለትም' ብዬ መለስኩላት። እናቴም ፈገግ ብላ፥ ለስለስ ባለ ድምጽ፥ 'የእኔ ልጅ እግዚአብሔር ሸባ የሆነ አካል ለምን እንደሰጠህ እኔ አላውቅም። ይሁን እንጂ፥ በዚህ ወቅት ይሄ አካልህ በቂህ ነው። እስከ ሕይወትህ መጨረሻ ድረስ የምትኖረው ይሆንን አካል ይዘህ ነው። ስለሆነም፥ 'ቆሻሻ! የማይ ረባ!' እያልክ ራስህን መጥራትህን አቁም አለችኝ።"

ይህ ሰው ነቀፋ፥ የሰዎች ክፉ ቃል ውስጥን ሰንጥቆ በመግባት ምን ያህል እንደሚጎዳ የተገነዘበው ገና የአምስት ዓመት ልጅ ሆኖ ነው። መናቅ፥ መገሥት የአዕምሮ ጭንቀት ያስከትልና ደስታን ያሸ ሻል። ይህ ሰው በፖሊዮ ምክንያት ከደረሰበት አካለ ስንኩልነት ይበልጥ በሕይወቱ የነበረበት ከፍተኛ ትግል "ነቀፌታ" ነው። ልዩ ልዩ ችግር ደርሶባቸው "የሥነ ምክር" እርዳታ ከሚፈልጉት ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ የሰዎችን ነቀፋ በምን ዓይነት ሁኔታ መቀበልና

ማስተናገድ እንዳለባቸው ያልተረዱ ናቸው። የሚገርመው ነገር፥ በእኛ ላይ ሌሎች የነቀፋ ቃል ሲሰነዝሩብን ይገባናል፥ እኛ በሌሎች ላይ የምንሠነዝረው የነቀፋ ቃል ግን ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል አይገባንም።

አግባብ ያልሆነ ነቀፌታ ለብዙዎች የልብ ስብራት ምክንያት ሲሆን እንጂ፥ ሲጎላ አናይም። የብዙዎችን ትዳር ከሥሩ ነቅሎ ሲጥል እንጂ ሲያቀራርብ አናይም። ነቀፌታ የባልና ሚስትን አለመስማማት በማጥፋት ፈንታ ይበልጥ ሲያራርቅ፥ በመካከላቸው የጥል ግድግዳ ሲያቆም እናያለን። "ነቀፌታ" ብዙዎችን ከመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሸሹ አድርጓል። የያዙትን ጠቃሚ አሳብ በሥራ ላይ እንዳያውሉት ብዙዎችን ተስፋ አስቆርጧል። ነቀፌታ በጎነት በውስጡ የለበትም። ያጠፋል፥ ይከፋፍላል። የሰውን ስሜት ይጎዳል። ነቀፌታ የበዛበት ሰው ስለ ራሱ ዝቅተኛ አስተያየት እንዲኖረውና ራሱን እንዲጠላ ይሆናል። ነቀፌታ ሰዎችን ተስፋ አስቆርጦ የመንፈስ ጭንቀት እንዲደርስባቸው ያደርጋል። ነቀፌታ ጠብን ይጭራል፥ አን ድነትን ያፈርሳል። ሁልጊዜ ግማሽ እውነት እንጂ ሙሉ እውነትን አይዝም። ሁልጊዜ የሚያተኩረው በአንድ ወገን ብቻ ነው። በነቃፊው እንጂ በተነቃፊው አቅጣጫ አይመለከትም። እግዚአብሔርም ይህን የነቃፊነት መንፈስና ዝንባሌን አብዝቶ ይጠላዋል። ለእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር ገና በባርነት በግብጽ ምድር በነበሩበት ዘመን እንኳን ያሰባቸውና በነ ያደረገላቸው ሕዝቦች ነበሩ። ይሁን እንጂ በበረሃ ውስጥ ወደ ተስፋው ምድር እየመራ ሲወስዳቸው ማጉረምረማቸው፥ ነቃፊና ስህተት ለቃሚ የሆነው ጠባያቸውና መንፈሳቸው እግዚአብሔር ሊታገሰው የማይችለው የልብ ህመም እንደሆነበት እናውቃለን።

ከነቀፌታ ፍጹም ነጻ የሆነ ሰው የለም። ሁላችንም መጠኑ ይለ ያይ እንጂ በመነቀፍም ሆነ በመንቀፍ ውስጥ እናልፋለን። ወላጆች ልጆቻቸውን፥ ልጆች ወላጆቻቸውን፥ ሚስት ባሏን፥ ባል ሚስቱን ይነቅፋሉ። ነቀፌታ በማብዛት የኑሮ ጓደኛቸውን ባሕሪ መለወጥ የሚችሉ መስሎ የሚታያቸው ባልና ሚስት አሉ። ያልተረዱት እውነት ቢኖር "ነቀፌታ" በልባቸው ያለውን ፍቅር ቀስ በቀስ ማጥፋቱ ብቻ ሳይሆን ደስታ የራቃቸው ሰዎች የሚያደርጋቸው መሆኑን ነው። የምንሰማቸው ነቀፋዎች እነዚህን ይመስላሉ.....

- *"...ሸሚዝህና ከራባትህ ጨርሶ አይሄድም። የእለቱን አለባበስ ልብ ብለህ ተመልከት። ለመሆኑ አንተ ከእርሱ ታንሳለህ እንዴ?"*
- *"...ሁልጊዜ ለብሰሽ ቶሎ አትወጪም። ቤተ ክርስቲያን እንጂ ዳንስ ቤት የምትሂጂ መሰለሽ እንዴ!"*
- *"...ኮትህ ተጨማዶ ምን ይመለከል! ኮትህን ተንተርሰህ የተኛህ ትመስላለህ። ምን ነክህ 'ሚሱቱ አትነግረውም ወይ?' በማለት እኔን ታሳደገኸኛለህ!"*
- *"...ገንዘብ ማጥፋት ደስ ይልሻል፣ ምን አለ በአትምሽ መናር ብትምከሪ!"*

ትክክል ያልሆኑ ነቀፌታዎች ለባልና ሚስት መጨቃጨቂያ ምክንያት ከመሆናቸው በቀር ገንቢነትም የሌላቸው፣ ለግሪም፣ ለግሱተ ካክል የተወረወሩ ቢሆኑም፣ ከሚያለሙት ይልቅ የሚያበላሹት ይበልጣል። ነቀፌታ ሁልጊዜ ሌላውን ለማጥፋት ለመጉዳትና አሳንሶ ለማሳየት ብቻ አይደለም። ከጥሩ ልብ፣ በጥሩ መንፈስ የሚመጣ ነቀፌታም አለ። ወላጆች ልጆቻችንን በየጊዜው ሲያጠፉ እንነቱፋቸ ዋለን። ዓላማችን ልናጠፋቸው ሳይሆን ልናለማቸው አስበን ነው። ችግራችን ግን ስሚታቸውን ሳንሰብር ግሪም አለመቻላችን ነው። ልጆቻቸውን የሚወዱ ወላጆች ልጆቻቸው በጥሩ ሁኔታ እንዲያድጉላቸው ስለሚፈልጉ፣ በጥንቃቄ የልጆቻቸውን እርምጃ ይከታተላሉ። በዚህ ምክንያት ሳያውቁት ልጆቻቸውን መንቀፍ ልማድ ይሆንባቸዋል። በዚህም ከሚጠቅሟቸው ይልቅ ይጎዷቸዋል።

ወላጆች ባለማወቅ በልጆቻቸው ውስጥ የማይወዱትን ጠባይ በግሪም ፈንታ ነቀፋ ያበዛሉ። ጸባያቸውን የሚያርመበትን ዘዴ በመፈለግ ፈንታ በልጆቻቸው ላይ ነቀፋ ስለሚያበዙ ወደፊት መታ ረምን እንዲጠሉ ያደርጓቸዋል። በባልና ሚስትም መካከል ይህን ዓይነት ችግር ይታያል። "ባሌን ስለምወደው እንዲያስተካክል የምፈልገውን ነገር እነግረዋለሁ" ግለት የተለመደ አነጋገር ነው። እዚህ ላይ ሁለቱም መጠንቀቅ ያለባቸው እርግታቸው ገንቢ እንጂ አፍራሽ እንዳይሆንባቸው ነው። አንዳንዶች የሚነቱፉት የመንቀፍ ልማድ ስላላቸው ብቻ ስለሆነ፣ ጓደኛቸው እንዲያስተካክል የሚፈልጉትን ነገር

ለግሪም መከራ ሲያደርግ አይተባበሩትም። በአሁኑ ጊዜ በባልና ሚስት መካከል የመፋታት ትልቅ ምክንያት ከሆኑት ነገሮች አንደኛው፣ እርስ በርስ መነታቀፍ ነው። ባልና ሚስት ሌላውን የመንቀፍ በሌላው ላይ ስህተት የመፈለግ ጸባይ ካላቸው፣ ፍቅራቸውን ከማቀዝቀዙም በላይ፣ የማያቋርጥ ግጭት ከኑሯቸው አይጠፋም። ነቀፋ በሁለት ይከፈላል። አንደኛው "የሚያንጽ" ሲሆን፣ ሁለተኛው "የሚያፈርስ" ነው። የዝህን ሁለት ዓይነት ነቀፋዎችን ልዩነት ባለማወቃቸው ነው አንዳንዶች "እናንጻለን" ብለው የሚያፈርሱት።

3. ሰዎች ሌላውን የሚነቅፉበት ምክንያት

3.1. ለመጥቀም ሲሉ የሚነቅፉ

ነቀፌታ የሚመነዘረው ሁልጊዜ ሌላውን ለማጥፋት፣ ለመጉዳትና አሳንሶ ለማሳየት ብቻ አይደለም። ፍቅር ከሞላው ልብ የሚፈልቅ ነቀፋ አለ። ከጥሩ ልብ በጥሩ መንፈስ የሚመጣ ነቀፋ አለ። ወላጆች ልጆቻቸውን ሲያጠፉ ይነቱፋሉ። ዓላማቸው ለማጥፋት ሳይሆን ለማልማት ነው። ችግራቸው ግን ስሚታቸውን ሳይነዱ ግሪም ወይም ግሱተካክል አለመቻላቸው ነው። ነቀፌታ በልጆቻቸው ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ስለማያውቁ ልጆቻቸውን መንቀፍ ልማድ የሆነባቸው ብዙ ወላጆች አሉ። አንዳንድ ወላጆች በራሳቸው ጉዳይ ላይ ብዙ ስለሚጠመዱ ለልጆቻቸው ጊዜ የላቸውም። ወደ ልጆቻቸው የሚመለከቱት ጥፋት ሲያጠፉ ለመቆጣት ወይም ለመቅጣት ብቻ ነው። አንዳንድ ልጆች ይህን ከተገነዘቡ፣ ወላጆቻቸውን ለመሳብ ሲሉ ሆን ብለው የሚያጠፉበት ጊዜ አለ። ወላጆች በቁጣ ቃል ልጃቸውን "አንተ ልጅ ተው ብዬሃለሁ" ይላሉ። ልጁም ተው የተባለውን ትዕዛዝ በመተበል ፋንታ፣ "ለምን?" ብሎ ይጠይቃል። አንዳንድ ወላጆች ምክንያቱን በማስረዳት ፈንታ፣ ተቆጥተው "ተው ስልህ መተው ነው! ምክንያቱን አትጠይቀኝ" ይላሉ። ልጁ የሚያደርገው ነገር ትክክል ቢሆንም ባይሆንም፣ ይሄ ሁኔታ ወላጅን በከፍተኛ፣ ልጅን ግን በዝቅተኛ ደረጃ ያስቀምጣል። በልጁ ላይ የዝቅተኛነት መንፈስ እንዳያመጣ የሚፈልግ ወላጅ፣ "ተው!" ያለበትን ምክንያት ማስረዳት አለበት። ሌላ ምክንያት ባይኖራቸውም እንኳን፣ "የምታደርገው

ነገር ስለሚያበሳጨኝ ነው" ብለው መልስ ቢሰጡት፥ "ተው" ያሉበት ምክንያት ልጁን አለአግባብ ለመንቀፍ እንዳልሆነ ይገነዘባል።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ለማረም የምንሞክረው፥ ሳንጣላ አብረናቸው መኖር እንድንችል ነው። ይሁን እንጂ፥ በፍቅር ወይም በአግባቡ ካላደረግነው መጥፎ ውጤት ያስከትላል። ቅርባችን ካልሆነ ሰው ነቀፌታ መቀበል የሚያቅተን ብዙ ጊዜ ነቀፌታቸው በፍቅር የተሞላ ስለማይሆን ነው። ቅርባችን ከሆኑትም እንኳን ቢሆን ዕርማታቸው በፍቅር ካልሆነ፥ መቀበል ያቅተናል። ልጆች ነቀፋ ሲበዛባቸው የወላጆቻቸውን ፍቅር መጠራጠር ይጀምራሉ። "አባቴ ቢወደኝ ኖሮ እንዲህ አይልኝም ነበር" ይላሉ። አንዳንድ ጊዜ ወላጆች የልጆቻቸውን ጠባይ በማረም ፋንታ ዝም ብለው ይነቅፋሉ። መንቀፋቸውን እንጂ በልጃቸው ላይ የሚያስከትለውን መጥፎ ነገር አይረዱም። በዚህ ዓይነት እየተነቀፉ የሚያድጉ ልጆች ትልቅ ሲሆኑ፥ በሥራቸውም ሆነ በትዳራቸው ላይ አንዳንድ ነገር እንዲያስተካክሉ ወይም እንዲያርሙ ሲነገራቸው፥ መቀበል ያቅታቸዋል።

3.2. ኃላፊነት ተሰምታቸው የሚነቅፉ አሉ

ብዙ ሰዎች ኃላፊነታቸውን ያከብራሉ። በኃላፊነት ሥፍራ ከተቀመጡ፥ "ማረም፥ ማስተካከል አለብኝ፥ ስህተት ሳይ ዝም አልልም" የሚሉ ጠንካራ ሰዎች አሉ። ዓላማቸው ለማጥፋት ሳይሆን ለማስተካከል ነው። ይሁን እንጂ ነቀፌታቸው ሌላውን የሚቆራርጥ፥ የሚያሳንስና የሚሰባብር መሆን የለበትም። ሌላው ሰው እንዲሆን ወይም እንዲያደርግ የሚፈልጉትን ነገር ጠንካራ ቃል ሳይሰነዝሩ በአግባቡ መንገር ወይም በጥበብ ማስረዳት ይገባቸዋል። አንዳንድ አለቆች ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውን የሚያሳዩት በትንሹም ሆነ በትልቁ ትዕዛዝ እያበዙ፥ "ይሄና ያ አልተደረገም" በማለት ከሥራቸው ያሉትን ሰዎች በመንቀፍ ነው። እነዚህን ከመሳሰሉ አሠሪዎች ጋር አብረን የምንሠራ ከሆነ፥ ይህን የሚያደርጉት ለክፉት ሳይሆን የተሳሳተ የአስተዳደር ዘይቤ በመጠቀማቸው መሆኑን ተገንዝበን በመበሳጨት ፈንታ በትዕግሥት ልናልፋቸው ይገባል። አንዳንድ አለቆች፥ አለቃው ወይም ዋናው ማን እንደሆነ ለማሳየት ይሞክራሉ። ብዙ ትዕዛዝ በመስጠትና ከሥራቸው ያሉትን ሠራተኞች በመንቀፍ አለቅነታቸውን ለማሳየት

የሚሞክሩ ሰዎች፥ ማስተዋል የጎደላቸው ናቸው። ትንሽ እንኳን ስህተት መስሎ የሚታያቸውን ነገር ካዩ በቀላሉ አያልፉትም። ነቀፌታ በግብዝታቸው የእነርሱን ደረጃ የሚያሳድግላቸው፣ በመንቀፋቸው ክብር የሚያገኙ፣ አለቅነታቸው የሚታይላቸው ስለሚመስላቸው ሁል ጊዜ ይነቅፋሉ። ስለሆነም፥ እነዚህን በሚመስሉ ሰዎች ስንነቀፍ ሁኔታውን ችላ ብለን እንለፈው እንጂ፥ አንበርግባቸው።

3.3. ለሚወዷቸው ሰዎች ተቆርቋሪው የሚነቅፉ አሉ

የሚወዷቸው ሰዎች የተሳሳቱ ሲመስላቸው ለማረም ቶሎ ይነሳሉ። ይህን ዓይነት ስሜት በሁላችንም ላይ አለ። የተሳሱት ነገር ስናይ ዝም ማለት አይሆንልንም። በዚህ ምክንያት ነው የነቀፋ ቃል ከአፋችን ሲወጣ የሚሰማው። ይህንን ከተረዳን አንዳንድ ጊዜ በበጎ መንፈስ ተነሱተው ሊያርሙን በመፈለግ የነቀፋ ድምጽ በሚያሰሙን እንዳንድ ሰዎች ቅር መሰኘት አይገባንም። ብዙ ጊዜ ሲደጋገምና ቋንቋው በጣም ጠንከር ሲልብን ግበሳጨቱ ግልጽ ነው። ቢሆንም ነቀፋው የተሰነዘረው በክፉ መንፈስ ባለመሆኑ በትእግስት ልናልፈው ይገባል።

በመሻሻላችን፣ በማደጋችንና በማሸነፋችን ደስ የሚላቸው በአካባቢያችን ብዙ ሰዎች አሉ። የምንሠራውን ሥራ በትክክል ስንሠራ ደስ ሲላቸው፥ አሠራራችን ልክ መስሎ ያልተሰማቸው እንደሆነ ደግሞ ቅር ይላቸዋል። ስለሚወዱን፥ ስለሚቆረቆሩልን ስንሳሳትና ስናጠፋ ዝም አይሉንም። የሚሰማቸውን ዕውነቱን ይነግሩናል። የእነዚህ ሰዎች ነቀፌታ አጥፊ ሳይሆን ገንቢ ነው። ምናልባት የአነጋገር ጥበብ ላይኖራቸው ይችላል። እኛ በምንፈልገው ዓይነት ቋንቋ አይነግሩንም ይሆናል። ስለሆነም ነው እንደሚወዱንና ለእኛ ደህንነት ሲሉ እንደሚያደርጉት እያወቅን በአነጋገራቸው የማንጎዳው። ሰው ሁሉ በሕይወቱ ብዙ ስህተቶችን ይሠራል። የሚሠራውን ሥራ በቅርብ ሆኖ እያየ ሲያጠፋ "አጥፍተሃል" የሚለው ሰው የሌለው የበለጠ ስህተት ይሠራል።

3.4. የተደበቀ ኢጅንዳ ኖራቸው የሚነቅፉ አሉ

አንድን መሳይ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመዘምራን የምታገለግል እህት ነች። በመንፈሳዊ ሕይወቷ ብርቱና ጠንቃቃ

ልጅ ነች። ማንኛውም ወጣት ክርስቲያን የሚናርበትን ዓይነት ደካም እንጂ፥ ይህን ያህል በሕይወቷ ጎልቶ የሚታይ የምትለማመደው ኃጢአት ያለም። አንድ ዕውደ፥ ክሰምንታዊ ፕሮግራም መጨረሻ ላይ ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መካከል አንዱ "አንቺን መሳይ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ዛሬ ልናነጋግርሽ እንፈልጋለንና ቶሎ ወደ ቢሮ እንድትመጪ" ሲል ነገራት። አንቺን መሳይ ልቧ ድንጥጥ አለ። ተንቀጠቀጠች። "ምን አጥፍቼ ይሆን?" በማለት ራሷን እየመረመረች ወደ ስብሰባው ገባች። ሁሉም ሽማግሌዎች ተገኝተዋል። ስብሰባውን የሚመራው መጋቢ፥ "ዛሬ አንቺን መሳይ፥ ዛሬ የተሰበሰብነው በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚታዩትን አንዳንድ ጤናማ ያልሆኑትን ነገሮች ለማጥራትና ለማስተካከል ነው። እንደምታውቂው እግዚአብሔር ይህችን ቤተ ክርስቲያን እንድንጠብቅ፥ እንድናስተዳድር ኃላፊነት ሰጥቶናል። የተሰጠንን ኃላፊነት ባንጠብቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂዎች ነን። በቤተ ክርስቲያናችን ኃጢአት እንዲሰለጥን አንፈልግም" አለ። የአንቺን መሳይ ልብ በኃይል እየመታ፥ "ምን ዓይነት ኃጢአት ሠርተሻል ልባል ይሆን?" እያለች በውስጧ ታሰላስላለች።

መጋቢው ንግግሩን በመቀጠል፥ "ቤተ ክርስቲያናችን በውጪ ባሉት ሰዎች ዘንድ ያለንተፋ ሆና እንድትገኝ እንፈልጋለን። ግን አንዳንድ አማኞች ሕይወታቸውን በሥርዓት መምራት ባለመቻላቸው ምክንያት ሁላችንም እንድንነቀፍ አንፈልግም። ስለዚህ በሕይወታቸው በአግባቡ የማይራመዱትን መዕመናንና አገልጋዮች እየጠራን ግለጠ ንተት መምከርና መገሰጽ አለብናል። አንቺንም ዛሬ የጠራንሽ በዚህ ምክንያት ነው። አንቺ በመዘምራን ጓድ ውስጥ ብታገለግይም መንፈሳዊ ሕይወትሽ የተዘናጋና ደካማ ነው። እንዲያውም አንቺ ቤተ ክርስቲያን የምትመጪው አንዳንድ ሰዎችን ለማየትና የትዳር ጓደኛ ለመፈለግ ብቻ እንደሆነ ይወራል። ውስጣዊ ሕይወትሽን የሚያውቁ አንዳንድ ቅን ወንድሞች በአንቺ ምክንያት ይሰናከላሉ ብለን እንፈራለን። ስለዚህ ዛሬ ልንነጋርሽ የምንፈልገው ሕይወትሽን እንድታስተካክይ ነው። እስከታስተካክይ ድረስ ከመዘምራን ጓድ ለጊዜው ታግደሻል። ጥያቄ አለሽ?" በማለት ንግግሩን ይዘጋል። አንቺን መሳይ ለጥቂት ደቂቃ ጸጥ ካለች በኋላ ስቅ ስቅ ብላ አልቅሳ እየተንቀጠቀጠች ብድግ ብላ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ፥ ምንም ዓይነት ጥያቄ

የለኝም" ብላ ወጣች። አንቺን መሳይ፥ ዓለም በላይዋ ላይ የተደፋባት መስሎ ተሰማት። እንዴት ወደ መኪናዋ ሄዳ መኪናዋን እስክታ እየነዳች እንደሄደች ሳታውቀው እቤቷ ገባች። አልጋዋ ላይ ተደፍታ ስቅ ስቅ ብላ እራሷን መግታት እስከሚያቅታት ድረስ አለቀሰች። ትንሽ ብስጭቷ በረድ ሲልላት ግሰብ ጀመረች። "ለምንድነው እንደ ዚህ በታላላት ጦር ሊወጉኝ የተነሱት? ከመካከላቸው ማንን አሰቀይሚ ይሆን?" እያለች ራሷን ስትጠይቅ፥ አንድ ነገር ትዝ አላት። ለካስ ከመካከላቸው አንደኛው የኑሮ ጓደኛ እንድትሆነው ጠይቋት "እምቢ!" ብላዋለች። ለዚያ ቁጭት መውጫ እንደሆነ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀባትም።

አንቺን መሳይ ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን መሄዷን አቆመች። መንፈሳዊ ሕይወቷ እነርሱ እንዳሉት ስላልነበረ፥ ከጌታ ጋር የበለጠ ተጣብቀች እንጂ ከጌታ አልሸሸችም። አሜሪካውያን ቤተ ክርስቲያን መሄድ ጀመረች። የሚገርመው ነገር አንቺን መሳይ ከቤተ ክርስቲያን መቅረቷ እነዚያን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ይህን ያህል አላሳሰባቸውም። ለዚህ ነው ከእነርሱ መካከል አንዱም ሁኔታዋን ለማወቅ ሊፈልጋት ወይም ሊጠይቃት ያልመጣው። ታሪኩ የፈጠራ ይሁን እንጂ ይህን የመሰለ ሁኔታ ያጋጠማቸው፥ ከቤተ ክርስቲያንና ከክርስቲያኖች ሸሽተው ለብቻቸው ተገልለው የሚኖሩ እንዳሉ አጠራጠርም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምላሳቸው ሊሾለ፥ ሊያንጽና ሊያበረታታ ሲገባ ብዙዎችን የሚያስደነግጥ፥ የሚቆራርጥ፥ የሚፈርድና የሚኮንን እየሆነ የብዙዎች ሕይወት መሰናከያ ምክንያት ሆነዋል። መገሰጽ የሚገባቸው "አይገሰጹ" ግለታችን አይደለም። ሲገሰጹ "እጠፉ" የተባሉት ነገር እውነትነቱ በጥንቃቄ ተመርምሮና ተመዝኖ በፍቅር ይቅረብ ግለታችን ነው። ዋናው ዓላማ ቆርጦ ለመጣል ሳይሆን ለመጠገንና በአግባቡ ለማሳደግ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ከእናንተ መካከል በእምነቱ ያልጸና ደካማ ሰው ቢኖር በፍቅር ተቀበሉት እንጂ በአስተሳሰቡ አትፍረዱበት" (ሮሜ 14፥1) ሲል የሚመክረን።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የበለጠ እንዲከበሩ፥ እንዲፈሩ የሚያስደነግጥና የሚያስበረግግ ቃላት ሲጠቀሙ ይታያሉ። እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲጠራን ባሪያ፣ አሽከር፣ አገልጋይ እንድንሆን እንጂ በሕዝቡ ላይ አለቃና ገዢ እንድንሆን እንዳልሆነ መገን

ዘብ ያስፈልገናል። በተዋረደ መንፈስ ሕዝቡን ስናገለግል እግዚአብ ሔርና የምናገለግለው ሕዝብ መልሶ ያከብረናል። የምንወረውረው ኃይለኛ ቃል ግን ሰዎች እንዲሸሹን ያደርጋል እንጂ፥ እንዲቀርቡን እንደማያደርገን እንወቅ።

3.5. ራሳቸውን ከፍ ለማድረግ ሲሉ የሚነቅፉ አሉ

አንዳንድ ሰዎች በሄዱበት ሥፍራ ሁሉ የሌላውን ሰው ሥራ፥ የደከመበትና የለፋበትን ነገር አሳንሰው፥ አቋሽው፥ ነቅፈው ለመናገር የሚሞክሩት በውስጣቸው ትልቅ ችግር ስላለባቸው ነው። ከዚያ ከሚነቅፉት ሰው የተሻለ ሥራ ሠርተው ማሳየት እንደማይችሉ ያውቁታል። ስለሆነም በዚያ ሰው አካባቢ በሚሆኑበት ጊዜ፥ የበታችነት ስሜት ይሰማቸዋል። የሚሰማቸውን የበታችነት ስሜት ከፍ ለማድረግ ዓይነተኛ መንገድ አድርገው የሚጠቀሙት የዚያን ሰው ድካምና ልፋት በመንቀፍ፥ የማይረባ እንደሆነ አድርገው በማቅረብ ነው። በአሰባበኩ የሚደነቅ ከሆነ፥ ነቃፊው ያንን ለማበላሸት፥ *"እርሱ እስ አንበላ የሚሆነው መድረክ ላይ ነው፥ ከመድረክ ውጪ ግን ሕይወቱ ሌላ ነው። እናንተ የማታውቁት ብዙ ነገር አለ"* በማለት የሌላውን አዕምሮ ለማቆሸሽ፥ ሌሎች እንዳይቀበሉት ለማድረግ ይሞክራል። ይህን የመሰለ ሁኔታ የሚታየው በአሁኑ ዘመን ባለነው ሰዎች መካከል ብቻ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ዘመንም ሙሴ ይህን ዓይነት ነቀፋ ደርሶበታል። ለሙሴ ቅርብ ከነበሩት ሰዎች መካከል ወንድሙ አሮንና እህቱ ሚርያም ነበሩ። ሕዝቡ በወቅቱ ለሙሴ የነበረው አክብሮትና አድናቆት ከፍተኛ ስለነበረ፥ እነርሱ እንዳይታዩ፥ እንዳይከበሩ የሸፈናቸው መስሎ ስለተሰማቸው፥ ይህን መጋረጃ ገፎ ለመጣል የራሳቸውን ሙከራ እንዳደረጉ ታሪካቸው ይመሰክራል። እራሳቸውን በሕዝቡ ዘንድ አጉልተው በማሳየት መከበርን ለማግኘት የመረጡት መንገድ፥ ስለ ሙሴ ክፉ ነገርን በመናገር ነበር። ይህን ዓላማቸውን ለመፈጸም በሙሴ ላይ ምክንያት ይፈልጉ ነበር። ለጊዜው ቀዳዳ መስሎ የታያቸው የሚስቱን ሁኔታ በማንሳት ነበር። *"ሙሴ ከኩሽ ነገድ የሆነች ኢትዮጵያዊት በማግባቱ ምክንያት ሚርያምና አሮን በሐሜት እንዲህ ሲሉ ነቀፉት። እግዚአብሔር የተናገረው በሙሴ ለማካይነት ብቻ ነውን? በእኛስ ለማካይነት ተናግሮ የለምን?"* (ዘሁል. 12፥1-2) አሉ።

አሮንና ሚርያም የራሳቸውን ታላቅ ነብይነት ለመናገር የሞከሩት ሙሴን አሳንሶ ለሕዝቡ ለማሳየት በመሞከር ነው። አባባላቸው፥ *"ዓይ ናችሁን ከሙሴ ላይ አንሱ፥ ነብይ ሙሴ ብቻ አይደለም። እኛም ነብዮች ነን"* ግለታቸው ነበር። በዚያን ወቅት የስንቶቹን ልብ በሙሴ ላይ እንዳሸፈቱ አናውቅም። ሙሴ አሮንና ሚርያም ለሰነዘሩበት ነቀፌታ መልስ ለመስጠት ብዙ ጥረት ሲያደርግ አናየውም። ይሁን እንጂ ሁሉን ማየትና መስማት የሚችለው ጌታ ለሙሴ ጠበቃ ቆመ ለት። ሙሴን፥ አሮንን እና ሚርያምን ሦስቱን ከድንኳኑ ደጃፍ አቁሞ እንዲህ አላቸው። *"እነሆ እኔ የምነግራችሁን አድምጡ! በመካ ከላችሁ ነቢያት ቢኖሩ ራሴን የምገልጣላቸው በራዕይ ነው፥ በሕል ም አነጋገራቸዋለሁ፥ ከአገልጋዬ ከሙሴ ጋር የምነጋገረው ግን ከዚያ በተለየ ሁኔታ ነው፥ እርሱ በቤቴ የታመነ ነው፥ ስለዚህም እኔ ከእርሱ ጋር ቃል በቃል በግልጥ እነጋገራለሁ እንጂ ስውር በሆነ አነ ጋገር አልነገረውም። እንዲያውም እርሱ እኔን በግልጥ አይቶኛል፥ ታዲያ እናንተ አገልጋዬ ሙሴን በመንቀፍ የሐሜት ቃል ለመናገር እንዴት ደፈራችሁ"* (ዙልቁ 12፥6-8)።

አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን አቋምና ያላቸውን ውስጣዊ የዝቅ ተኛነት ስሜት ከፍ ለማድረግ ከእነርሱ የተሻሉ ናቸው ብለው የሚ ያስቧቸውን ሰዎች በነቀፋ መልክ ገፍተው ይጥላሉ። ይህንን ዘዴ በሕዝቡ ላይ ለመንገሥ ትልቅ ጉጉት የነበረው አቤሴሎምም ተጠቅ ሞበታል። *"እኔ ንጉሥ ብሆን ይህን አሳዛኝ ሁኔታ አጠፋላችሁ ነበር"* ይላቸው ነበር። የዘመኑ የፖለቲካ ሰዎችም ይህንን ዘዴ ሲጠቀሙ እናያለን። ራሳቸውን የተሻለ አድርገው ለማሳየት፥ የተወዳዳሪያቸውን አቋምና ፍልስፍና አጨልመው ያቀርባሉ። ድካም ቢኖርበት ያንን ድካም ኢጋልጠው ለሕዝቡ ማሳየት አንዱ መንገዳቸው ነው። ድካም እንኳን ባይኖርበት፥ ሳይሆን አይቀርም የሚል የፈጠራ ወሬ ያስወሩ በታል። ያም የፖለቲካ ሰው ሊናገርበት የሚገባውን ፍሬ ሀሳብ በመ ናገር ፈንታ ተቃዋሚው ያቀረበበትን ነቀፋ ለማስተካከል ሲታገል ብዙ ጊዜ ያጠፋል ብለው ስለሚያምኑ ነው። ያም ለተወዳዳሪው ጥሩና አመቺ ጊዜ ይሆንለታል። ይህን ዓይነቱ ባህሪ የሚታየው በፖለቲካ መድረክ በሚሻሙ ሰዎች መካከል ብቻ ሳይሆን በቤተ ክር ስቲያንና በክርስቲያኖችም አካባቢ ጎልቶ እየታየ ነው። ይሄም ጎጅነቱ የተነተፈውን ሰው ብቻ ሳይሆን የነቃፊውንም ሕይወት እየቦረቦረ

ደስታ የሌለው፥ ስለ እውነት ግድ የሌለው ሰው ያደርገዋል። በክርሱ ሥር የሚገለገለውንም ክርስቲያን ሠራዊት ይጎዳል። ባንክርፍት የተባለ ጸሀፊ "ዮሳረቤታቸውን ዝና በማበላሸት ደስታ የሚሰማቸው ሰዎች፥ ስለ 'እውነት' ፍጹም ግድ የሌላቸው ናቸው" አለ። የእግዚአብሔር ቃል አንዱ በሌላው ላይ ክፉ ቃል እንዳይናገር (ያዕ. 4፥11) ቢያዝም፥ አማኞች ብዙ ጊዜ ይህን ቃል በሕይወታቸው ሲጥሱት ይታያሉ። በዚህ ምክንያት ብዙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ከአገልግሎታቸው ተባረዋል። የብዙዎች ልብ ተሰብሯል። ብዙ የእግአብሔር ሥራ ተበላሽቷል። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ተከፋፍሏል።

ፊልፕ ስካፍ የተባለው ታሪክ ጸሀፊ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ስለ ናረው ስለ ታወቀው ማርቲን ሉተር ሲጽፍ እንዲህ አለ። "ማርቲን ሉተር ጽሁፍና ምላስ ብዙ ጊዜ ሌሎችን የሚያስቆጣ፥ የጠብ መርዝ የሚረጭ ነበር። ተቃዋሚ መስለው የሚታዩትን ሁሉ ምህረት በሌለው በምላስ ጥርስ ይወጋቸው ነበር" አለ። በጊዜው የተሀድሶ እንቅስቃሴ መሪ ከነበሩት ውስጥ አንደኛው የነበረ ዝዊንግሊ እንደ ማርቲን ሉተር በህጻናት ጥምቀት አላምንም ስላለ ማርቲን ሉተር የዝዊንግሊንን ዝና ለማጥፋና ለማበላሸት ከፍተኛ ጥረት ያደርግ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። በዚህም ዘመን አሉ በሚባሉ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህ ችግር ይታያል። ያላቸውን ልዩነት በግለታሪቅ ፈንታ ወይም የግይታረቅ ከሆነ ተቻችሎ ለመኖር በመሞከር ፈንታ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት እያሰፉት ሲሄዱ ማየት ያሳዝናል። የታወቀው ወንጌላዊ ጸክ ቫን ኪምፐ የሙዲ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ዓመታዊ ኮንፍራንስ ላይ እንዲናገር ተጋብዙ በዝግጅት ላይ እያለ፥ አንድ ቀን ቺካጎ ውስጥ ሊያደርግ ስላለው ታላቅ ስብሰባ (ክሩሴድ)፥ ከአዘጋጁ ኮሚቴ ቴሌግራም ደረሰው። ቴሌግራሙ የያዘው መልዕክት በሙዲ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሊደረግ በታሰበው ዓመታዊ ስብሰባ ላይ መስበክ እንደሌለበት፥ እምቢ ብሎ ከሰበክ ግን ቺካጎ ላይ ሊያደርግ ያሰበውን ስብሰባ የሚሠርዙበት መሆኑን የሚገልጽ ነበር። ይህን ያደረጉት በእነሱ ግምት የሙዲ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የእነርሱን ያህል ወግ አጥባቂ ባለ መሆኑ ብቻ ነበር።

ጸክ ቫን ኪምፐም ዛቻቸውን ስለ ፈራ በኮንፍራንሱ ላይ መናገሩን ሠረዘ። የሚገርመው ግን የሙዲ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

ቤት ባለሥልጣናት እነዚያን የናቋቸውንና የነቀፏቸውን ሰዎች እንደ አመጣጣቸው ሳይሆን በፍቅር የተቀበሏቸው መሆኑ ነው። ጸክ ለሚያደርገው ክሩሴድ በትምህርት ቤቱ ሬዲዮ መግለጫ እንዲሰጡና ግስታወቂያ እንዲናገሩ ሲጠየቁ፥ በተራቸው በመበቀል ፈንታ በተጠየቁት መሠረት በደስታ ግስታወቂያውን አደረጉላቸው። እኛም "ግትህትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድር ጋችሁ ቁጠሩ እንጂ ወገን በመለየትን በራስ ወዳድነት ወይም ያለ እኔ ማን አለ በሚል ትምክህት ምንም ነገር አታድርጉ" (ፊልጵ. 2፥3) የሚለውን መሪ ቃል በሕይወታችን ለመለማመድ እንትጋ።

የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር የነበረው ጆን ኦውን፥ የኮሐንስ ቡንያንን ስብከት ለመስማት ለንደን ሄደ። ንጉሥ ቻርለስ ሁለተኛው፥ ይህንን ሰምቶ በመደነቅና በመገረም "እንዴት አንተን የመሰለ ታላቅ የተማረ ሰው፥ ፍጹም ትምህርት ከሌለው ሰው ለመስማት ይሄዳል?" ሲል ጠየቀው። ጆን አውንም የራሱን ትልቅነት ለማንጸባረቅ "እውነ ትህን ነው" በማለት ፈንታ፥ "ግርማዊ ሆይ! የዚህ ያልተማረው ቦኮ ሐንስ ቡንያንን ዓይነት ዕውቀትና ችሎታ ቢኖረኝ የተማርኩትን ትምህርት ሁሉ አተው ነበር" አለ። ከሌላው በልጦ ለመታየት የሚሞክር ሰው ከሌላ ሰው መማር ያስቸግረዋል። እርሱ አለመማሩ ብቻ ሳይሆን፥ ሌሎችም እንዳይማሩ እንቅፋት ይሆናል። የሌላውን ችሎታ አምኖ መቀበል ትህትና ከመሆኑም በላይ፥ ከታላላት ጦርነትና ከጥላቻ ያድናል። "እንዲሁም እያንዳንዱ የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን፥ የሌላውንም ሰው ጥቅም ያስብ። በዚህ ዓይነት ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየው የትህትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገባል" (ፊልጵ. 2፥4) የሚለውን ምክር በሥራ መተርጎም ይገባናል።

3.6. <u>የራሳቸውን ድካም ለመሸፈን ሌላውን ይነቅፋሉ</u>

አንዳንድ ሰዎች ነቀፋ ሲያበዙ የሚታዩት ሌላውን ሰው ሆን ብለው ለመጉዳት ፈልገውና አስበው አይደለም። የራሳቸው የሆነ ውስጣዊ ችግር ስላለባቸው ነው። በሌላው ላይ የነቀፋ ቃል ሲወረውሩ፥ የነቀፉትን ሰው ለመጉዳት ሳይሆን በውስጣቸው የታመቀውን መራራነት መተንፈሳቸው ነው። እነዚህ ሰዎች በሕይወታቸው የተጎዱበት፣ የቆሰሉበት፣ ስሜታቸው የተጎዳበት ሁኔታዎች ቀደም ሲል

ተፈጥረዋል። ታዲያ ብስጭታቸውን፥ ህዘናቸውን የሚወጡት ሌላውን በመንቀፍ ሲዋጉ ነው። በቀና መንፈስ ሁኔታቸውን ብንመለከትላቸው "እርዱኝ! ተጎድቻለሁ!" ማለታቸው ነው። አንዳንድ ነቀፋ የሚያበዙ ሰዎች ጊዜ አግኝተን በልጅነታቸው ያለፉብትን ሕይወት ብንመረምር በሌሎች ብዙ ነቀፋ ደርሶባቸው የተጎዱ፥ ጤናማ ባልሆነ ግንኙነት ምክንያት የቆሰሉ ሰዎች መሆናቸውን ለማወቅ ጊዜ አይፈጅብንም። በውስጣቸው ልዩ ልዩ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ሌላውን መኮነን ቢጣም ይቀላቸዋል። አስተዋይ ከሆንን፥ የተጎዱ ሰዎች ጉዳታቸውን የሚወጡት ሌሎችን በመንቀፍ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን። አንዳንድ ሰዎች በግልጽ፥ በንዴት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲነቅፉን ስንሰማ፥ *"ዝባችሁን እርዱኝ! ውስጣዊ ጉዳት አለብኝ"* ማለታቸው መሆኑን እንዘንጋ።

የራሳቸውን ድካም ወደሌላው ሰው ማስተላለፍ፥ ወይም ሌላውን ምክንያት ማድረግ የሚፈልጉ አሉ። በዕለታዊ የኑሮ ትግላቸው ያል ተሳካላቸው ከሆነ፥ ቶሎ ብለው ራሳቸውን ከአቅፉ ለማዳን ሲሉ ሌላ ውን ሰው መንቀፍ ይጀምራሉ። ለምሳሌ ጓደኞቹ የግል ትምህርት ተምረው ሲመረቁ ሲያይ፥ እንደ እነርሱ ብዙ ነገር መስዋዕት ከፍሎ በመግር ፈንታ ደካማ መስሎ በሌሎች እንዳይታይ ቶሎ ብሎ ሚስ ቱን ምክንያት ያደርጋል። *"እንጂ እዚህና እዚያ እንሂድ ባትጸኝ ናሮ ዛሬ እኔም ከጓደኞቼ እኩል ትምህርቱን ጨርሼ እመረቅ ነበር"* በማ ለት በየምክንያቱ በቃላት ሚስቱን ይገርጣል። ሰው የራሱን ድካም፥ ውድቀቱን ወደሌላው ማስተላለፍ ተፈጥሯዊ ባሕሪው ነው። ሲሳሳት፥ "ተሳስቻለሁ" ብሎ ስህተቱን አይቀበልም። ሌላውን በመንቀፍ የስህተቱን ወይም የችግሩን ምክንያት ሌሎችን ያደርጋል።

3.7. <u>"እኔን ምሰሉ" የሚል ሰሜት ሰላላቸው ይነቅፋሉ</u>

አንዳንድ ሰዎች ሰው ሁሉ የእነርሱን ዓይነት ምርጫ፥ አስተያየት እንዲኖረው ይፈልጋሉ። እንደ እነርሱ ካልተናገረ፥ እነርሱ እንደሚ ያስቡት ካላሰበ፥ እነርሱ የመረጡትን ካልመረጠ፥ በእነርሱ ግምት ያ ሰው ልከ አይደለም። ያንን ሰው ለመለወጥና እነርሱን እንዲመስል ለማድረግ ስለሚፈልጉ ይነቅፉታል። እነርሱን የሚመስል ሰው ከበዛ ላቸው፥ የውስጣዊ ችግራቸው የሚቃለልላቸው መስሎ ይሰማቸዋል።

እግዚአብሔር ሁላችንንም የተለያየን አድርጎ ፈጥሮናል። የራሳችን መልክ፣ ባህሪ፣ የምንወደውና የምንጠላው እንኳን የተለያየ እንዲሆን አድርጎ ፈጥሮናል። በዓለም ላይ ያለ ሰው ሁሉ አንድ ዓይነት ቢሆን ናሮ፥ ዓለም ምን ዓይነት ችክ የሚልና የሚሰለች ሥፍራ ይሆንብን ነበር? ሁላችንም የተለያየን ሰዎች በመሆናችን የተለያየ ሀሳብና አስ ተያየት አለን። ያም ግምታችንና አመለካከታችንን እንደሚያሰፋልን አምነን በመቀበል ፈንታ የግጭታችን ምክንያት ስናደርገው ያሳዝ ናል። *ካቶ የተባለ ጸሀፊ፥ "ሰዎች በአስተሳሰባቸው ሲለያዩ በሁሉም ነገር የማይጋጠሙ (የማይሰማሙ) አድርገው ይወስዱታል። ልዩነታ ቸው እርስ በእርስ ቅራኔን ይወልዳል። ቅራኔም አንዱ ሌላውን መግ ፋትን፥ በሌላው መናደድን ይወልዳል። ሰዎች ሌላውን የመውደድ ችሎታቸው ይለያያል። በዚህ ምክንያት አስተያየታቸውና ግምታቸው በዚያው መጠን ስለሚለያይ ኩራትና ንዴት ከውስጣቸው እንዲፈልቅ ይሆናል"* አለ።

አንዳንድ ባልና ሚስት ብዙ ጊዜ ልዩነታቸውን ተቀብለው በመ ናር ፈንታ፥ አንዱ ሌላውን ለመለወጥ ሲታገሉ ይታያሉ። እርግጥ ነው በዓላማ አንድ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በየግል አስተያየት የሚወዱትና የሚጠሉት የተለያየ መሆን ይችላል። ይህንን እውነት ያልተረዱ፥ የኑሮ ጓደኛቸውን እንደነርሱ እንዲያስብ፥ እነርሱ የወደ ዱትን እንዲወድና እንዲመርጥ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ጥረታቸው ካልተሳካ፥ እነርሱን ካልመሰለ፥ በአስተሳሰቡና በምርጫው ከነርሱ ከተለየ፥ ትክክል ያልሆነ ስለሚመስላቸው፥ የኑሮ ጓደኛቸውን ለመለ ወጥ የነቀፋ ቃል ይጠቀማሉ። ነገር ግን ነቀፌታ ያፈርሳል እንጂ አይሸሳም። ያሳንሳል እንጂ አያሳድግም። ያራርቃል እንጂ አያቀራር ብም። ሌላው ሰው እኛን እንዲመስል መታገል፥ ያንን ሰው ከማስ ጨነቁ ሌላ በመካከላችን መለያየትና ጭቅጭቅን ስለሚያስከትል እርስ በርስ መጎዳቀፋችንን እንተው። ሳናውቅ የምንወረውረው የነቀፋ ቃል ሌላውን ሊያደማ እንደሚችል እንወቅ።

4. <u>ነቀፋ ሲደርስብን ምን እናድርግ?</u>

እኛ የምንወረውረው የነቀፋ ቃል ሌሎችን ሊጎዳ እንደሚችለው ሁሉ፥ ሌሎችም በእኛ ላይ የሚወረውሩት የነቀፋ ቃል ሊጎዳን ይች

ላል። "ከኑቀፍ ደስ ይለኛል" የሚል ሰው ይናራል ብለን ግመን ያቅ ተናል። ሰዎች ስለ እኛ መልካም ቃል ሲናገሩ፥ ሲያሞግሱን ደስ የሚለንን ያህል ሲነቅፉንና ክፉ ቃል ስለ እኛ ክፉ ሲያወሩም ደስ አይለንም። ይሁን እንጂ፥ መጠኑና ዓይነቱ፥ እንዲሁም ምክንያታችን ይለያይ እንጂ፥ ግናችንም ከኑቀፉ ነጻ መሆን አንችልም። "አትንቀ ፉኝ" ብለን ነታሬዎችን ማስቆም ስለማንችል፥ በኑቀፉ ውስጥ እን ዴት ግለፍ እንደምንችል ግወቅ አለብን። የተወረወረብን ነቀፋ ሰብ ርብራችንን ሳያወጣው፥ እንዲሁም "ለምን ተነቀፍኩ" ብለን የበቀል እርምጃ ሳንወስድ እንዴት ግለፍ እንችላለን? ነቀፌታ በሕይወታ ችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፥ በምንም ምክንያት ይሁን፥ ከየትኛውም አቅጣጫ ይምጣ፥ ነቀፌታን ለመቋቋም ራሳች ንን ግዘጋጀት ይገባናል። አንዳንድ ሰዎች የሚያደርጉት ነገር በነና ጠቃሚ ቢሆንም፥ አንዳንድ ነቀፌታ ሲሰነዘርባቸው ያደርጉት የነበረ ውን ነገር ጥለው በተስፋ መቁረጥ በመሞላት ጥግ ይዘው ይቀመ ጣሉ። ይሄም ነታሬዎቻቸውን በጣም ደስ ያሰኛል። አንዳንዶች ደግሞ መልሰው በመንቀፍ አጸፋውን ይመልሳሉ። ነቀፋ ሲደርስብን መሸ ሽም ሆነ ከነታሬው ጋር የቃላት ጦርነት ግካሄድ፥ ሁለቱም ጠቃሚ አይደሉም። ነቀፋ ሲደርስብን፥

4.1. <u>ከኑቀፍ ነጻ የሆነ ግንም እንደሌለ እንወቅ</u>

ከመነቀፍ ነጻ መሆን የሚችል ሰው ስለሌለ፥ "መነቀፍ ሊደርስብኝ ይችላል" ብለን እንጠብቅ። ሰውን ሁሉ ግሰደሰት የቻለ ግንም ሰው እስካሁን ስለሌለ፥ እኛም ሰውን ሁሉ ደስ እናሰኛለን ብለን አንጠ ብቅ። ያስተግርኩትን ትምህርት፥ የሰበክሁትን ስብከት፣ የጻፍኩትን ጽሁፍ ሁሉም ይወደዋል ብዬ ሳምን ትልቅ ስህተት መሥራቴ ነው። ሀሳቤን መቀበል የሚያቅታቸው፥ ንግግሬ የማይጣፍጣቸው፥ ጽሁፌ የማያስደስታቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የሚወዱኝ እንዳሉ ሁሉ፥ ሊጠሉኝ የሚችሉም ይኖራሉ። ይህንን እውነት ካላወቅሁና አምኜ ካልተቀበልኩ፥ በጎ ያልሆነ ነገር ስለ እኔ ሲነገር ብሰማ በአንድ ጊዜ ስብርብሬ ነው የሚወጣው። እኔ ለመሥራት መብት እንዳለኝ ሁሉ፥ እነርሱም እኔ በሠራሁት ላለመገልገል ቢፈልጉ መብታቸው የተጠ በቀ ነው። እንዲሁም የፈለጉትን ዓይነት አስተያየት መስጠት ይች

ላሉ። ነታሬዎች የሌሉበት አካባቢ ፈጽሞ የለም። ስለሆነም፥ የሚነቅፉ ሰዎች እስካሉ ድረስ ግንም ከኑቀፉ ግምለጥ ወይም ነጻ መሆን አይ ችልም። ለምሳሌ አንድ ሰው ገንዘብ ለግኘት ቢሯሯጥ፥ "ስግብግብ" ይባላል። "ለገንዘብ ግዴለኝም" ቢል፥ "ለግደግ ጉጉት የሌለው" ይባ ላል። ገንዘቡን ቢቆጥብ፥ "ንፉግ"፥ ገንዘቡን ቢያጠፋ ደግሞ "ብኩን" ይባላል። ድሃ ቢሆን፥ "የግይሠራ ሰነፍ"፥ ሀብታም ቢሆን ደግሞ፥ "አጭበርብሮ ያገኘው ነው" መባሉ አይቀርም። በወጣትነቱ ቢሞት፥ "በልጅነቱ ተቀጨ" ይባላል፥ ዕድሜ ጠግቦ ቢሞት ደግሞ፥ "የሕብ ረተ ሰብ ሽክም ዝር" ይባላል። አዋቂዎች እንደሚሉት፥ የማይነቀፍ ሰው ቢኖር፥ እዚህ ዓለም ያልመጣ ወይም ገና ያልተወለደ ሰው ነው። ፍጹም የሆነው፥ በቅድስናው ተወዳዳሪ የሌለው፥ ምንም ዓይ ነት እንከን የግይገኝበት ኢየሱስም እንኳን ተነቅፏል። ኢየሱስ ከኑቀፉ ነጻ ካልሆነ፥ እኛም ከኑቀፉ ነጻ መሆን የግንችል መሆናችንን ማወቅ ይጠቅመናል።

4.2. <u>ነቀፌታውን በጥንቃቄ እንመዝን</u>

ነቀፌታ ከየትና ከምን የመጣ ነው? ነቀፌታው ምን ያህል እውነት ነው? ጠቃሚ ነው? ምን ያህል በነነት አለበት? ነታሬዎቹ እነማን ናቸው? ነቀፋቸው ምን ያህል እውነትነት አለው? ብሎ መጠየቅና መመርመር አስፈላጊ ነው። ነቀፋውን ብቻ ሳይሆን፥ ነታ ሬዎችንም መመርመር ይጠቅማል። አንድ ጊዜ "አንድ ሰው ጋዜጣ ላይ አውጥቶ ስሜን አጠፋ" በማለት በጣም የተበሳጨና ያዘነ አንድ ሰው ነበር። ሁኔታው በጣም ስላበሳጨው፥ "ስለ ተነቀፍኩበት ነገር ምን ግድረግ አለብኝ?" በማለት አንዱን ምሁር ምክር ጠየቀ። የተ ጠየቀውም ምሁር ሲመልስለት፥ *"ምንም አታድርግ። አርፈህ ተቀ መጥ"* አለው። ይህን ያለበትን ምክንያት ሲገልጽ፥ *"በከተማው ውስጥ ካሉት ሰዎች ጋዜጣውን ገዝተው የሚያነቡት ምናልባት ግማሾቹ ይሆናሉ። ከግማሾቹ መካከል ደግሞ ያንን ጹሁፍ አያነቡትም። አሁ ንም ካነበቡት ውስጥ ደግሞ ግማሾቹ ስለምን እንደተጻፈ ያልገባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከገባቸው መካከል ደግሞ ግማሾቹ ጸሀፊው ያለውን አላመኑትም። ካመኑት መካከል ደግሞ ግማሾቹ፥ በአንተ ሕይወት ውስጥ ምንም ዓይነት ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ አይደሉም። ስለዚህ*

ምን አሰጨነቀህ?" አለው። ይሆን ሲለው፥ ጋዜጣው ላይ የወጣውን ታሪክ "እንብዘው፥ ነገሩ ገብቷቸው፥ ይሆናል ብለው የተቀበሉት በጣም ጥቂት ሰዎች ስለሆኑ፥ እነርሱም ቢሆኑ ምንም ሊያደርጉህ የሚችሉ ስላልሆኑ አትጨነቅ" ግለቱ ነበር።

ገንቢ ያልሆነ ነቀፋ የሚወረውሩብን ሰዎች ስለ እኛ ያላቸው አስተያየት ምን እንደሆነ ስለምናውቅ፥ ለእነርሱ ልንናደድላቸው አይገባም። ጉልበታችንን በንዴት የምንጨርሰው ከሆነ፥ ለማድረግ የተነሳነውን በጎ ሥራ እንዳንሠራ ጉልበት እናጣለን። ስለ እኛ በጎ ነገር የማይመኙ፥ በምንሠራው ሥራ ሁልጊዜ ደስ የማይሰኙ፥ በእኛ ላይ የሚቀኑ፥ በሥራችንና በአገልግሎታችን ላይ እንከን የሚፈልጉ ሰማችንን ለማበላሸት ከሚፈልጉ ሰዎች የመጣ መሆኑን እናውቃለን። ወቀሳቸው በምን መንፈስ እንደተወረወረ ስለምናውቅ፥ ስለሚወረውሩት ነቀፋ ልንጨነቅ አይገባም። ነቀፌታው ትክክል ከሆነ፥ በምስጋና እንቀበለው። ባይሆን ደግሞ በመናደድ ጤንነታችን እንዲታወክ አናድርግ። ሰዎች በንዴት ሲሞሉ አንዳንድ ጊዜ ሊጠቅሟቸው የሚፈልጉትን ሰዎች ሊጎዱ ይችላሉ። መራራነትም በልባችን እንዲፈጠር አንፍቀድ። አንዳንድ ሰዎች አልፎ አልፎ ነቀፋ ካልደረሰባቸው ምን ጊዜም ስህተታቸውን ሊያዩና ሊያርሙ አይችሉም። ነቀፌታው አግባብ ያለውም ባይሆን፥ በነቀፋቸው ድካማችንን ለማየት ስንችል ነቃፊዎችን ልናመሰግናቸውና ስህተታችንን ልናርም ይገባል።

4.3. ነቀፌታውን ለበጎ እንጠቀምበት

ነቀፌታን ለጥቅማችን ልናውለው ይገባል። ነቀፌታውን ስንመረምረው ገንቢ የሆነ ነቀፌታ ከሆነ፥ ከነቀፌታው ግትረፍ ወይም መጠቀም ይገባናል። ነቀፌታው ገንቢ በመሆን ፈንታ አፍራሽ ከሆነ በተቻለን መጠን ንቀን ማለፍ አለብን። ራሳችንን ከነቀፋው በላይ እናድርግ። "ሲቢለሰ" የተባለ ታላቅ የሙዚቃ ምሁር ከተማሪዎቹ መካከል አንዱን፥ አልፎ አልፎ የሚነቅፉት ሰዎች እንደሚኖሩና ስለ እነርሱም መጨነቅ እንደሌለበት ሲመክረው እንዲህ አለው። "ምንኛ ቅጉ ሰዎች ሁልጊዜ ይኖራሉ። ማሲታወስ ያለብህ ነገር ቢኖር፥ ለነ ቃፊዎች ሀውልት የማይቆምላቸው መሆኑን ነው" አለው። ይሆን ሲል ልትደርስበት የሚገባውን ደረጃ ነቃፊዎችን በመፍራት ወደ ኋላ እንዳትል ግለቱ ነበር። አንድ ጊዜ፥ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ ፓስተሩን መቀበል ያቃታቸው ሦስት ሰዎች ነበሩ። ለግበሳጨትና ተስፋ ለማስቆረጥ፥ በሰበከ ቁጥር "ስብከትህ ልክ አይደለም፥ ይሄ ጎደለው፥ ያ ጎደለው" እያሉ የነቀፋ አስተያየታቸውን ማንነታቸውን ሳይገልጹ ጽፈው ይልኩለት ነበር። እርሱም ጎደለ ያሉትን በየጊዜው እያስተካከለ፥ ያሰባበኩን ይዘት እያሻሻለ መጣ። አንድ ቀን "ስትሠትናቸው የተነሳ ስማቸውንም ባይጽፉም እነዚህ ሰዎች ጠቅመውኛልና በሕዝቡ ፊት ማመስገን አለብኝ" ብሎ ወሰነ። አንድ ዕሁድም ስብከቱን ከመጀመሩ በፊት፥ "ብዙዎቻችሁ ስብከቴን በየሳምንት ታዳምጣላችሁ። ይሁን እንጂ አስተያየታችሁን አለምታችሁኝ አታውቁም። ከእናንተ መካከል ሦስት ሰዎች ግን ስማቸውን ሳይጽፉ በታማኝነት አስተያየት ስለሚጽፉልኝ፥ አስተያየታቸውም በጣም ስለጠቀመኝ ዛሬ በእናንተ ፊት ማመስገን አለብኝ" ብሎ ተናገረ። ነቃፊዎቹ ዓላማቸው ለመጥቀም ሳይሆን ለመጉዳት ነበር። ፓስተሩ ግን "ተጠቀምኩ" ሲል፥ "እኛ ያደረግነው ልንጎዳው ነው እንጂ ልንጠቅመው ስላልሆነ፥ የሚጠቅመው ከሆነ ሁለተኛ አንልክለትም" ብለው መጻፋቸውን አቆሙ። ነቀፌታን ለጥቅማችን ማዋል እንደምንችል ይሄ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል።

ምዕራፍ ፭

አሉባልተኛ (ሐሜተኛ) ምላስ

"ሰነፍ በንጥቂ ጥልን ያነሣሣል፥ በመለፍለፉም ይደበደባል። ሰነፍ በሚናገርበት ጊዜ ራሱን በጉዳት ላይ ይጥላል፥ የራሱም አነጋገር ወጥመድ ሆኖ ይይዘዋል።"
(ምሳሌ 18፥7-7)

መጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ስለ ምላስ ከመቶ ጊዜ በላይ መጠቀሱን ስናይ፥ ምላስ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ምን ያህል ከፍተኛ ሥፍራ እንደያዘ መገንዘብ እንችላለን። ጤናማ ባልሆነ ምላስ ያል ቆሰለና ጉዳት ያልደረሰበት፥ ወይም መልካም በሆነ ምላስ ደስታን ያላገኘ፥ ያልሳቀና ያልተጽናና ሰው በዚህ ዓለም ይኖር ይሆን? ምላስ ያቆሰላቸው እንዳሉ ሁሉ፥ ምላስ የፈወሳቸውም እንዳሉ ግልጽ ነው። በክፉ ምላስ ምክንያት ትዳራቸው የፈረሰ፥ ከሚወዱት አብሮ አደግ ጓደኛቸው ጋር የተለያዩ፥ የምላስ ጦር ሲበዛባቸው መሮአቸው ከሕብረተሰቡ ሸሽተው ለብቻቸው የተቀመጡ፣ ከቤተ ክርስቲያን ሕብረት የወጡ፣ ከአማሎታቸው የተባረሩ፣ ክፉ

ምላስ በሰው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ሕያው ምስክሮች እንደሚሆኑ ግልጽ ነው። ክፉ ሰዎች፥ ምላሳቸው ክፉ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። *"ክፉ ሰዎች ሐሜትን ያሰራጫሉ፥ ሁከትንም በማነሣሣት በፍትር የተ ሣሥሩትን ወዳጆች ይለያያሉ"* ይላል (ምሳሌ 16፥28)። ስለሆነም፥ *"...በከንቱ ከሚለፈልፉ ሰዎች ራቅ"* (ምሳሌ 20፥19) ብሎ ሠለ ሞን ይመክረናል። ምላስ የግቱስልም ሆነ የመፈወስ ኃይል እንዳ ለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው"* (ምሳሌ 18፥21) ይላል። ይህ እውነት ከሆነ ምላሳችን ሕይወት በመስጠት ፈንታ ወደ ሞት (ማጥፋት) የሚያደላው፥ ምክንያቱ ምን ይሆን? ወሳኙ ምላሳችን ሳይሆን የልባችን አቋም ነው።

1. <u>አሉባልታ አሳባቂነት ይሆን?</u>

እንዳንድ ልጆች፥ ወንድማቸው ወይም እህታቸው መጥፎ የሆነ ነገር ሲያደርጉ ካዩ፥ ዝም በማለት ፈንታ ለወላጆቻቸው ይናገራሉ። በዚህ ምክንያት *"አሳባቂ"* የሚል የትጽል ስም ይሰጣቸዋል። ዮሴፍ ወንድሞቹ የሚያደርጉትን ክፉ ነገር ለአባቱ ሊያዕቆብ ይነግር እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል (ዘፍ. 37፥2)። ዮሴፍ ስለ ወንድሞቹ የተናገረው እውነት ቢሆንም፥ *"አሳባቂ"* መባሉ እንደግ ይቀር ግልጽ ነው። ወላጆች ልጆቻቸው ያደረጉትን መጥፎ ነገር ቢሰሙ፥ ልጆቻቸውን በቅጣትም ሆነ በሌላ መንገድ ሊያርሟቸው ስለሚችሉ፥ መናገሩ ክፉ አይሆንም። ይሁን እንጂ፥ ማንም *"አሳባቂ"* ተብሎ መጠራት፥ ወይም በአሳባቂነት መታወቅ ስለማይፈልግ አይ ተው ዝም ማለትን የሚመርጡ እንዳሉ እናውቃለን። ለመሆኑ በሌላ በኩል አሉባልታ ማውራት "አሳባቂነት" መሆኑ ይገባን ይሆን? ይህ እውነት ከሆነ በአሁኑ ጊዜ "የማሳበቅ" ጠባይ ጎልቶ የሚታየው በልጆች ላይ ሳይሆን፥ በዕድሜ በጎለመሱት ላይ እንደሆነ የታወቀ ነው። "አሳባቂነት" ወይም "አሉባልተኛነት" የሚጎዳው የተወራብትን ሰው ብቻ ሳይሆን፥ ያወራውንም ሰው ጭምር ነው። በአሉባልታ ወይም በሐሜተኛ ምላስ ተወግተው የቆሰሉ፥ ቁስሉ ገና ያልዳነላ ቸው፥ እንዲሁም በመቆየት ብዛት ቁስላቸው ቢድንም፥ የመቁሰላቸው

ምልክት የሆነው ጠባሳ ጎልቶ የሚታይባቸው በዚህ ዓለም ብዙዎች እንደሆኑ የታወቀ ነው።

2. የአሉባልታ ባሕሪ

2.1. አሉባልታ ሲሰፋፋ ፈጣን ነው

የአሉባልታ ወሬ በእጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ሥፍር ይደርሳል። እንዲሁም ወሬው ከአንዱ ወደ ሌላው እየተላለፈ ከመጪረሻው ሰው ዘንድ ሲደርስ ወሬው፥ ከመጀመሪያው ፍጹም የተለየ እንደ ሚሆን የታወቀ ነው። ለምሳሌ፥ ሃያ ሰው መርጠን *"በበግ ላይ በግ ዘለለ፥ በውሻ ላይ ውሻ ዘለለ"* የሚለውን መልዕክት እንዱ ለሌላው በስልክ እንዲያስተላልፍ ብንጠይቅ፥ የመጪረሻው መል ዕክት ከመጀመሪያው ፍጹም የተለየ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ለመጀመሪያው ሰው "ይህን መልዕክት ለእከሌ አስተላልፍለትና፥ እርሱም ለሚቀጥለው ሰው ይህንኑ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ንገረው" ብንለውና መልዕክቱ ከአንዱ ወደ ሌላው እንዲተላለፍ ቢደረግ፥ ሃያኛው ሰው ላይ ሲደርስ፥ መልዕክቱ *"በበግ ላይ በግ ዘለለ፥ በውሻ ላይ ውሻ ዘለለ"* የሚለው መሆኑ ይቀርና *"ውሻው በንን በላት"* የሚል እንደሚሆን እንገምታለን።

ልክ እንደዚሁ የአሉባልታም ወሬ ከአንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፍ፥ ወሬው መጀመሪያ ከነበረበት ፍጹም የተለየ እንደሚ ሆን እርግጠኞች ነን። ወሬው ወደ ብዙዎች ዘንድ እንዲደርስ ከተፈለገ ደግሞ፥ ነጋሪው *"ምስጢር ነው። ለማንም እንዳትናገር። ለእኔም የነገረኝ ሰው 'ምስጢር ነው' ብሎ ነውና አደራህን ለራስህ ብቻ ጠብቀው"* ማለት አለበት። የሚገርመው ነገር፥ ይህን ሲል፥ "ምስጢር ነው ብሎ ከተነገረው ታዲያ ለእኔ ለምን ይነግረኛል?" ብሎ ሰሚው እንደሚታዘበው አለማሰቡ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *"የሚሰማብኝ የለም ብለህ በሰውር እንኳ ቢሆን ንጉሥን አትማ፥ በተኛህበት አልጋህ ላይ ሆነህም ባለጸጋን አትሰደብ፥ ምክንያቱም ምስጢርህን የሰሙ ነገር ጠላፊዎች ከንፍ እንዳለው ወፍ ቢርረው ሊነግሩብህ ይችላሉ"* ይላል (መክብብ 10፥2)። ሐሜተኛ ሰው ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጸው፥ *"ሐሜትን*

የሚገልጥ ሰነፍ ነው" (ምሳሌ 10፥18)፥ እንዲሁም *"...ሐሜተኛ ሰው ምስጢር አይጠብቅም"* ይላል (ምሳሌ 11፥13)።

ሐሜት ክንፍ እንዳለው ወፍ በሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ሥፍራ ይደርሳል። አንድ ጊዜ የሮማ ፓርላማ አባል የሆነ አንድ ሰው ሚስቱ ፓርላማ ውስጥ ስለ ምን እንደሚወያዩ እንዲነግራት ታስቸግረው ነበር። ምስጢር መጠበቅ የማትችል መሆኗንና እን ዲሁም ወሬ ከአንዱ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ በምን ያህል ፍጥ ነት ሊዳረስ እንደሚችል ለማየት ፈልጎ፥ ሚስቱን እንዲህ አላት። *"ልዩ ዜማ የሚያዜም አንድ የወፍ መንጋ፥ የወርቅ ራሥ ቁር በራሳቸው ላይ ደፍተው፥ ጦር ይዘው በሰማይ ላይ እየበረሩ ስለ ሆነ፥ ስለዚህ የወፍ መንጋ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለ በት ፓርላማው ሊወያይበት ነው"* ብሎ የራሱን ታሪክ ፈጥሮ ከነ ገራት በኋላ፥ በቀጥታ ወደ ፓርላማ ሄደ። ያቺም ሴት ባሏ ልክ ቤቱን ለቆ እንደወጣ ቤት ውስጥ ለምታገለግለው ሠራተኛዋ ፓርላማው በአሁኑ ጊዜ ስለምን ለመወያየት እንደወሰነ ባሏ የነገ ራትን ገልጻ ነገረቻት። ሠራተኛዋም የቅርብ ጓደኛዋ ለሆነችው ሌላ አገልጋይ አስተላለፈች። ያቺም አገልጋይ ለወንድ ጓደኛዋ "ምስጢር ነው ለማንም እንዳትናገር" ብላ ተናገረች። ያ የፓርላማ አባል ፓርላማ ደርሶ መደበኛው ወንበሩ ላይ ልክ ሲቀመጥ፥ አጠገቡ የነበረ ሌላ የፓርላማ አባል ጠጋ ብሎ፥ አዲስ ዜና አለኝ አለውና *"ልዩ ዜማ የሚያዜም አንድ የወፍ መንጋ፥ የወርቅ ራሥ ቁር ደፍቶ፥ ጦር ይዞ በሰማይ ላይ እየበረሩ ስለሆነ፥ ስለዚህ የወፍ መንጋ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ፓርላማው ዛሬ በዚህ አሳብ ላይ ሊወያይ ነው"* አለው። ያም የፓርላማ አባል በኃይል እየሳቀ፥ ሚስቱ አጠገቡ ያለች ይመስል፥ *"አንቺ የእኔ ሚስት! ስለ ፍጥነትሽ የተመሰገንሽ ነሽ"* አለ።

2.2. አሉባልታ ከጀመረ ማቆሚያ የለውም

አሉባልታ ሲስፋፋ ፈጣን መሆን ብቻ ሳይሆን፥ አንዴ ከተጀ መረ ማቆሚያ የለውም። አንድ ጊዜ በአሉባልታ ወሬ በጣም የተጎዳች አንዲት ሴት ጭንቀቷን ለአንዱ እንዲህ ስትል ጻፈች። *"ጥሩ ጠባይ ያላት የ16 ዓመት ሴት ልጅ አለችኝ። አሉባልታው*

ከየት እንደ ፈለቀ አላውቅም፥ ትምህርት ቤቷ ውስጥ ይህቺው ሴት ልጄ 'አርግዛለች' እየተባለ ይወራል። ልጄ እንዳትጎዳ ከዚያ ትምህርት ቤት አስወጥቼ ሌላ ትምህርት ቤት ላስገባት ፈልጌ ነበር። ይሁን እንጂ፥ ከትምህርት ቤት ብትቀር፥ 'ልትወልድ ቀረች፥ ወይም 'ሰላረገዘች ትምህርት ቤቱን ሊቃ ወጣች' ይባላል ብዬ ፈራሁ። እዚሁ ቀርታ ትማር፥ አርጉዝ አለመሆኗ ጊዜ ይሰየዋል ብዬ አሰባለሁ። ይሄም ያስፈራኛል። ምክንያቱም ጊዜው ደርሶ አለመውለዷን ሲያዩ ደግሞ 'አስወርዳ ነው' ማለታቸው አይቀርም ብዬ ነው። ለመሆኑ ምን ባደርግ ይሻለኛል?" ብላ ጠየቀች። አሉባልታ የሚያሰራጩ አንዳንድ ተንኮለኞች፥ ለመጉዳት ቆሚፈልጉትን ሰው ለመጉዳት አንዱ በር ቢዘጋባቸው ሌላ በር መክፈታቸው አይቀርም። አሉባልታ አውሪዎችንና አሉባልታን በምን ዓይነት መንገድ ማስተናገድ እንደምንችል ወደ ፊት በሰፊው እንመለከታለን።

2.3. <u>አሉባልታን መልሶ ማስተካከል ከባድ ነው</u>

አሉባልታ አንዴ ከተሠራጨ፥ አሉባልታውን የሰሙት እነማን እንደሆኑ ሰለማይታወቅ መልሶ ለማስተካከል ፈጽሞ አይቻልም። በመካከለኛው ክፍለ ዘመን አንድ ጊዜ አንድ ወጣት፥ አንድ ካህን ዘንድ ሄዶ "እውነት ባልሆነ አሉባልታ የሰውን ስም በማጥፋት የጎዳሁ ስለሆንኩ፥ ስለ ኃጢአቴ ምን ላድርግ?" ብሎ ካህኑን ጠየቀው። ካህኑም ሲመልስለት፥ "ሂድና በዚህ ከተማ ውስጥ ባሉት ቤቶች ሁሉ በራፋቸው ላይ የዶሮ ላባ አስቀምጥ" አለው። ያም ወጣት እንደተነገረው አደረገ። ሌላ ማድረግ የሚገባው ነገር ካለ ለመጠየቅ ወደ ካህኑ ዘንድ ተመልሶ ሄደ። ካህኑም ያንን ወጣት፥ "አሁን ደግሞ ሂድና ቢያንዳንዱ ቤት በራፍ ላይ ያስቀመጥከውን የዶሮ ላባ ለቅመህ አምጣ" አለው። በዚህን ጊዜ ወጣቱ፥ "ይሄማ እንዴት ይቻላል? እስካሁን የዶሮ ላባዎቹን ነፋስ በከተማ ሁሉ ስለሚበትናቸው መሰብሰብ አስቸጋሪ ነው" አለው። ካህኑም፥ "እውነትህን ነው፥ ልክ እንደዚሁ አንተ የበተንከውም አሉባልታ በከተማው ሁሉ ስለ ተሰራጨ፥ መልሶ መሰብሰብ ከባድ ነው" አለው።

ምላስ እንደተራበ እንስሳ አንዳንዶቻችን አሉባልታ ለማውራትም ሆነ ለመስማት በጣም የሚያጓጓን ለምን ይሆን? ደሆን ስሜት መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጸው "የሐሜተኛ ሰው ቃል እንደጣፋጭ ምግብ ደስ እያሰኘ እስከ ውስጥ ሰውነት ይወርዳል" ይላል (ምሳሌ 26፥22)። የሐሜተኛ ሰው ቃል የማይጣፍጠን፥ ወይም የማያስደስተን፥ አሉባልታው ስለ እኛ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው። አይሁዶች እንዲህ የሚል እነጋገር አላቸው። "አንድ ውሻ የጮኸ እንደሆነ፥ የመንደሩ ውሾች ሁሉ ይሰበሰቡና፥ መጀመሪያ የጮኸው ውሻ ለምን እንደጮኸ ምክንያቱ ባይገባቸውም፥ ዝም ብለው አብረው ይጮኻሉ። አንተ ግን ቅዱስ ሰው ሃኖ እንደዚያ መሆን የለብህም" ይላሉ። ልክ እንደዚሁ እኛም መጀመሪያ አለ ብልታውን ያወራው ሰው በምን ምክንያት፥ ወይም በምን መንፈስ ተነሳስቶ ያንን የመሰለ አሉባልታ እንዳወራ በትክክል ሳናውቅና በደንብ ሳይገባን፥ ወሬው እውነት መሆን ወይም አለመሆኑን ሳናጣራ፥ ዝም ብለን የማውራት ዝንባሌ አለን። በሌላው ወገን ያለውን ታሪክ ሳይሰሙ መፍረድም ሆነ አስተያየት መስጠት ለራሳችንም ሆነ ለሌላው ሰው "ሀቀኞች" አያደርገንም።

3. <u>ሐሜትና አሉባልታ ምንድነው?</u>

ሐሜት ማለት ምን ማለት ነው? እንደ ዌብስተር መዝገበ ቃላት ገለጻ፥ ሐሜት ማለት፥ ስለ ሌላው ሰው እውነት ያልሆነ ነገር ማውራት ማለት ነው። ይሁን እንጂ፥ እኛ ክርስቲያኖች መመሪያችንን የምናገኘው ከዌብስተር መዝገበ ቃላት ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ "ሐሜትን" እንዴት ይገልጸዋል?" ብለን መጠየቅ ይገባናል። መጽሐፈ ቅዱስ "ሐሜትን" የሚገልጸው ዌብስተር መዝገበ ቃላት ከሚገልጸው ፍጹም በተለየ ሁኔታ ነው። ሐሜት እውነት ያልሆነ ነገር ብቻ ሳይሆን፥ እውነት የሆነም ነገር ስለ ሌላው ማውራት ማለት ነው። ካሮል ሜሆል (Carole Mayhall) "የሚጎዳ ቃል፥ እንዲሁም የሚፈውስ ቃል" (Words That Hurt & Words That Heal) በሚለው መጽሐፏ "ሐሜት" ምን እንደሆነ ጥሩ አድርጋ ገልጻዋለች።

"ብሉይ ኪዳን ሐሜት "የሌላውን መልካም ሰም (ዝና) ማጥፋት መሆኑን ያሳያል። ዮሴፍ በልጅነቱ ስለ ወን ድሞቹ ክፉነት ለአባቱ አወራ። "...ወንድሞቹ የሚፈ ጽሙትንም በደል እያመጣ ለአባቱ ይነግር ነበር" (ዘፍ. 37፥2)። ዮሴፍ የሚያወራው እውነትነት ያለው ቢሆ ንም፥ መጥፎ ሪፖርት ነበር። ይኸው ቃል በዘጎልቄ ላይ ተጠቅሷል። ከአያሱና ከካሌብ ጋር የከነአንን ምድር እንዲሰልሉ የተላኩት አሥሩ ሰላዮች፥ "...በእስ ራኤላውያን መካከል አሳብች ወሬ አሰራጩ...." ይላል (ዘጎልቄ 13፥32) ስለ ተሰፋይቱ ምድር ሰላዮቹ ያሰራ ጩት ወሬ መልካምነት የሌለው ወሬ ነበር። በአዲስ ኪዳን ደግሞ "ሐሜት" የሚለው ቃል በሁለት ዓይነት መልክ ተገልጿል። አንደኛው፥ "መናገር" ማለት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ "ተቃራኒ" ማለት ነው። ስለዚህ "ሐሜት" ማለት በሌላው ላይ ተቃራኒ የሆነ ነገር መና ገር ማለት ነው። ሐሜት ማለት የሚወራው ነገር እው ነትም ቢሆንም ባይሆንም፥ የሌላውን ሰው ሰምና ዝና ለማጥፋት ወይም ለማበላሸት የሚወራ ወሬ ነው።"

የተወራው ወሬ እውነትነትም ቢኖረው፥ ወሬውን በአደባባይ ለሁሉም መናገር አለብን ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ ለራሳችን ነጻነት ለመስጠት፥ ወይም የሚሰማን ሰው እንዳይታዘበን፥ *"ይህን የማወራልህ፥ ተብሎ ያለቀ ወሬ ስለሆነ ነው። እንዴት አንተ ወይም አንቺ አልሰማሽም..."* በማለት ነው። በወሬ ትንሽ ቅመም ጨምረን ከማውራታችን በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ንግግራችን ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት የሚመክረንን እንመልከት። *"ከቶ ከአ ፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፥ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም፥ ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ"* ይላል (ኤፌ. 4፥29)። ሐሜትን ከማውራትም ሆነ፥ ከመስማት ራስን መጠበቅ እንዴት ይቻላል? ሐሜት የሚያመጣውን ጉዳት የተረዱ ሁለት ክርስቲያን ባልና ሚስት፥ ለራት ሰዎችን ሲጋብዙ፥ ተጋባዦች በግልጽ ማየት እንዲችሉ፥ ግድግዳቸው ላይ በትልቁ *"በመካከላችን ያልተገኘ ሰው ሰሙና ታሪኩ በቤታችን አይጠራም"*

የሚል ጽሁፍ ጽፈው ይለጥፋሉ። ይሄም ለጋባዦችም ሆነ ለተ ጋባዦች በጣም ጥሩ ማስጠንቀቂያ ይሆንላቸዋል። እንዴት ግሩም አሳብ ነው! ራሳችንን ከሐሜት ለመጠበቅ ይህን የመሰለ ጥንቃቄ እናድርግ ይሆን?

ብዙ ጊዜ ሳናስብ በችኮላ በመናገራችን ምክንያት፥ ራሳችንን ችግር ውስጥ እንጥላለን። ከመናገራችን በፊት፥ በማሰብ ፈንታ፥ ከተናገርን በኋላ፥ ስለ ተናገርነው ነገር የማሰብ ጸባይ አለን። አማርኛ ተናጋሪ የሆንን ሁሉ የምናስበው በአማርኛ ነው። በእን ግሊዝኛ ለመናገር ስንፈልግ፥ በአዕምሯችን የምናስበውን ወደ እንግሊዝኛ እየተረጎምን እናቀርበዋለን። ሳናስብ ዝም ብለን የመ ጣልንን ለመናገር ብንሞክር፥ እንግሊዝኛውን ስብር ብሩን ነው የምናወጣው። በዚሁ ዓይነት በጥንቃቄ ሳናስብ የመጣልንን ሁሉ የምንናገር ከሆንን፥ በራሳችንም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳችን የታወቀ ነው። ብዙ ጊዜ "ለምን እንዲህ ብዬ ተናገርኩ?" ብለን እንጸጸታለን። የእግዚአብሔር ቃል *"ሳያስብ በችኮላ ከሚናገር ሰው ይልቅ ለዕምር የጎደለው ሰነፍ የተሻለ ተስፋ አለው"* ይላል (ምሳሌ 29፥20)። "እከሌ ሠረቀ" የሚል ወሬ ብንሰማ፥ እውነት መሆኑን ሳናረጋግጥ፥ "ሠረቀ" የተባለው ሰው የሚሰጠውን ምክንያትና አስተያየት ሳንሰማ "ሠረቀ" ብቻ ሳይ ሆን፥ ለጆሮ እንዲጣፍጥ ጨማምረን "ባንክ ሰብሮ ሠረቀ" ብለን እናወራለን። ለምሳሌ ባልና ሚስት ተጋጭተው፥ ከሁለቱ አንደ ኛው ምክር ለመጠየቅም ሆነ የሚያዝንለት ሰው ለማግኘት፥ የኑሮ ጓደኛው ያደረሰበትን በደል ወደ አንድ ሰው ዘንድ ሄዶ ችግሩን ይገልጻል። ሰሚው በአንድ ወገን ያለውን ታሪክ ብቻ ሰምቶ ቢፈርድ፥ ስለ ሌላው ሰው ያለው አስተያየት መጥፎ ቢሆን፥ እን ዲሁም አንድ አቅጣጫ የያዘውን ወሬ ለሌላው ቢያስተላልፍ፥ ትልቅ ስህተት ይሠራል። በዚህ ዓይነት የተጋጩትን ባልና ሚስት ከመጥቀም ይልቅ የበለጠ ሊያራርቃቸው ይችላል። እንዲሁም፥ የራሱንም የግል መንፈሳዊ ሕይወት ያበላሻል። ያዕቆብ *"ወንድ ሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፥ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል"* ይላል (ያዕ. 4፥11)። ስለዚህ "ተበደልኩ" የሚለውን ሰው ብቻ ሰምተን ከመፍረድ ወይም

አስተያየት/ክመስጠት እንጠንቀቅ። አሉባልታ አውሪዎች ለመሆኑ እንዴት ዓይነት ሰዎች ናቸው? ሐዋርያው ጳውሎስ በእንደኛው ከፍለ ዘመን፥ ሥራ በግጣት ምክንያት አሉባልታ ያሰራጫሉ ብሎ የፈራው ባል የሌላቸው ሥራ ፈት የሆኑ ሴቶችን ነበር። *"...ሥራ መፍታት ብቻ ሳይሆን ለውን የሚያመጡ በሰው ነገር የሚጨነቁ መናገር የማይገባቸውን የሚናገሩ ይሆናሉ"* ይላል (1 ጢሞ. 5፥ 13)። ጳውሎስ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ቢኖር ኖሮ፥ አሉባልታ አውሪዎችና ሐሜተኞች ባል የሌላቸው ሴቶች ብቻ አለመሆናቸውን ይረዳ ነበር። በዘመናችን የሐሜትና የአሉባልታ ችግር ጎልቶ የሚታየው በዓለማውያን ዘንድ ብቻ ሳይሆን፥ በክር ስቲያኖችም አካባቢ እንደሆነ የታወቀ ነው።

4. ሰዎች አሉባልታና ሐሜት የሚያወሩበት ምክንያት

4.1. ሌላውን ሆን ብለው ለመጉዳት ሲፈልጉ

አንዳንድ ሰዎች የጠሉትን ሰው ለመጉዳት፥ እውነት ያልሆነ አሉባልታ ያስወሩበታል፥ ወይም እውነት ባልሆነ ምክንያት ይከ ሱታል። በፖለቲካ ዓለም የተሰለፉ፥ ተወዳዳሪያቸውን በትክክለኛው መንገድ መቅደም ካቃታቸው፥ አሉባልታ በማሰወራት ለመቅደም ይሞክራሉ። በኅለም ውስጥ ያሉ ሰዎች ይህን ዓይነቱን ዘዴ መጠቀማቸው አይደንቀንም። የሚደንቀን ግን "ክርስቲያኖች" ብለው ራሳቸውን የሚጠሩ ሰዎች ሲጠቀሙበት ማየት ነው። ጊዜው አርብ ማታ ነው። አንድ ጊዜ ጥቂት ክርስቲያኖች ለአ ዳር ጸሎት ተሰብስበዋል። መንፈሳቸውን ለጸሎት ለማዘጋጀት መዝሙር ከዘመሩና አጭር መልዕክት ካዳመጡ በኋላ ስብሰባውን የሚመራው ሰው የጸሎት ጥያቄ መቀበል ጀመረ። ተራ በተራ የተለመደውን ዓይነት የጸሎት ጥያቄ ማቅረብ ጀመሩ። *"ጌታ ለን ራችንን በታላቅ ኃይል እንዲነበናት... መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያናችን እንዲሆን፥... ለለገልጋዮች ...ወደ ኋላ ለተመለሱት ክርስቲያኖች ወዘተ. እንጸልይ"* የሚል የጸሎት ጥያቄ ቀረበ። የጸሎት ጥያቄው አልቆ ሁሉም ወደ ጸሎት ሊሄድ ሲል፥ የሁሉ

ንም ጆሮ መሳብ በምትችልበትና ለስለስ ባለ ድምጽ *"ወንድሞቼና እህቶቼ"* አለች እህታችን መሰለች። ያኔ ሁሉም ለማዳመጥ ጆሮ ውን ነቃ አደረገ። የድምጿ ልስላሴና አነጋገር፥ ቅድስና በአነጋ ገር የሚለካ ቢሆን ኖሮ ለመሰለች ከፍተኛ ደረጃ ያሰጣት ነበር። ብርቱ ክርስቲያን በሚያስመስላት ድምጿ መሰለች *"ወገኖቼ! ለሳ ሙኤልና ለትሁት አጥብቀን እንጸልይላቸው። እንደምታዩት አዳር ጸሎታችን ላይ ከተገኙ ብዙ ጊዜ ሆኗቸዋል። መንፈሳዊ ሕይወታ ቸው እንደ ድሮው አይመስለኝም። እኔ እንኳ በትዳራቸውም ላይ ችግር ሳይኖርባቸው አይቀርም ብዬ አምናለሁ"* ስትል የጸሎት ጥያቄ አቀረበች።

ብዙዎች ስለ ሳሙኤልና ስለ ትሁት ትልቅ ግምት ስለነበራ ቸው ሁኔታው ሲያስደንቃቸውና ሳያሳዝናቸው አልቀረም። መሰ ለች ያቀረበችው የጸሎት ጥያቄ ከልብ በመቆርቆር ነው ወይስ *"አሉባልታ በጸሎት መልክ"* ማቅረቧ ነው? ለመጥቀም ነው፥ ወይስ ለመጉዳት ነው? መንፈስን መመርመር የሚችለው ጌታ መሰለች ለሳሙኤልና ለትሁት ያቀረበችው የጸሎት ጥያቄ ጥሩ ተመኝታላቸው እንደሆነና እንዳልሆነ ያውቃል። ሳሙኤል ትሁ ትን ለትዳር ጠይቆ ከማግባቱ በፊት፥ መሰለች ሳሙኤልን ለኑሮ ጓደኝነት ትመኘው ነበር። እርሱን ወደ ራሷ ለመሳብ የተቻላትን ሁሉ ብታደርግም ሳሙኤልን መሳብ አልቻለችም። ተስፋ የቆረ ጠችው ሳሙኤል ትሁትን ካገባ በኋላ ነው። በዚህ ምክንያት ልቧ የተቀየመው በሳሙኤል ላይ ብቻ ሳይሆን በትሁት ላይም ነበር። የጸሎት አሉባልታ ያቀረበችው በዚህ ምክንያት ነበር። *"አሉባልታ በጸሎት መልክ"* ያልነው ሀሳብ በአሁኑ ጊዜ በአማኞች መካከል በጣም የተለመደ ሆኗል። የመሰለች የጸሎት ጥያቄ ከልብ የወጣ አልነበረም። ዓላማዋ ግልጽ ነው። የሳሙኤልና የትሁት መንፈሳዊ ይዞታ መሰለች እንዳቀረበችው አልነበረም። በአዳር ጸሎት ላይ መገኘት ያልቻሉበት ምክንያት ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ ምክ ንያት እንጂ በክርስትና ሕይወታቸው ስለ ደከሙ አልነበረም። ስለዚህ መጠንቀቅ ያለብን ነገር ቢኖር፥ በተለያየ የግል ምክን ያት፥ ቤተ ክርስቲያን መጣት ያልቻሉትን ሁሉ፥ "ክሕይወታቸው ደክመዋል" እያልን አሉባልታን በጸሎት አማካኝነት እንዳናወራ ነው።

ለምሳሌ፥ መሰለች የጸሎት ጥያቄውን ያቀረበችው ከላይ በገለጽነው ምክንያት አይደለም ብለን እንመን። "ለመሆኑ ትዳራቸው ላይ ችግር እንዳለባቸው በምን አወቀች? ማን ነገራት?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። አንድ ቀን ሳሙኤልና ትሁት ሆስፒታል ሰው ጠይቀው ሲወጡ፥ በአንድ ምክንያት የጋለ ክርክር ሲያደርጉ ስላየቻቸው፥ "ችግር ላይኖርባቸው አይቀርም" የሚል የራሷን ግምት ወስዳ ይሆናል። አባባሏ "ሳይሆን አይቀርም" በሚል ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው። ባልና ሚስት በውይይታቸው ሁልጊዜ የሚስማሙ፥ ምንም የማይጨቃጨቁ አድርጎ መገመት፥ የጋብቻን እውነተኛ ተፈጥሮና ባሕሪ አለመረዳት ይሆናል። "ሳይሆን አይቀርም" በሚል ግምት ብቻ ስለ ሌሎች ክርስቲያኖች ማውራት፥ የምናወራው ከልብ በመቆርቆር እንኳን ቢሆን ትልቅ ስህተት ነው።

በሌላ በኩል መሰለች እንዳለችው ሳሙኤልና ትሁት በመን ፈሳዊ ሕይወታቸው የቀዘቀዙና በጋብቻቸውም ላይ ችግር ይኑር ባቸው ብለን እንውሰድ። ይህንን ይዘታቸውን መሰለች እንዴት ማወቅ ቻለች? ችግራቸውን ራሳቸው እስኪያስተካክሉት ድረስ ግንም ሰው እንዲያውቅባቸው አይፈልጉም ይሆናል። ይህ የግል ጉዳያቸው እንጂ በአደባባይ የሚወጣ የሕዝብ ጉዳይ አይደለም። ምናልባት በመንፈሳዊ ሕይወቷ ብርቱ ስለመሰለቻቸው መሰለች በጸሎት እንድትረዳቸው ይህንንም በሚስጥር እንድትይዘው አስ ጠንቅቀው ነግረዋት ይሆናል። ይህን እንጂ፥ ከፈቃዳቸው ውጪ በመሰለች አማካኝነት የግል ችግራቸው፥ የጓዳቸውና የቤታቸው ሁኔታ በአደባባይ በጸሎት ስም መታወጁ ትክክል አይደለም። ይህ ዜና ለብዙዎች በመድረሱ ሳሙኤልና ትሁት ማወቃቸው አይቀ ርም። ሳሙኤልና ትሁት በጸሎቱ ከሚያገኙት ዕርዳታ ይልቅ፥ አሉባልታው ደበልጥ ይጎዳቸዋል። በዚህ ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመቅረብ ይልቅ እየሸሹ ይሄዳሉ።

4.2. <u>አሉባልታ ጎጂነቱን ባለማወቅ ነው</u>

ክርስቲያኖች የሌላውን ሰው ድካም (ውድቀት) ለማውራት የሚፈልጉበት ምክንያት ምን ይሆን? ይሄ ችግር ዓለም አቀፍ

ይመስላል። በጀርመን አገር በ1920 (እ.ኤ.አ.) ክርስቲያኖች በጋራ የሚኖሩበት የአማኞች ሕብረት ተቋቁሞ ነበር። የሀሜትና የአሉ ባልታ ምላስ ሕብረታቸውን እንደሚያጎደፈው አስቀድመው ስላ ወቁ በዚህ ሕብረት ውስጥ ከነበራቸው ልዩ ልዩ የመተዳደሪያ ደንብና ሕግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የነበረው፥ "ማንኛውም አማኝ በሌላው አማኝ ላይ የፍርድ ቃል (የመኮነን) ቃል እንዳይ ናገር የሚል ነበር። ክርስቶስም በተራራው ስብከቱ ላይ ይህንኑ አስተምሯል። *"በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ላይ አት ፍረዱ፥ ምክንያቱም በሌሎች ላይ በምትፈርዱበት ዐይነት በእና ንተም ላይ ይፈረድባችኋል። እንዲሁም በምትሰፍሩበት መሰፈሪያ ይሰፈርባችኋል"* ይላል (የማቴ. 7፥1-2)። ክርስቶስ ሊያስተላልፍ የሞከረው ትምህርት፥ ሌላው ላይ መፍረድ፥ መንቀፍና መተቸት ክርስቲያናዊ ተግባር አለመሆኑን ነው። ግብዝ በራሱ ዓይን ላይ የተጋደመውን ግንድ በማንሳት ፈንታ በሌላው ዓይን ላይ ያለ ውን ትንሽ ስንጥር ለማንሳት ይሞክራል። ይሁን እንጂ፥ በመካከ ላችን ያሉትን ሀሰተኛ ነብያትና አስተማሪዎችን ለይተን ማወቅና በእነርሱ ላይ መፍረድ የለብንም ማለት አይደለም። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአግባቡና በሥርዓት የማይራመዱ መታ ረም፥ መቀጣት፥ አስፈላጊ ከሆነም ከአገልግሎት መገለል የለባቸ ውም ማለት አይደለም።

የደከመውን በመደገፍ ፈንታ ማጋለጥ፥ ለፍርድ ማቅረብ ጥንትም ቢሆን በሃይማኖት ሰዎች እካባቢ የተለመደ ባህሪ ነበር። በክርስቶስ ዘመን አንዲት ሴት ስታመነዝር አግኝተው ክርስቶስ እንዲፈርድባት እያዳፉ ይዘዋት መጡ። ክርስቶስም ኃጢአተኛዋ እርሷ ብቻ ሳትሆን እነርሱም እንደሆኑ በሚገባቸው መንገድ ለማሳየት *"ከእናንተ መካከል ኃጢአት የሌለበት በመጀመሪያ ድን ጋይ ይወርውርባት"* ሲል ነጻነት ሰጣቸው (የዮሐ. 8፥7)። በክር ስቶስ ፊት መዋሸት እንደማይችሉ ስለተገነዘቡ፥ ክሳቸውንና የተ ከሰሰችውን ሴት ከክርስቶስ እግር ሥር ጥለው ጠፉ። ኢየሱስ ግን በመፍረድ ፈንታ፥ "ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ" በማለት ካስጠነ ቀቃት በኋላ በነጻ አሰናበታት። የሀሜትና የአሉባልታ ምላስ ሹል በመሆኑ በጣም ይጎዳል። አሉባልታ ጎጂ መሆኑን እያወቁ፥ አሉ

ባልታ ሲያወሩ ሕሊናቸውን የማይቆረቁራቸው ለምን ይሆን? "ኃጢአት ሲደጋገም እንደ ጽድቅ ይቆጠራል" የሚል አባባል እንዳለ እናውቃለን። አሉባልታንና ሀሜትን ብዙ ጊዜ በሕይወታቸው የተለማመዱ ህሊናቸው ደንዝዞ ኃጢአትነቱ ስለማይሰማቸው ነው። ብዙዎች ፍቅራቸውንና ሕብረታቸውን የሚያዳብሩት አሉባልታ በማውራት ነው። ተገናኝተው ሌላውን እየቆራረጡ፥ እያሳነሱ ሲያወሩ ሞቅ ይላቸዋል። ሁለት አሉባልታ የሚወዱ ሰዎች በሌላ ነገር እርስ በርሳቸው ባይጣጣሙ፥ በሀሜት ወሬያቸው ግን በጣም ይግባባሉ። ስለሆነም፥ ሲገናኙ ሁልጊዜ ማውራት የሚፈልጉት እነርሱን ስለሚመለከታቸው ጉዳይ ሳይሆን፥ ስለሚያሙት ሰው ነው።

የአሉባልታና የሀሜትን ጎጂነትና አደገኛነት አስጠንቅቀው የሚናገሩና የሚጽፉ፥ በክርስትና እምነት ውስጥ ያሉ ብቻ ሳይሆኑ ዓለማውያንም ጭምር ናቸው። የአሉባልታንና የሀሜትን ባህሪና እንዲሁም የሚያስከትለውን ጉዳት ከተረዱት ፈላስፋዎችና አዋቂዎች መካከል፥

(1) ሸሪዳን-- "አሉባልታ አውሪዎች 'ምን እያደረጋችሁ ነው?' ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ፥ 'ውሸት እየሸቃቀጥን ነው' የሚል ነው አለ።

(2) ፓስካል-- አሉባልታን ሲገልጽ "የአሉባልታ ትከከለኛ ትርጉም፥ ሁለትና ሁለት አምስት ነው ብሎ ማውራት ነው" አለ።

(3) ፕላቱስ-- "አሉባልታ አውሪዎችና አሉባልታ ተቀባዮች (አድማጮች) ሁለቱም በስቅላት መቀጣት አለባቸው። አውሪውን ምላሱን ይዞ ማንጠልጠል፥ ሰሚን ደግሞ ጆሮውን ይዞ ማንጠልጠል ነው" አለ።

(4) ሶቲል የተባለው ምሁር ደግሞ የአሉባልታን አደገኛነት ሲገልጽ፥ "አሉባልታ አውሪዎች የሚያጠፉት ጥፋት እሳትና ሰይፍ ከሚያጠፉት ይበልጥ ፈጣንና አደገኛ ነው" አለ።

4.3. በጥላቻ ምክንያት

አሉባልታና ሀሜት ይጎዳል እንጂ ማንንም አይጠግንም። ሀሜተኛው ሀሜት በሚያወራበት ሰው ላይ የጥላቻ እንጂ የፍቅር መንፈስ እንዳለበት አያንጸባርቅም። በሌላው ላይ አሉባልታ ማውራት ያንን ሰው ድምጽ በሌለው መሣሪያ እንደ መግደል መሆኑን ብንረዳ ብዙዎቻችን ራሳችንን እየነጨን ንስህ እንገባ ነበር። አንድ ጊዜ በውሻው በጣም የተናደደ፥ በራሱ እጅ ተኩሶ መግደል ያልፈለገ አንድ ሰው ውሻውን፥ *"ሂድ ከፊቴ ጥፋ፥ እኔ በእጄ ተኩሼ አልገድልህም።* መጥፎ ስም ብቻ አሰጥሃለሁ" በማለት ውሻውን ገበያ መካከል ውስዶ ከለቀቀው በኋላ፥ *"ዕብድ ውሻ... ዕብድ ውሻ!..."* በማለት ጮኸ። የዚህን ሰው ጩኸት የሰማ ሰው ሁሉ፥ ሰውየው የተናገረው ነገር እውነት መሆኑንና አለመሆኑን የሚያጣራበት መንገድ ስለሌለው፥ ራሱን ለማዳን ሁሉም ሸሽቶ ለማምለጥ መሯሯጥ ጀመረ። ይሄ ዕብድ ውሻ ሌላውን ሰው ከመንከሱ በፊት ሁኔታው ያላሰበው አንድ ሌላ ሰው ሽጉጡን አውጥቶ ያንን ውሻ ተኩሶ ገደለው። የውሻው ባለቤት እንዳወጀው፥ ያ ውሻ ያበደ ውሻ አልነበረም። ይሁን እንጂ፥ "ዕብድ ውሻ" የሚል ስም ስለተሰጠው፥ እንዳበደ በመቆጠሩ ተገደለ። ልክ እንደዚሁ ሀሜትና አሉባልታ በሌላው ላይ ማስወራት፥ እኛ ተከሰን ባንገድለውም፥ ለገዳይ አሳልፈን እንደመስጠት የሚቆጠር መሆኑን መዘንጋት የለብንም። በአሉባልታና በሀሜት ተመተው የቆሰሉ፥ የደሙና የተጎዱ ስንቶች ይሆኑ? ቤታቸው ብቻ ይቁጠራቸው።

አሉባልታና ሐሜት በእግዚአብሔር ዘንድ ያስጠይቃል። *"በእውነት እላችኋለሁ ሰዎች በሚናገሩት ምንም ጥቅም በሌለው ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል። ምክንያቱም ከቃልህም የተነሳ ይፈረድልሃል፥ ከቃልህም የተነሳ ይፈረድብሃል"* ይላል (የማቴ. 12፥36-37)። በሌሎች ላይ እንደ ፈረድነው በእኛም ላይ አንድ ቀን ይፈረድብናል። የሚፈረድብንም በጠባያችንና በአኗኗራችን ይዘታ ሳይሆን፥ በምላሳችን በሌሎች ላይ ባደረስነው ጉዳት መጠን ነው። በእኛ አሉባልታና ሀሜት ምክንያት ሌላው የነበረውን መልካም ስም ቢያጣ፥ ከሥራው ቢባረር፥ ከሌላው ሰው ጋር እንድኑርና ግንኙነቱ እንዲሻክርና እንዲበላሽ ብናደርግ፥

በቤተሰብ መካከል ብጥብጥና ጠብ እንዲፈጠር ምክንያት ብንሆን፥ ለዚያ ሁሉ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂዎች እንሆናለን።

አንድ ኦሞቂ ሰው የአሉባልታንና የሀሜትን ምክንያት ሲገልጽ፥ *"ጊዜ ለመግደል (ጊዜ ለማሳለፍ) ሲሉ ብቻ አንዳንድ ሰዎች የሰው ሰም ይገድላሉ (ያጠፋሉ)"* አለ።

- *"ታፈሰችን ዛሬ ተብለጭልጫ ጸጉር ሠሪ ቤት አየኋት። ከርስትናውን ችላ ሳትለው አትቀርም..."*
- *"ኧረ እኔም ከንፈሯን ቀለም ተቀብታ፥ ቅንድቧን ላጭታ አየኋት..."*
- *"ጸሎት ቤት ካየኋት ብዙ ጊዜ ነው። ጌታን ሳትተው አትቀርም..."*
- *"ኧረ ከእጮኛዋም ጋር ሳትለያይ አትቀርም። አብረው ሆነው አይቻቸው ለላውቅም..."*
- *"እሰቲ እባካችሁን እንጸልይላት!..."* ይባላል።

ነቀፌታ መልኩን ለውጠና ተሸፋፍኖ የሚቀርበው በአሉባልታና በሀሜት መልክ ነው። ሀሜት አውሪው ሰው ብዙ ጊዜ ስለ ሌላው ሰው ተቆርቋሪ መስሎ ይቀርባል። ብዙ ጉዳት ያመጣል ብለው ስለማያስቡ፥ ሥራ ሲፈቱ ብዙዎች ሀሜትን እንደ ጊዜ ማሳ ለፊያ ይጠቀሙበታል። ይሁን እንጂ እየቆየ ሲሄድ ያመረቅዝና ወደ ካንሰርነት ይለወጣል። አሉባልታና ሀሜት የሚያዘወትር ሰው፥ ምንም ያህል ጎጂና አጥፊ መሆኑን ቢረዳም፥ በወሬው ልዩ ደስታ ስለሚያገኝበት ራሱን ከዚያ ልማድ ማላቀቅ ያቅተዋል። "ነቀፌታና" አሉባልታ (ሐሜት) የሚለያዩበት በአንድ ነገር ብቻ ነው። ይኸውም፥ ብዙ ጊዜ ነቀፋ የሚያደርገው ተነቃፊው ሰው ባለበት ሲሆን፥ ሀሜትና አሉባልታ የሚወራው ሁልጊዜ ከባለጉዳዩ በስተኋላ ወይም በድብቅ ነው። ምንም ያህል ተቆርቋሪ በመምሰል ይወራ እንጂ፥ አሉባልታና ሀሜት ሰውየው በሌለበት ስምና ዝና ውን ዘልዝሎና ቆራርጠ መግደል ነው። ከላይ በምሳሌ እንደተመለከትነው "ለእከሌ እንጸልይለት" በማለት ሀሜትና አሉባልታ ጸሎት መልክ ማቅረብ ሥጋዊነት እንጂ መንፈሳዊነት አይደለም።

5. <u>አሉባልታ መለያው ምንድነው?</u>

ሀሜት ጎጂነቱን፥ መለያየቱንና እንደ እሳት ማቃጠሉን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን መንገድ ያስባሉ፥ ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው። ክፉ ሰዎች ሀሜት ያሰራጫሉ፥ ሁከትን በማነሳሳት ሰፍቅር የተሳሰሩ ትን ወዳጆች ይለያያሉ"* ይላል (ምሳሌ 16፥27-28)። ሀሜትና አሉባልታ ምን ያህል በሰው ሕይወት አደገኛና መርዛምነት እን ዳለው ለማስረዳት አንድ ሰው ይህን ታሪክ በምሳሌ ተናገረ። አንድ ሰው ውሻ ነክሶት ዕርዳታ ለማግኘት ወደ ሀኪም ዘንድ ሄደ። ሀኪሙ በጥንቃቄ ከመረመረው በኋላ ራሱን እየነቀነቀ *"ወንድሜ! በመጥፎ ውሻ ተነክሰሃል። በሕይወት ለመቆየት ያለህ ጊዜ በጣም ጥቂት ቀናት ብቻ ነው፥ አዝናለሁ ምንም ልረዳህ አልችልም"* አለው። ሰውየውም ጥቂት ካሰበ በኋላ ወረቀትና እርሳስ እንዲሰጡት ጠይቆ ለብዙ ደቂቃ ያህል እያሰበ መጻፍ ጀመረ። መጻፉን ጨርሶ ሊነሳ ሲል፥ ኑዛዜውን የጻፈ ስለመሰለው ሀኪሙ *"ይህን ያህል ጊዜ የፈጀብህ ኑዛዜህ በጣም ረጅም ቢሆን ነው"* አለው። ሰውየውም ሲመልስ *"ኑዛዜ አይደለም። ከዚህ ሰወጣ የምነክሳቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር እያወጣሁ ነበር"* አለው። በዚህ ዓይነት፥ ሀሜትና አሉባልታ የሌላውን ስምና ዝና መግደያ መርዝ መሆኑን ስንቶቻችን ተገንዝበንው ይሆን?

በብሉይ ኪዳን "አሉባልታ" የሚለውን ቃል ይጠቀሙበት የነበረው በጠቅላላው መጥፎ ሪፖርት ሲሰጥ ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ "አሉባልታ" ማለት የሌላውን ሰው ጥሩ ስም መግፈፍ ወይም ዝናውን ማጉደፍ ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ "አሉባልታ" ማለት በሌላው መፍረድ ወይም የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት ማለት ነው። የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሀፊ *"ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማመኑ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል፥ በሕግም ላይ የፈርዳል"* ይላል (ዕብ. 4፥11)። ስለ ሌላው የሚወራው ወሬ ሁሉ አሉባልታ ወይም ሀሜት ነው ማለት አይደለም። ታዲያ መለያው ምንድነው?

(1) ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው፥ ወይም ወሬው የሚወራበት

ሰው፥ ስለ ሁኔታው የሚያውቅ ከሆነ፥ ያ ሀሜት ወይም አሉባልታ አይባልም።

(2) ወሬውን የሚያወራው ሰው ያለው ስሜት እንዴት ነው? አውሪው ይሆን ወሬ ሲያወራ ደስ እያለው ነው? ወይስ በሁኔታው ከልቡ እያዘነና እየተጨነቀ ነው? ወሬውን ሲያ ወራው ቅር እያለው ነው? ከሆነ አሉባልታ አይደለም።

(3) የተናጋሪው ዓላማ፥ ወሬው የተወራበት ሰው በሰሚዎች ዘንድ መጥፎ መስሎ እንዲታይ ለማድረግ ነው?

(4) ወሬውን ሌሎች ከመስማታቸው በፊት፥ ጉዳዩ ከሚመለ ከተው ሰው ጋር ተነጋግሮበታል?

(5) ወሬውን የሚያወራው ሰው ስለ ሌላው የሚናገረው ግድ መነገር ያለበት ስለሆነ ነው?

የተወራበት ዓላማ ትክክል ካልሆነ፥ አሉባልታ ወይም ሀሜት ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ *"እርስ በርሳችሁ አትተማሙ"* (ያዕ. 4፥11) በማለት የመከረንን ምክር በሕይወታችን ለመለማመድ ሁላችንም ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለብን።

አሉባልታ እውነትም ይሁን ውሸት፥ ዓላማው ሌላውን ሰው ለመጉዳት ወይም ስለ ሌላው ሰው በግውራት ልዩ የሆነ ደስታን ለማግኘት እስከ ሆነ ድረስ፥ ያ ወሬ ጤንነት የማይሰጥ አሉባልታ ነው። አንዳንድ ሰዎች ስለዚያ ሰው የሚናገሩት ነገር እውነት ከሆነ ማግቱ ወይም አሉባልታ ማውራቱ ትክክል ይመስላቸዋል። የሚናገሩት ነገር እውነትነት ያለው መሆኑን ብቻ ሳይሆን ለማውራት የተነሱበት ዋናው ውስጣዊ ግፊት (ሞቲቭ) መመርመር አለበት። እውነትነት አለው የሚሉትን ወሬ ለማውራት የፈለጉበት ምክንያት ምንድነው? ወሬው ማንን ይጠቅማል? የሚናገሩት በፍቅር መንፈስ ነው? በሌላው ሰው ድካም ደስ መሰኘት ኃጢአት ነው። ወሬው የተወራበት ሰው ወይም የታማው ሰው በሌለበት ወይም እርሱ ተገኝቶ ሁኔታውን ለማስረዳት ዕድል ሳይሰጠው፥ ሌሎች መጥፎ አስተያየትና ግምት በሰውየው ላይ እንዲኖራቸው ማድረግ ክርስቲያናዊ ባህሪ አይደለም። የምንናገረው ወሬ እውነትነት ካለው፥ ሰውየው ባለበት ጊዜና ወቅት ለመናገር

መፍራት የለብንም። በሰውየው ፊት መናገር የማንችለውን፥ በሌ ለበት ላለመናገር ለራሳችን ቃል እንግባ።

ሀሜትና አሉባልታ መጥፎነቱን ከተረዳን ማግቱን እንተው። ስለ ሌላው ሰው ከፉ ነገር ብንሰማ በዓይናችን ካላየን ወይም በሁ ለት በሦስት ምስክር ካላረጋገጥን ወሬውን አምነን አንቀበል። እውነት መሆኑን እንኳን ብናረጋግጥ፥ ወሬው የተወራበትን ሰው የሚጠቅመው ካልሆነ አናውራ። አንድ የአረቦች አባባል አለ፥

"ሌላው በሚሰጥር ያጫወተህን ምስጢር ለመግለጽ ብትፈተን፥ ወሬውን ወደ ሌላው ከማስተላለፍህ በፊት በሦስት ወርቃማ በሮች እባክህን እለፍ። የመጀመሪያው ጠባብ በር 'እውነት ነው?' የሚል ሲሆን፥ ሁለተኛው ጥያቄህ 'አስፈላጊ ነው?' የሚል ይሁን። ለነዚህ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ካገኘህ፥ የመ ጨረሻው ጠባብ በር አለልህ። ያም 'ምን በጎነት አለበት?' የሚል ጥያቄ ነው።"

ብዙዎቻችን ሀሜት (አሉባልታ) ኃጢአትና ጎጂ መሆኑን እና ውቃለን። ችግራችን ግን ከዚህ መጥፎ ባህሪ እንዴት መላቀቅ እንደምንችል አለማወቃችን ነው።

6. <u>አሉባልታ ሲነገርብን ምን ማድረግ አለብን?</u>

(1) የአሉባልታ ወሬ ከየት እንደመጣ ወይም ከየት እንደ ተጀ መረ መሠረቱን ለማወቅ መሞከር ከድካም በስተቀር ጥቅም የለውም። አሉባልታን የሚረጭ ሰው በተፈጥሮ ተንኮለኛ ሰው ነው። ወይም እንደ ባለአዕምሮ የሚያስብ ሰው አይ ደለም። አሉባልታው የመጣው እውነት ከማይናገር ሰው ከሆነ፥ ወሬውም እውነተኛነት የለውም። ሀሜተኛውን እጅ ከፍንጅ ይዞ ማፋጠጥ፥ ሌላ ክፉ ወሬ እንዲያወሩ ዕድልና መንገድ መስጠት ይሆናል።

(2) አሉባልታ ብዙ ጊዜ በቀላሉ ስለሚዛመት፥ ማን እንደጀመ ረው መወቅ ያስቸግራል። ሁሉም "ከእከሌ ነው የሰማሁት"

እያለ አንዱ ሌላውን መጠቆም ይጀምራል። አሉባልታው የፈለቀበትን ምንጭ ለማውጣት መሞከር በገዛ እጅ ሌላ ችግር በራስ ላይ መጨመር ይሆናል። ስለዚህ አሉባልታን ለማስቆም፥ ወሬውን ችላ ማለት አንዱ ጥሩ መንገድ ነው።

(3) በአሉባልታና በሀሜት ነፋስ የነፈሰውን ወሬ ለማረም ወይም ሀሰተኛነቱን ለመግለጽ መሞከር፥ ያልሰሙ ሰዎችን እንዲሰሙ ማድረግ ነው። አሉባልታ እንደ ማንኛውም ኃጢአት ዕድል ከሰጠነው ፈጥኖ ያድጋል። ብዙ ጊዜ ትክክል ያልሆነ ወሬ ስለ እኛ ሰምተዋል በማለት ያንን ለማስተካከል በሞከርን ቁጥር አሉባልታው እየጨመረና እያደገ ይሄዳል። ያልሰሙትም እንዲሰሙት ይሆናል። ሌላው ጉዳይ ስለ እኛ ትክክል ያልሆነ ወሬ ሰምተዋል በማለት ራሳችንን ለመግለጽ ስንሞክር ብዙዎች ስለ ጉዳዩ ፍጹም አለማወቃቸውን እንረዳለን። ቢሰሙ እንኳን ይህን ያህል ለአሉባልታው ሥፍራ ሰጥተውት እንዳልነበረ እንገነዘባለን። እኛ ወሬውን ለማስተባበል ስንሮጥና ስንታገል ሲያዩ፥ ይበልጥ አሉባልታው እውነትነት ይኖረው ይሆናል ብለው እንዲያስቡና እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል። ስለ እኛ የተወራውን አሉባልታ በገዛ እጃችን እንዳናስፋፋው እንጠንቀቅ። ብዙ ጊዜ አሉባልታን ችላ ብለን ስንተወው በገዛ እጁ እየጠፋ ይመጣል። "ጊዜ ይለየዋል" በማለት በእርጋታና በጸጥታ ለመተው ስንሞክር፥ ሳናስበው አሉባልታው ሞቶና ተቀብሮ እናገኘዋለን።

(4) ሌሎች አሉባልታ ሲያወሩብን፥ አጸፋውን ለመመለስ እኛም ስለ እነርሱ ማውራት ስንጀምር፥ ይበልጥ እሳቱ ይሰፋፋና ወደ ሌሎችም እንዲደርስና እንዲጎዱ ይሆናል። አንዳንድ ተንኮለኛ ሰው "እንዲህ ነህ ብሎ የነገረኝ እከሌ ነው" በማለት ንጹህን ሰው አሳልፎ የሚሰጥበትም ጊዜ እንዳለ ማወቅ ይረዳናል። እኛም ይህን ሰምተን ሳናረጋግጥ ያን ሰው ብንጠላውና ስለ እርሱ ክፉ ነገር መናገር ብንጀምር ትልቅ ስህተት ላይ እንወድቃለን። ስለዚህ አሉባልታን ለማጥፋት ሌላ አሉባልታ ማውራት ይጎዳል እንጂ እየጠቅምም።

(5) አሉባልታና መጥፎ ወሬ ሲወራብን ልባችን ማዘኑና ቅር

መሰኘቱ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፥ በዚህ ልባችን መራራ ሥር ካበቀለና በጥላቻ ከተሞላን የምንጎዳው እኛው ራሳችን ነን። በአሉባልታና በሀሜት ተሰነካክሎና ተፈነካክቶ የሚወድቅ ቢኖር፥ መራራነት ያጠቃው ሰው ብቻ ነው። በአሉባልታው መረበሽ፥ ራሳችንን ከአሉባልታ አውሪዎች ጋር እኩል ማድረግ ወይም እንደነርሱ ማነስ ነው። በአሉባልታ ወሬ መረበሽ እውነቱን እያወቅን ራሳችንን እንደ መጠራጠር ይቆጠራል።

(6) በአሉባልታ ወሬ ተደናግጠን ስለ ራሳችን ያለን ግምትና አስተያየት ዝቅተኛ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እና ድርግ። ማንነታችንን ሊወስነው የሚችለው አሉባልታና ሀሜት መሆን አይገባውም። ስለ ራሳችን አሉባልታ በሰማን ቁጥር ራሳችንን መደበቅና ማሸሹ አሉባልታውን አይቀንሰውም። ሸሽተን ከተደበቅን፥ ሰዎች የተነገረው አሉባልታ እውነት መስሏቸው እንዲፈርዱብን ዕድል ይሰጣቸዋል።

(7) ደግነታችንን የማይመኙ ሰዎች ጎጂ የሆነ አሉባልታ ሲያስወሩብን ልባችንን ሰፋ አድርገን በንቃት እንቁም። ሊጎዳን የሚፈልግ ጠላት እንደሚታገለን ልብ እንበል። በቀላሉ እንዳይጎዳን ራሳችንን እናጠናክር። ነቅፈታው የተሻለ ሰው ያድርገን እንጂ እንዲጎዳን አንፍቀድለት።

(8) አንዳንድ ሰዎች የአሉባልታ ወሬ ሲያስወሩብን ስንሰማ፥ ይህን ያህል ከፍተኛ ዋጋ አንስጠው። ለእነርሱም አጸፋውን ለመመለስ አንታገል። ክፉ ቃል ስለ እነርሱ ከአፋችን አይውጣ። ስጋትና ጭንቀት ወደ ውስጣችን እንዲገባ የልባችንን በር አንክፈት። ኃይላችንን፥ ቆጥበን ለእግዚአብሔር ክብር እናውለው እንጂ ከእነርሱ ጋር "ለእንካ ሰላምታ" መጠቀሚያ አናባክነው። በጎ የሆነ ነገር ብቻ እንጂ ክፉ ነገር ስሜታችንን አይቀስቅሰው።

(9) የአሉባታ ወሬ ለሚያወሩብን ሰዎች እንጸልይላቸው። በተፈጥሯችን ሰዎች የሚጎዳንን ሉባልታ ሲያስወሩብን ያስቆጣናል፥ እራሳችንን እንድንከላከል ወይም አስፈላጊውን መልስ እንድንሰጥ ያደርገናል። ይሁን እንጂ ትክክለኛ አይደለም። በተሞጋገው ቁጥር የበለጠ መጥፎ እየሆነ ይሄዳል።

ከመጥፎ ወሬ ይልቅ ጥሩ ወሬ ቶሎ ይሰፋፋልና ስለሚጠሉንና ክፉ ስለሚያመሩብን ሰዎች እኛ በክፋላችን ጥሩ ነገር እናወራ። ያ መልካም ወሬ ለጎዱን ሰዎች ቶሎ ይደርሳቸውና የአዕምሮ ጸጸት ያሳድርባቸዋል።

አሉባልታ አልፎ አልፎ እውነተኛነት ይኖረዋል። በእርግጥ እንደሚወራው በኃጢአት ወድቀን ሊሆን ይችላል። ከሆነስ ምን እናድርግ? *"ጠላቶቼ መውደቄን አውቀዋል፥ ያንንም ተጠቅመው ሊቆራርጡኝ፥ ተሰፋ ሊያስቆርጡኝና በርግጌ እንድጠፋላቸው ይፈልጉ ይሆናል። ይህ እንዲሆን አልፈቅድላቸውም። ከዚህ በኋላ ተሻሽዬ እንጂ ደከሚ እንዲያዩኝ አልፈልግም"* በማለት በን ስህ ውሃ ታጥበን፥ ራሳችንን አሻሽለን የምንቀርብበት ምክንያት እናድርገው። አሉባልታን መቋቋም የምንችለው ለጥቅማችን ያዋ ልነው እንደሆነ ብቻ ነው። ጆሮ የሚበጥስ ወሬ ስለ ራሳችን ስን ሰማ፥ ቶሎ ተሰፋ ቆርጠንና ፍርክስክስ ብለን አንውደቅ። ነገር ግን ይበልጥ ወደ ፊት የሚገፋን፥ የበለጠ የሚያሠራን፥ ራሳችንን እንድንለውጥና እንድናሻሽል የሚያደርገን መሣሪያ አድርገን እንጠቀምበት። ዳዊት አንድ ጊዜ ከፍተኛ ኃጢአት በሰውና በእ ግዚአብሔር ፊት ፈጸመ። ኦርዮንን አስገድሎ ሚስቱን ቀምቶ አገባ። ያን በማየት ሕዝቡ በሀሜት ሊቆራርጡት ሲነሱ፥ ይውጣ ላችሁ ብሎ በደለኛነቱን ግልጽ አድርጎ መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 51 ላይ ጽፎ አወጣው።

7. <u>አሉባልታ ሲደርሰን ምን እናድርግ?</u>

አሉባልታና ሀሜት መጥፎ መሆኑን እናውቃለን። ሌላውን መቆጣጠር ባንችል እንኳን ራሳችንን መቆጣጠር እንችላለን። ይሁን እንጂ፥ ችግራችን አሉባልታና ሀሜት ሲደርሰን አስተያየት ከመስጠት ለመቆጠብ፥ ንግግሩን ለማቋረጥ እንዴት እንችላለን? የሚል ነው።

(ሀ) አስቀድሞ ፕላን ማውጣት ይጠቅማል። በተለይ እንግዳ ቤታችን ጋብዘን እንደሆነ፥ እኛ ጋባዦች የውይይታችን አቅጣጫ ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት መወሰን ያስፈ

ልገናል። የጋበዝናቸው ሰዎች ጥሩ ጊዜ ኖሯቸው በጨ ዋታችን ታንዘፈፉ፥ ከአሉባልታና ከሀሜት ወሬ ተጠብ ቀው ደስ ብሏቸው እንዲሄዱ መሞከር ያስፈልገናል።

(ለ) በሕብሰባችን ላይ ያልተገኙት ሁሉ በሌሉበት በምንም ዓይነት መልክ እንዳይነኩ ለመከላከል አስቀድመን መወ ሰን። ሳፍሰፀው በጨዋታ መልክ የቀረበውን የአንዱን ስም አንስቶ አሞሙን እየተነተኑ ማውራት ከሆነስ ያኔ ምን ማድረግ እንችላለን? አንድ ጊዜ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከርስቲያኖች ተሰብስበው ቡና እየጠጡ የአንዱን ክርስቲያን ስም እየጠሩ ከፍ ዝቅ ሲያደርጉትና ከመካከላ ቸው ሁኔታው ደስ ያላሰኘው ሰው ፈገግ ብሎ *"ወገኖቼ ውይይታችን አቅጣጫውን እየለወጠ በመሄዱ፥ ደስ አላ ለኝም። እስቲ ይህን ዓይነት ወሬ ሰናወራ በመካከላችን ተገኝቶ ቢሰማ ምን ይሰማው ነበር?"* ሲል በጥሩ ሁኔታ ተናገረ። ይህን ሲሰሙ፥ ወዲያው አሉባልታውንና ሀሜ ቱን አቁመው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ተመለሱ።

(ሐ) የአሉባልታና የሀሜት ችግር ሁላችንንም ስለሚነካን በእ ርግጥ ዕለታዊ የሆነ ጸሎት ሊያስፈልገን አይቀርም። ዳዊት ችግሩን ስለተረዳው *"እግዚአብሔር ሆይ! ለአፌ ጠባቂ አኑርሃ በከንፈሮቼም በር ላይ ዘበኛ አቁም"* (መዝ. 141፥ 3) ሲል ጸለየ። ዳዊትን የመሰለ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ብሎ ከጸለየ፥ እኛማ ምን ያህል መጸለይ ያስፈልገን ይሆን? ስልካችንን አንስተን ንግግር ከመጀ መራችን በፊት፥ እንዲሁም ለምሳ ወይም ለእራት ከሰው ጋር ቀጠሮ ኖሮን ከመሄዳችን በፊት *"ጌታ ሆይ! አባክህን ለአፌ ጠባቂ አኑርሃ መናገር የማይገባኝን እንዳልናገር እርዳኝ"* በማለት ከልባችን መጸለይ ይገባናል። የምንናገ ረው ቃል በውስጣችን የምናስበው ሀሳብ፥ በእግዚአብሔር ፊት የተሸሸገ፥ የማይታወቅ አይደለም። ከአፋችን አው ጥተን ከመናገራችን በፊት እያንዳንዱን ቃል አስቀድሞ ያውቃል። ጨለማ በሆነው ልባችንና አዕምሯችን ውስጥ የምናስበው ሀሳብ ሁሉ ግልጽ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት

ይታያል። ብዙ ጊዜ ችግራችን እግዚአብሔር ትልቅ የሚለውን ኃጢአት፥ እኛ አቃለን እንደ ትንሽ ኃጢአት ስለምንመለከተው ነው።

አሉባልታ የሚጠነሰሰው በአዕምሮ ውስጥ ነው። የሚወለደው በኃጢአተኛው ተፈጥሯችን ውስጥ ሆኖ በእኛ እምቢ ባይነት፥ ትናትና ምቀኝነት እያደገ ይሄዳል። አድጎ አድጎ አንድ ቀን በግልጽ እስኪፈነዳ ድረስ፥ ራሱን ሰውሮ ይቆያል። ይህን ባህሪ ለማሸነፍ ትልቅ ዲሲፕሊን ወይም ውሳኔ ማድረግን ይጠይቃል። ውሳኔውም ኃጢአት የሆነውን "እምቢ" ትክክል የሆነውን "እሺ!" ማለት የቻልን እንደሆነ ነው። ስለዚህ አዕምሯችን ሀሜትንና አሉባልታን እንዳያፈልቅ እራሳችንን እናለማምድ።

ምዕራፍ ፯

ተሳዳቢ ምላስ

"ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፥ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም፥ ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ።"
(ኤፌሶን 4፥29)

ከሰዎች አንደበት የሚወጣው ቃል በራስም ሆነ በሌላው ሰው ሕይወት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ ባለፉት ምዕራፎች በሰፊው ተመልክተናል። ስለዚህ ነው ያዕቆብ *"ምላስም እንደ እሳት ናት፥ ምላስ በአካል ከፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፥ ሥጋችንንም ሁሉ ታቆሻሻለች"* ያለው (ያዕ. 3፥6)። እንደገና የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ፥ ረጅም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመቆየታቸው ብቻ፥ ያደጉ ወይም የበሰሉ ናቸው ማለት አይደለም። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ቢታይባትም፥ ከአባላቱ መካከል አብዛኛዎቹ ሥጋ ማኘክ ሲገባቸው ገና ወተት በመጋት ላይ ያሉ ሕጻናት እንደ ነበሩ ሐዋርያው ጳውሎስ መጀመሪያ በጻፈላቸው መልዕክቱ ላይ ገልጾታል። ለዚህ ነው ሥጋዊ

ክርስቲያኖች ብሎ የጠራቸው። *"ሲጋዊ ክርስትያኖች ናችሁ"* ያለበትን ምክንያት ሲገልጽ፥ *"...እርስ በርሳችሁ ስለምትቀናኑና ስለምት ከራከሩ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደለምን?..."* ይላቸዋል (1 ቆሮ. 3፥3)። እንደ ጳውሎስ አጻጻፍ ሥጋዊ ክርስቲያን ካሰኛቸው ምክን ያቶች መካከል አንደኛው ከአፋቸው የሚወጣው ጤናማ ያልሆነ ቃል ነበር። በዘመኑ ያለነው ክርስቲያኖችም፥ ከአፋችን በሚወጣው ቃል መንፈሳዊ አቋማችን ይለካል። ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ባዶ ስንሆን፥ መንፈሳዊ ነገር ሲያልትብን፥ መጽሐፍ ቅዱስ *"ሰው በአፉ የሚናገረውን በልቡ የተረፈውን ነው..."* (የማቴ. 12፥34) ስለሚል፥ ባዶ ከሆነው ልባችን ሌላውን የሚያንጽና የሚገነባ ቃል ሊወጣ እንደማይችል ግልጽ ነው። ስለዚህ፥ ስንበሳጭ፥ ልባችን በቁጣ ሲሞላ፥ ከአፋችን የሚወጣው ቃል ሌሎችን የሚገነባ ቃል ሳይሆን የሚያፈርስ፥ የሚያጽናና ቃል ሳይሆን ተስፋ የሚያስቆርጥ ይሆናል።

1. <u>የስድብ ቃል ከአፋችን የሚወጣበት ምክንያት</u>

ብዙ ጊዜ የስድብ ቃል ከአፋችን የሚወጣው በኃይለኛ ቁጣ (ንዴት) ውስጥ ስንሆን ነው። ስሜት በሕይወታችን አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንደኛው እንደሆነ የታወቀ ነው። ይህንንም ታላቅ ስጦታ የሰጠን እግዚአብሔር ራሱ ነው። ስሜት አንዳንድ በሕይወታችን ልንወስድ የሚገባንን እርምጃ እንድንገመግም የሚያደርገን ዓይነተኛ መሣሪያ ነው። የስሜትን ጠቃሚነትና አስፈላጊነት እንደሚገባው ካልተረዳን፥ በአግባቡ ልንጠቀምበት አንችልም። *ደስ ሲለን መሳቅ፥ የሚያሳዝን ነገር ሲያጋጥመን ማዘን፥ የሚያስደነግጥ ነገር ሲያጋጥመን መደንገጥ፥ የሚያስፈራ ነገር ሲያጋጥመን መፍራት* ባንችል ኖሮ ለብዙ ክፉ ነገር የተጋለጥን በሆንን ነበር። መናደድ ወይም መቆጣት ከስሜቶቻችን መካከል አንደኛው ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው፥ የሚያስደስት ነገር ሲገጥመው ደስ እንዲለው፥ የሚያስቆጣ ነገር ሲደርስበት ደግሞ እንዲቆጣ አድርጎ ስለሆነ፥ መናደድ ወይም መቆጣት ኃጢአት አይደለም። *"መቆጣት ትክክል አይደለም፥ ወይም ኃጢአት ነው"* እየተባልን ስላደግን፥

በተቻለን መጠን ቁጣችንን በውስጣችን ለመደበቅ እንሞክራለን። *"ስሜት"* በራሱ *"በጎ ወይም ክፉ፥ ጥሩ ወይም መጥፎ"* አይደለም! ከሁለቱም *"ገለልተኛ"* (neutral) ነው።

ቁጣችን ኃጢአት ወይም አጥፊ የሚሆነው በአግባቡ ካልተጠቀምንበት ብቻ ነው። ስሜታችንን በአግባቡ ከተጠቀምንበት ጥሩ ውጤት አለው። ቁጣቸውን በትክክለኛው መንገድ የማይጠቀሙ ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ። ይኸውም

1ኛ/ የሚያስቆጣ በጎ ያልሆነ ነገር ሲደርስባቸው፥ ምንም እንዳልሆኑ አስመስለው ስሜታቸውን የሚደብቁ ናቸው።

2ኛ/ በጎ ያልሆነ ነገር ወይም የሚያስቆጣ ነገር ሲደርስባቸው፥ የሚወስዱት እርምጃ ሌላውን ቢጎዳም፥ "ንዴቴ ከውስጤ መውጣት አለበት" በማለት መልካም ያልሆነ ነገር የሚፈጸሙ ናቸው።

ንዴታቸውን የሚገልጹት ሰዎች፥ የሚያስቆጣ ነገር ሲያጋጥማቸው፥ በንዴት ገንፍለው ያናደዳቸውን ሰው፥ የበታችነት ስሜት እስከሚያደቀው ድረስ የስድብ ቃል ያወርዱበታል። ስሜታቸውን የማይገልጹት ደግሞ ምንም ያህል አሳዛኝ ነገር ቢደርስባቸውም፥ የቁጣ ስሜታቸውን ውስጣቸው ይቀብራሉ። ያለአግባብ ሲረገጡና ሲጎዱ፥ "ተረገጥኩ፥ ተጎዳሁ" አይሉም። ስሜትን መደበቅም ሆነ ያለአግባብ መግለጽ፥ ሁለቱም ትክክል አይደለም።

ብናውቅም ባናውቅም፥ ማንኛውም ዓይነት ስሜት በሕይወታችን ያለውን ጥማት (ፍላጎት) ገላጭ ነው። ለምሳሌ ሲርበን፥ መብላት እንዳለብን የረሀብ ስሜታችን ይነግረናል። "የህሙም ስሜት" ሲኖረን ደግሞ በሰውነታችን ውስጥ አንድ ነገር ልክ አለመሆኑንና ህክምና እንደሚያስፈልገን ይገልጽልናል። እነዚህን ስሜቶች ችላ ብለን፥ ማስተካከል ብናስተካከል ይኸውም ሲርበን ባንበላ፥ ሲያመን ባንታከም በራሳችን ላይ የበለጠ ጉዳት እንደምናስከትል ግልጽ ነው። ፍጹም ስሜት የሌለን ሰዎች ብንሆን ኖሮ ምን ያህል የምናሳዝን ሰዎች እንሆን ነበር? ሲያመን ቶሎ ህኪም ቤት ሄደን ካልታከምን በቀላሉ ሊድን የሚችለው ለሞት ያደርሰናል። የቁጣስ (የንዴት) ስሜትስ ከዚህ የተለየ ይሆን? አንድ ሰው ከፍ ዝቅ አድርጎ ሲሰድ

በን፥ ወይም በሌላው ሰው ላይ ከፉ ነገር ሲደርስበት እያየን የማ
ናደድ ወይም የማንቆጣ ብንሆን፥ ጤናማነታችን ያጠራጥራል፡
አንዳንድ ቁጣ ጽድቅ ያለበት ስለሆነ፥ ዝም በማለታችን እግዚአ
ሔርን እናሳዝነዋለን። እግዚአብሔርን ማሳዘን ደግሞ ኃጢአት እ
ደሆነ እናውቃለን። ስለዚህ፥ የቁጣ ስሜታችንን አዳምጠን ሁኔታው
ለማስተካከል በቶሎ እርምጃ መውሰድ አለብን።

2. ቁጣ ምንድነው?

ቁጣ ምን እንደሆነ በደንብ ለመረዳት፥ አዲስ ኪዳን የተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ምን እንደሚለው ማወቅ ይጠቅመናል። የግሪክ ቋንቋ "ቁጣን" በሦስት ልዩ ልዩ ቃል ይገልጸዋል።

1ኛ) "ቴሞስ" (Themos) ይለዋል። ይሄ ቃል ቁጣን የሚገልጸው መጥፎ እንደሆነ አድርጎ ነው። "ሥርዓት የጎደለው፡ ሁከት፥ በስሜት መገንፈል... ድንገት መፈንዳት.." ማለት ነው። ኃይለኛ ቁጣን መግለጫ ነው (ኤፌ 4፥31፣ ገላት 5፥2)።

2ኛ) "ኦርጅ" (Orge) የሚለው ቃል ነው። ይሄም ቅሬታን የሚ ገልጽ ነው።

3ኛ) "አጋናክተሰስ (Agnaktesis) ይለዋል። ይሄም ቁጣን በአ ግባቡ መጠቀምን ይገልጻል።

2.1. የቁጣ ዓይነቶች

ዶክተር ድዋይት ካርለሰን (Dr. Dwight L. Carlson) "ቁጣንና መጎዳትን ማስወገድ" (Overcoming Hurts and Anger) በሚለው መጽሐፋቸው አራቱን የቁጣ ዓይነቶችን ጥሩ አድርገው ገልጸውታል።

1ኛ) የተቆጣው ሰው መቆጣቱን ራሱም ሆነ በአካባቢው ያሉት ሰዎች በግልጽ ያወቁት ቁጣ፥

2ኛ) ለተቆጪው ግልጽ ሆኖ፥ አካባቢው ባሉት ሰዎች ግን ያልታወቀ ቁጣ። የዚህ ሰው ፍልስፍና፥ "ዋጋ ቢያስከፍ ለኝም ከሁሉ ሰው ጋር በሰላም ልኑር" የሚል ነው።

3ኛ) በሁሉም ዘንድ ግልጽ ሆኖ፥ ለተቆጪው ግን ግልጽ ያል ሆነ ቁጣ፥

4ኛ) መቆጣቱን በራሱም ሆነ አካባቢው ባሉት ሰዎች ያልታ ወቀ ቁጣ፥-- ይሄኛው ከሌሎቹ ሁሉ የበለጠ አደገኛ ነው።

በተለያየ መንገድ ቁጣን ለመሸፈን፥ ወይም እንደሌለ አድርጎ ለማሳየት ጥረት እናድርግ እንጂ፥ ለተቆጪውም ሆነ በአካባቢው ላሉት ሰዎች ግልጽ ሆኖ ባይታይም ከቁጣ ነጻ መሆን የሚችል ሰው የለም። ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ስሜት፥ "ቁጣንም" ጨምሮ በአግባቡ ሊጠቀምበት ይገባል። ሰውን ሊያስቆጡት የሚችሉ በቀን ውስጥ ብዙ ሁኔታዎች እንዲሚያጋጥሙት የታወቀ ነው። ስለዚህም ቁጣን በአግባቡ በመግለጽ ፈንታ ስሜትን መደበቅ፥ እራስንም ሆነ በአካባቢው ያለውን ሰው መዋሸት ስለሆነ፥ በኃጢአት መኖር ነው።

2.3. ቅዱስ ቁጣ ይኖር ይሆን?

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከማንኛውም ሰው የበለጠ ተቆጪ ሆነው የምናያቸው፥ እግዚአብሔርንና ሰይጣንን ነው። ሰይጣን በጥፋት ላይ፥ እግዚአብሔር ግን ጽድቅን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ይቆጣል። ፍጹም ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር ሲቆጣ ማየታቸው ጥያቄ የሚ ፈጥርባቸው አንዳንድ ሰዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው። ትክክል ያልሆነ ነገር ሲያይ፥ ወይም ሲያጋጥመው፥ ቁጣውን በትክክል ይገ ልጻል። *"እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ ነው፥ ስለ ክፉ ነገርም ሁልጊዜ ቁጣውን ይገልጣል"* ይላል (መዝ. 7፥11)። ታላቅ የእግዚ አብሔር ሰው የነበረው ሙሴም ሕዝቡ ጣኦት ሲያመልክ በማየቱ በጣም ተቆጣ። *"ሙሴም ወደ ሰፈሩ ተጠግቶ ጥጃውንና ጭፈራ ባየ ጊዜ እጅግ ተቆጣ ይሄቸው የመጣውንም ጽላቶች በተራራው ሥር ወርውሮ ሰባበራቸው"* ይላል (ዘጸ. 32፥19)። ዳዊትም፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት እንዳይወድቅ የደገፈውን ሰው እግዚአብሔር በመግደሉ በጣም ተበሳጭቶ ነበር (2 ሳሙ. 6፥8)። በአዲስ ኪዳንም ኢየሱስ ብዙ ጊዜ እንደተቆጣ እናነባለን። *"...ኢየሱስም ስለ ልባቸው ድንዛዜ አዝኖ በዙሪያው ያሉትን በቁጣ ተመለከተና..."* ይላል (የማር.3፥5)።

እግዚአብሔር የሚቆጣ መሆኑን ካመንንና "ቁጣ" በአግባቡ እስከ ሆነ ድረስ ሁልጊዜ "ልክ አይደለም" ማለት አንችልም። *"ምንም ያህል ብትቆጡ፥ ኃጢአት ሳትሥሩ፥ ቁጣችሁም ሳይወገድ ፀሐይ አይጥለቅባችሁ"* ይላል (ኤፌ. 4፥26)። አስፈላጊ የሆነ ቁጣ እንዳለ ሁሉ፥ አስፈላጊ ያልሆነ ወይም ትክክል ያልሆነ ቁጣም እንዳለ እና ውቃለን። ጳውሎስ *"...ንዴትና ቁጣ ጩኸትና ስድብ... ከእናንተ ወዲያ ይራቅ"* ይላል (ኤፌ. 4፥31)። ዘማሪውም *"ሲጋትና ብዙ ወደ ችግር ስለሚመሩ አትቆጣ፥ አትናደድም"* ይላል (መዝ. 37፥8)።

2.4. <u>የቁጣ ምክንያቶች</u>

የቁጣ ስሜት በተፈጥሮ ከእግዚአብሔር የተሰጠንም ቢሆንና፥ ሊያስቆጡን የሚችሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች አሉ፥

(1) መብታችን የተገፋ ሲመስለን እንቆጣለን።

(2) በሕይወታችን እርካታ ሰናጣ፥

(3) ዓላማችንን የሚያጨናግፍብን ነገር ሲያጋጥመን፥

(4) ጥቃቅንም ሆነ ታላላቅ አንዳንድ የሚያስቆጣ ነገር ሲያጋጥመን፥

(5) ሰዎች ያልተረዱን ሲመስለን፥

(6) የጠበቅነውን ነገር ሳናገኝ ስንቀር፥

(7) የስሜት መታወክ ሲደርስብን እንቆጣለን።

አብዛኛዎቻችን ስለ ቅድስና ብለን ከምንቆጣበት ጊዜ ይልቅ፥ የምንፈልገውን ነገር ባለማግኘታችን የምንቆጣበት ጊዜ ይበልጣል። ቁጣቸውን በአግባቡ በመግለጽ ፈንታ ለመደበቅ የሚሞክሩ፥ ወይም በምንም ዓይነት ሁኔታ ቁጣችንን መግለጽ አለብን በማለት ያስቆጣቸውን ሰው በመሳደብ፥ ከፉ ቃል በመናገር ስሜታቸውን የሚገልጹ አሉ። በቁጣ ምክንያት ከአፋችን አውጥተን የምንወረውረው ከፉ ወይም የስድብ ቃል፥ ሌላውን ሰው ብቻ የሚጎዳ ሳይሆን፥ የግል ሕይወታችንን፥ ትዳራችንን፥ ከሰው ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ሊያበላሽ እንደሚችል የታወቀ ነው። የቁጣ ቃል አንዴ ከተወረወረ

ልንመልሰው እንደማንችለው ቀስት ነው። ቀስት አንዴ ከተወረወረ፥ የተወረወረበትን ዓላማ ሳይፈጽም አይመለስም። የቁጣ ቃልም ያበላሸውን፥ እንዳይበላሽ ማድረግ አይቻልም። ስለሆነም፥ ሐዋርያው ያዕቆብ *"...ሰው ሁሉ ለመሰማት የፈጠነ፥ ለመናገርና ለቁጣም የዘገየ ይሁን። ምክንያቱም የሰው ቁጣ፥ የእግዚአብሔር ጽድቅ በሰው ሕይወት ውስጥ ፍጹም እንዲሆን አያደርግም"* በማለት ጥሩ ምክር ይመክረናል (ያዕ. 1፥19-20)።

3. <u>"በአንድ ራስ፥ ሁለት ምላስ"</u>

ወሰን የለሀ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በመሆኑ በክርስቲያኖች ዘንድ የተከበረ ነው። አልፎ አልፎ ስለሚሰብክ በማስተማር ችሎታው ብዙዎች ያደንቁታል። ለሙሉ ጊዜ አገልግሎትም መውጣት ይቃጣዋል። ወሰን የለህን "ይሄ ይጎድለዋል" ብሎ የሚከሰው ማንም የለም። ረጋ ያለ፥ ድምጹን ቆጥቦ የሚናገር፥ ሥነ ሥርዓት ያለው ሰው ነው። ወሰን የለህ ሌሎች "ነው" እንደሚሉት ይሆን? ለአንድ ሳምንት ያህል እስቲ ወሰን የለሀን ቀረብ ብለን እንመልከተው።

አንድ ቀን በተወሰነው ሰዓት እንዲቀሰቅሰው የሞላው ሰዓት ሳይደውል ወይም ሳይቀሰቅሰው ቀረ። ብዙ ጊዜ ከእንቅልፉ ከሚነቃበት አንድ ሰዓት ዘግይቶ በመነሳቱ፥ ከወትሮው የሥራ መግቢያ ሰዓቱ አንድ ሰዓት አሳልፎ እንደሚገባ ስላወቀ በጣም አዘነ። እንዲ ቀሰቅሰው ሰዓቱን የሞላው ራሱ ስለሆነ፥ ምክንያት አድርጎ የሚቆጣው ሰው አልነበረውም። ሊተኛ ሲል ሰዓቱን ሚስቱ ሞልታው ቢሆን ኖሮ፥ ጉድ ፈልቶባት ነበር። ወሰን የለህ "ተሳስቼ ነው የሞላሁት" በማለት ፈንታ፥ "ጊዜውን ጠብቆ የማይደውል፥ የማይረባ ሰዓት ነው" በማለት በሰዓቱ ላይ መበሳጨት ጀመረ። በዚህ ብቻ አላበቃም። ሰዓቱን ለመቅጣት ይመስላል፥ አንስቶ በኃይል በመወርወር ከግድግዳው ጋር አጋጭቶ ስብርብሩን አወጣው። ይህን ሲያደርግ የሚጎዳው ሰዓቱ ሳይሆን ራሱ መሆኑን ቢያውቅም፥ ግድ አልነበረውም። በዚህን ጊዜ ከአፉ የሚወጣው የስድብ ቃል በጣም ያሳፍራል። ይህን የሚያደርገው የሚታዘበው ሰው ባለመኖሩ ይመስላል።

ሰዓቱን ከግድግዳ ጋር አጋጭቶ ሲሰባብረው፥ ሚስቱ ደንግጣ

ከዕንቅልፏ ባና ተነሳች። ለስለስ ባለ ድምጽ "ምነው? ምን ሆንክ?" ብላ ጠየቀችው። በዚህ ወቅት ክፉ ምላሱን ወደ እርሷ ያዞርና በእርሷ ላይ አነጣጥሮ መተኮስ ይጀምራል። *"ምን እንደልሽ ትፈልጊ ያለሽ? ዝም ብለሽ እንደ ግንድ ቀኑን ሙሉ ተጋደሚ! አንቺማ ምን አለብሽ ተኝተሽ ትበያለሽ! ደም መጣጭ (ፓራሳይት) ነሽ!"* ብሎ ይሰድባታል። ጸባዩን ብታውቅም፥ *"ምነው እቴ ምን አደረግሁሀ? ለምን ትሰድበኛለህ?"* ብላ ጠየቀችው። በዚህን ጊዜ ወሰን የለህ ድምጹን ከፍ አድርጎ እየጮኸ *"እባክሽን ተይኝ! እንግዲህ በጥዋት ተነሳሽ በምላስሽ ልትለበልቢኝ! አንቺ እቤት ውስጥ ትለበልቢኛለሽ፥ የሥራ አለቃዬም አሥር ደቂቃ አረፈድክ ብሎ ይለበልበኛል፥ አሁንስ የት አባቴ ልድረስ?"* ብሎ ያለአግባብ መበሳጨት ጀመረ። ጅሮ የሚበጥስ የስድብ መዓት በሚስቱ ላይ አውርዶ ተቻኩሎ ከቤቱ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወጣ። በዚህ ወቅት ወሰን የለህ ክርስቲያን መሆኑን አስታውሰ፥ *"ይህን ዓይነት ክፉ ወይም፥ የስድብ ቃል ከአፌ መውጣት አልነበረበትም፥ በጣም አዝናለሁ"* ብሎ አልተጸጸተም። ክርስቲያኖች በሌሉበት አካባቢ፥ ክፉ ቃልን መናገር ወይም መሳደብን ተለማምዶታል።

መኪናው ውስጥ ገብቶ ሞተሩን ሲያስነሳ፥ *"ሚስቴ ምን አደረገችኝና ነው ይህን ዓይነት የሰድብ መዓት ያወረድኩባት? እርሷንም እግዚአብሔርን በደልኩ"* በማለት የአዕምሮ ጸጸት ፈጽሞ አልተሰማውም። ትራፊክ ፖሊስ የለም ብሎ በሚያስብበት አካባቢ ከተወሰነው ፍጥነት በላይ መንዳት ጀመረ። እንደ እርሱ የቸኮለ ሰው የትራፊክ ሕግ ሳይጠብቅ ድንገት ከፊቱ ጥልቅ አለበት። ሊገጨው ትንሽ ነበር የቀረው። ወሰን የለህ በዚህን ጊዜ በጣም ተናደደ። ሰውየውም ባይሰማ፥ የመኪናውን መስታወት ዝቅ አድርጎ እጁን እያወራጨ *"ደደብ! የማይረባ! ቆሻሻ! አህያ!"* እያለ በሰውየው ላይ የስድብ መዓት አወረደበት። የሚያስደንቀው ነገር ግን መኪናው ጓላ ላይ *"ኢየሱስ ያድናል"* የሚል ጽሁፍ ለጥፎ፥ "ክርስቲያን ነኝ እወቁልኝ" የሚል ይመስላል። መኪናው ላይ የለጠፈውን ጽሁፍ ያነበበ፥ ወሰን የለህ የተሳደበውን ስድብ የሰማ ሌላ ሰው ቀድሞት እያለፈ፥ "ታዝ ብኩህ" የሚል ይመስላል አንገቱን ነቅንቆበት ሄደ። ወሰን የለህ የሰውየውን ሁኔታ አይቶ ወደ ራሱ በመመለስ ፈንታ፥ ይሄም ሰው የበለጠ ያበሳጨውና በእርሱም ላይ የስድብ መዓት ያወርድበታል።

ዘህ ዓይነት እየተበሳጨ መሥሪያ ቤቱ ይደርሳል። ሥራ የገባው አንድ ሰዓት አሳልፎ ነበር።

ልክ ቢሮው እንደገባ ከሥራ ባልደረባዎቹ አንዱ፥ አለቃችን *"ወሰን የለህ ሲመጣ በቀጥታ እዩ ቢሮ እንዲመጣ" ንገሩት ብሏልና ሂድና አነጋግረው"* አለው። ወሰን የለህ እየተጎነጨ አለቃው ቢሮ ገባ። አለቃውም *"ሰንት ሰዓት እንደሆነ ለማወቅ ለመሆኑ ሰዓትህን አይተሃል? ዛሬ ደግሞ ምክንያትህ ምን ይሆን?"* ብሎ ጠየቀው። ምን ዓይነት መልስ እንደሚሰጥ አስቀድሞ ስለተዘጋጀበት ተዝናንቶ ምክንያቱን መናገር ጀመረ። *"ሚስቴ እኩለ ሌሊት ላይ ድንገት ታማ ሆስፒታል ይዣት ሄጄ ነበር። ሌሊቱን ሙሉ ዕንቅልፍ አልተኛሁም። አሁንም እርሷን ባዶ ቤት ጥዬ ነው ወደ ሥራ የመጣሁት"* አለው። የወሰን የለህ አለቃም የቀረበለትን ምክንያት ስላልተጠራጠረ ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠው አሰናበተው። ወሰን የለህም የህሊና ክስ ሊያስጨንቀው ሲገባ፥ እንዲያውም ስለብልጠቱ ራሱን እያደነቀ ወደ ምድብ ሥራው ሄደ። በዚህ ዓይነት ሳምንቱ አልቆ ዕሁድ ደረሰ። ወሰን የለህና ሚስቱ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። በዕለቱ መልዕክት የሚያቀርበው ወሰን የለህ ስለ ነበረ መድረኩ ላይ ወጥቶ እንደ መልአክ ይሰብክ ነበር። *"ሚስቴ ግብዝ ብላ በትዝብት ዓይን ታየኛለች"* ብሎ አላፈረም። ሁለት ዓይነት መልክ ይዞ መኖርን ስለተለማመደ፥ ሕሊናው ደንዝዟል። እነዚያን ክፉ ቃላት በሚስቱ ላይ በወረወረበት ምላሱ፥ ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል መስበክ ጀመረ። "በአንድ ራስ ሁለት ምላስ" የያዘውን ባሏን ሲሰብክ ቁጭ ብላ ስታዳምጥ ሚስቱ ምን ይሰማት ይሆን? ሐዋርያው ያዕቆብ፥ *"ከአንድ አፍ ምስጋናና እርግማን ይወጣሉ፥ ወንድሞቼ ሆይ! ይህ ሊሆን አይገባም። ከአንድ ምንጭ ጣፋጭ ውሃና መራራ ውሃ ሊወጣ ይችላልን? ወንድሞቼ ሆይ! የበለስ ዛፍ የወይራ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን? ወይስ የወይን ተክል የበለስ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን? እንዲሁም ከመራራ ውሃ ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ ይችላልን?"* (ያዕ. 3፥10-12) ሲል የተናገረው እንደ ወሰን የለህን ዓይነቶችን ነው።

በወደቀው ዓለም ውስጥ እስከ ኖረ ድረስ፥ ሰው ሊያበሳጩት ከሚችሉ ነገሮች ማምለጥ አይችልም። ነገር ግን የሚያስቆጣውን ነገር የሚያስተናግድበትን መንገድ መምረጥ ይችላል። ግማሹ ታግሶ

ግለፍ ሲችል፥ ሌላው ደግሞ በየጥቃቅኑ ምክንያት ቁጣው ይገነፍላል። በሚፈልጉት ሰዓት እንዲደውል የሞሉት ሰዓት በሰዓቱ ደውሎ ባይቀሰቅሳቸውም የማይቆጡ፥ በግዴለሽ አነዳዳቸው አደጋ ሊፈጥሩ ባቸው የነበሩ ነጂዎችን በምሕረት የሚያልፉ፥ ከሥራ ሲመጡ ምግብ በጊዜው ባይቀርብላቸው የሚታገሱ፥ ለፍተው የሠሩትን ሥራ አለቃቸው ደስ ስላልተሰኘ "እንድ ገና በደንብ ሠርተህ አቅርብልኝ" ቢላቸውም፥ ያለማጉረምረም ትዕዛዙን የሚፈጽሙ፥ ከአፋቸው የስድብም ሆነ ሌላ ክፉ ቃል የማይወጣቸው ክርስቲያኖች አሉ።

4. ሰዎች የሚናደዱት በምን ምክንያት ይሆን?

ለመሆኑ ለምን ይሆን አንዳንድ ሰዎች በቀላሉ የሚናደዱት? ንዴትን የሚቀሰቅሱ ብዙ ምክንያቶች እንዳሉ አዋቂዎች ይናገራሉ። ሲደከመን በቀላሉ እንናደዳለን። የደም ግፊቱ ከፍ ሲል በቀላሉ የሚናደድ አንዳንድ ሰው አለ። ሴቶች በወር አበባ ጊዜያቸው በቀላሉ ሆድ ስለሚብሰቸው፥ የማያስቆጣው ትንሹ ነገር ሁሉ ያስቆጣቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ባልና ሚስት የሚጋጩበት ምክንያትና ሁኔታ በጣም የሚያስቅና የሚገርም ነው። አንድ ቀን አንድ ባልና ሚስት እራት ለመብላት ሆቴል ሄዱ። አሳላፊዋ ሥፍራ ፈልጋ አስቀመጠቻቸውና የሚያዙትን ምግብ እንዲመርጡ የምግብ ዝርዝር የያዘውን ወረቀት ለያንዳንዳቸው ሰጥታ ሄደች። ባልየው "ምን መብላት ትፈልጊያለሽ?" ብሎ ሚስቱን ጠየቃት። በጣም ተናዳ፥ ፊቷ ቡርቡሬ መስሎ "ምንድነው አንተ ሁልጊዜ እኔን የምትጠይቀው? የራስህ ምርጫ የለህም እንዴ? ለአንተ የምወስንልህ እኔ ነኝ እንዴ?" አለችው። ደንግጦ "ምን ሆንሽ? ምን ትፈልጊያለሽ ያልኩት ለአንቺ አንጂ ለእኔ አይደለም። ደህና አይደለሽም እንዴ?" ይላታል። አሁንም በቁጣ ቃል "ደህና ያልሆንክሀውስ አንተ ነህ አንጂ እኔ አይደለሁም" አለች። በዚህ ጊዜ ምን መመለስ እንዳለበት ግራ ስለገባው አዘኖ ዝም ይላል። ከጥቂት ጸጥታ በኋላ "እባክህን እቤቴ ውሰደኝ! እኔም አብጀለሁ፥ አንተ ሰው ነህ ብዬ ከአንተ ጋር አብሬ መውጣቴ" ብላ ተነስታ ወጣች። ምርጫ አልነበረውምና ወደ ቤት ይዟት ሄደ። በዚያን ቀን ሁለቱም ያለዕራት አደሩ። ይህቺ ሴት ምናልባት የወር አበባዋ ደርሶ ይሆናል ያለአንዳች ምክንያት የተቆጣችው።

ባሎች፥ ሚስቶቻቸው በወር አበባቸው ጊዜ የሚኖራቸው የጠባይ ለውጥ መረዳት ከቻሉ፥ በየወሩ የሚሆን ስለሆነ፥ የወር አበባቸው የሚመጣበትን ትክክለኛውን ቀን፥ ወይም አካባቢውን ግወቅ አስቀድሞ እንዲዘጋጁና በዚያን ወቅት በትእግሥት ሚስቶቻቸውን ማለፍ እንዲችሉ ይረዳቸዋል።

5. ሰዎች ንዴታቸውን የሚገልጹት በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?

ሁላችንም አልፎ አልፎ በተለያየ ምክንያት እንናደዳለን። ስንናደድም ሁላችንም ንዴታችንን የምንወጣበት ነገር እንፈልጋለን።

(1) በተለያየ መንገድ ንዴታቸውን የሚገልጹ አሉ። አሜሪካን አገር ለትምህርት በመጣሁበት በመጀመሪያው ዓመት ላይ ብዙ የደነቁኝና ግራ ያጋቡኝ ነገሮች አጋጥመውኛል። አንደኛው ይሄ ነው። እኔ ባለሁበት ዶርሚቶሪ ውስጥ፥ እኔ ካለሁበት ክፍል አጠገብ ተማሪዎች ሲጠማቸው እንዲጠጡ ታስቦ የቆመ ውሃ መያዣ ዕቃ (ፋውንቴን) አለ። ማታ ማታ፥ በተለይ ዕኩለ ሌሊት ላይ፥ አንዳንድ ተማሪዎች ያንን የውሃ ዕቃ እየመጡ እንደኳስ በኃይል በግራቸው ይረግጡታል። ሁለትና ሶስት ሳምንት ካየሁ በኋላ፥ እርግጫው የማይቆም መሆኑን ስረዳ፥ ቀረብ የሚለኝን አንዱን ተማሪ፥ አንዳንድ ተማሪዎች ይህን የሚያደርጉት ለምንድነው? ብዬ ጠየቅሁት። አጠያየቄና ግራ መጋባቴ አስገርሞት እየሳቀ፥ *"በትምህርትና በጥናት ድከም ሲላቸው፥ ከውስጥ የሚሰማቸውን የብስጭት ስሜት ከውስጣቸው ማስወጣታቸው ነው"* አለኝ። እኔም "ለካ አገራችን ውስጥ አንዳንድ ባሎች ማታ ማታ ውሃ ቀጠነ እያሉ ሚስቶቻቸውን የሚደበድቡት ለዚህ ይሆን?" ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። *ከላይ በገለጽኩት ዓይነት ከውስጣቸው የተጠራቀመውን ቁጣ ሲግስወጣት የሚመክሩት፥ አንዳንድ የሥነልቦና ምሁራን የሚሰጡትን ትክክል ያልሆነ ምክር የተቀበሉ ናቸው።*

(2) አንዳንዶች ደግሞ ከውስጣቸው ብስጭት ሲሰማቸው፥ ብ
ጭታቸው ካለፈ በኋላ የሚጸጸቱበትን መጥፎ ቃል ከአፋቸ
እያወጡ እንደጦር ይወረውራሉ። ባናደዳቸው ሰው ላ
የያዙትን ዕቃ ይወረውራሉ። አለቃቸው እቢሮው ጠር
ሲገስጻቸውም ሆነ የማይወዱትን ዓይነት ሥራ እንዲሠ
ሲያዛቸው፥ ተናደው እያጉረመረሙ በውስጣቸው እየተ
ደቡ በሩን በኃይል ዘግተው ይወጣሉ። ግብግ ጠሪው የ
ለገውን ለመጥራት፥ ያልፈለገውን ላለመጥራት መብት እ
ዳለው ቢያውቁም፥ "እከሌ ሌሎችን ሁሉ ቤቱ ጠርቶ ሲ
ብዝ፥ እኔን ለምን አልጠራኝም?" በማለት እየተበሳጩ
በዚያ ሰው ላይ ክፉ ነገር ለማለትም ሆነ ለማድረግ ወ
ኋላ የማይሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። የተናደደ ሰው፥ ሲ
ደድ ወይም ሲቆጣ የሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ነገሮች ቢና
ሩትም፥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የሚታየው ግን፥ ያስቆጣ
ውን ሰው እየጮኹ በመሳደብ ነው።

(3) በቀላሉ የሚናደዱ፥ ንዴታቸውን በስድብ መግለጽ ብቻ
ሳይሆን፥ በልዩ ልዩ ዓይነት መንገድም መበቀል የሚፈልግ
ሰዎች አሉ። ለምሳሌ በባሏ በጣም የተናደደች ሴት በዎ
ላዋ ከፉ ቃል ሳትናገር ከባሏ ጋራ "እኩል-ለኩል" የምትፈ
ጣበት፥ ወይም የምታበሳጭበት መንገድ ትፈልጋለች። ቤተ
*አይጠረግም፥... ሁሉ ነገር እንደተዝረከረከ ይተዋል... የተ
በላባቸው ሳሆኖች ሳይታጠቡ ይቆለላሉ... በሰዓቱ ምግብ
አይሠራም፥ አልጋው አይነጠፍም፥ ልጆቹ አይታጠቡም፥
ልብሳቸው አይቀየርም... ማቀዝቀዣው ውስጥ የሚበላ ነገር
አይኖርም።* ይህን ዓይነቱን ጸባይ የሥነ ልቦና ምሁሮች
"ልዝብ (ቀለስተኛ) ጠብ ጫሪነት" (passive-aggressive)
ብለው ይጠሩታል። ባልም ከሥራ ሲመጣ ቤቱ ውስጥ
የሚያየው ነገር ያስደነግጠውና "ምን ነው?" ብሎ ይጠይ
ቃል። ምን ማለቱ እንደሆነ ቢገባትም፥ "ምኑ?" ብላ ጥያቄ
ውን በጥያቄ ትመልሳለች። ቤቱ ውስጥ የሚያየውን፥ ከላይ
የገለጽነውን ሁኔታዎች ይነግራታል። ሁኔታው በጣም እን
ዳበሳጨው ታይና በልቧ "እኩል-ለኩል ሆንን" በማለት ደስ

*ይላታል። "እኩል ለኩል" መሆን ብቻ አያረካትም፥ እርሷ
ከተናደደችው የበለጠ እንዲናደድ ትፈልጋለች።*

*ልታስተላልፍለት የፈለገችው መልዕክት በደንብ ቢገባ
ውም፥ ድምጹን ለስለስ አድርጎ "ራት የለም እንዴ? ከሌለ
ሆቴል ሂደን እንብላ፥ እኔ እርቦኛል" ይላታል። እርሷም
ንዴቷን ለመወጣት አመቺ ጊዜ ትጠብቅ ስለነበረ፥ "እራት
እያዘጋጀሁ የማቀርብልህ ገረድህ ነኝ እንዴ? ሚስትህ እንጂ
ገረድህ አይደለሁም። ዕቃው ይታጠብ... አልጋው ይነ
ጠፍ... በሰዓቱ እራት ይቅረብልኝ ለማለት ገረድ መቅጠር
አለብህ።... ምነው እነ እከሌን አታያቸውም እንዴ? ሚስ
ታቸውን የሚይዙት እኮ እንደሚስበር እንቁላል አድርገው
ነው!... የመኪና በር እየከፈተ ሲያስገባት... ወንበር እየሳበ
ሲያስቀምጣት አታይም... እኔ ከእርሷ በምን አንሳለሁ?...
አሁንስ አበዛሽው! ዘመዶቼ ሁሉ 'ተይ አትቸኩዪ! ወንድ
እርሱ ብቻ አይደለም' ሲሉኝ 'ግድ የለም ክርስቲያን ነው
ብዬ አገባሁህ።* ካገባሁህ በኋላ *'ቤቱ አልተጠረገም፥ እራት
በጊዜ አልቀረበልኝም' እያልክ ታጉረመርማለህ።* ምን
*መስዩ ታየሁህ! አንተስ ምንድነህ? ዕድሌን አበላሸኸብኝ።
ስንቶቹ ዓይናቸውን ጥለውብኝ እንደነበረ ታውቃለህ ብዬ
አምናለሁ! አሁንስ አበዛኸው! ...አንገሸግሾኛል! መጨማለ
ቁን ትተህ በሰላም መኖር ትፈልግ እንደሆነ በሰላም ኑር!
ካልሆነ ግን ቤቱን ጥዬልህ እሄዳለሁ።* መፋታት ደግሞ
በእኔና በአንተ አልተጀመረም" ትለዋለች።

ስለ ቁጣና በቁጣ ስለሚሞሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ይና
ገራል።

*(1) "ቁጣ በጭካኔና በጥፋት የተሞላ ነው፥ ቅንአት ግን ከቁጣ
የባሰ ነው" ይላል (ምሳሌ 27፥4)።*

*(2) "ቁጣ የሰነፎች ቂም በቀል መወጫ ስለሆነ የቁጡነት ሰሜ
ትህን ተቆጣጠር" (መክብብ 7፥9)።*

*(3) "ቁጡዎች የሞኝነት ሥራ ይሠራሉ፥ ጠቢባን ግን ትዕግ
ሥተኞች ናቸው" (ምሳሌ 14፥17)።*

(4) "በቶሎ የሚቆጡ ሰዎች ጠብን ያነሣሣሉ፥ ግልፍተኞን ብዙ በደል ይፈጽማሉ" (ምሳሌ 29፥22)።

(5) "ከጋትና ብስጭት ወደ ችግር ሰለሚመራ አትቆጣ፥ ... ናደድም" (መዝ. 37፥8)።

6. ፈጽሞ አለመናደድ ይቻላል?

በቀላሉ በንዴት ቱግ የሚሉ ሰዎች መቼ ቱግ እንደሚሉ፥ ዓ እንደሚያስቆጣቸው፥ ተቆጥተው ምን ዓይነት ክፉ ነገር እንደግ ደርጉ፥ እንዲሁም ምን ዓይነት የስድብ ቃል ከአፋቸው እንደሚወ አይታወቅም። አብረዋቸው ለሚኖሩ ሰዎች እጅግ በጣም አስቸ ጋሪ ናቸው። በቁጣ ሲገነፍሉ ማንጋገር ቀርቶ አጠገባቸውም መ የሚያስፈሩ ሰዎች ናቸው። አጠገባቸው ባለ ዕቃ ወርወረው ይ ታሉ። አይሁዶች ስለ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የሚሰጡት ምክ አለ። *"በቁጣ ከሚገነፍለው ሰው ጋር ከርከር (ጠብ) አታንሳ፥ ወደ በቡረሃ ውስጥ አብረኸው አትጓዝ። ደም መፋሰስ ለእርሱ ምን አይደለም። የሚገላግል ሰው ከሌለ ያጠፋሃል"* ይላሉ።

የመናደድ ስሜታችን "ማብራያና" ማጥፊያ የለውም። "ፈጽ አልናደድም" ማለት አንችልም። የሚያስቆጣ ነገር ሲያጋጥመ መቆጣት የተፈጥሮ ባሕሪያችን ነው። ይሁን እንጂ፥ በንዴት ገን ለን' ክፉ ቃል መናገር፥ መሳደብ ወይም ሌሎችን መጉዳት አለብ ግለት አይደለም። ቁጣችንን የምንገልጽበትን መንገድ የመምረ ፈቃድና ኃይል ግን አለን። በሕይወታችን አስቸጋሪ ነገር ሲያጋ መን ንዴታችንን መቆጣጠር ራሳችንን ካላለማመድነው፥ በቁጣች ጊዜ ሁሉ በራሳችንም ሆነ በሌሎች ላይ ክፉ ነገር ማድረግ ልማ ይሆንብናል። እንዲህ ዓይነቱ ጸባይ በቤተሰብ ውስጥ እንደ ተላላፊ በሽታ ሊተላለፍ ይችላል። ወላጆች የሚያስቆጣ ነገር ሲያጋጥመ ቸው በቀላሉ የሚናደዱና የሚሳደቡ ከሆነ፥ ልጆችም ወላጆቻቸው የሚያደርጉት ነገር ትክክል ይመስላቸውና እነርሱም በተመሳሳይ መንገድ የንዴት ስሜታቸውን መግለጽ ይጀምራሉ። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ *"ከንዴተኛና ከቁጡ ሰው ጋር ባልንጀራ ሆነህ አት ተባበር፥ ምክንያቱም የእርሱን ጠባይ ከተማርህ መላቀቅ አትች ልም"* ያለው (ምሳሌ 22፥24-25)። ቁጡና ንዴተኛ የሆነ ጓደኛ ካለ

ንስ፥ ምን ማድረግ አለብን? በአንደኛው ክፍለ ዘመን የነበረ፥ ሲኒካ የተባለ ሮማዊ ፈላስፋ ስለ ቁጡነት ብዙ ጽፏል። ከምክሩ ውስጥ አንደኛው፥ *"ቁጡና ንዴተኛ የሆነ ሰው በንዴት ሲገነፍል፥ በፍቅር ታገሡት። ጦርነት ለማካሄድ ሁለት ሰው ይጠይቃል። ከሁለት አንዱ ዝም ካለ፥ ጠብ አይኖርም"* የሚል ነው።

የሲኒካ ምክር የማይሠራበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ፥ ከልምምድ እንዳየነው የሲኒካ ምክር ጠቃሚ ነው። አንድ ሰው በቁጣ ገንፍሎ ከፉ ስድብ ቢሰድበን መልሰን የተሳደብን እንደሆነ፥ ተቆጪው ትክክል መሆኑን ማሳየታችን ወይም መግለጻችን ነው። ቁጣን በቁጣ መመለስ የሚነድ እሳት ውስጥ ቤንዚል መጨመር ማለት ነው። ግጭቱን ይበልጥ የከረረ እንዲሆን እናደርገዋለን። መጽሐፍ ቅዱስም *"...ሰዎች ክፉ ነገር ሲያደርጉባችሁ እናንተም መልሳችሁ ክፉ ክፉ ነገር አታድርጉባቸው... ወንድሞቼ ሆይ፥ ቁጣን ለእግዚአብሔር ተው እንጂ ራሳችሁ አትበቀሉ..."* (ሮሜ 12፥17፥ 19) በማለት ይመ ክረናል። አንዳንዶች "ምላስ ዱላ ሆኖ ማንንም አያቆስልም" ይበሉ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ክፉ ምላስ እንደሚያቆስል በግልጽ ይናገራል። *"ያሉ ዋንታቄ የተነገረ ቃል እንደ ሰይፍ ያቆሰላል፥ ቡጥ በብ የተነገረ ቃል ግን ይፈውሳል"* ይላል (ምሳሌ 12፥18)።

7. አንዳንድ ሰዎች ሲሳደቡ ለምን አይቆረቁራቸውም?

አንዳንድ ሰዎች የስድብ ቃል ካፋቸው ሲወጣ፥ የማይቆረቁራ ቸው፥ በሌላው ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ፈጽሞ የማይሰማቸው ናቸው። ምክንያታቸው ምን ይሆን? *"መሳደቤ አይደለም፥ እውነት መናገሬ ነው። እውነት በመናገሬ ልደነቅ ይገባል። ሌባውን ሌባ ማለት፥ ንጽህናውን ሳይጠብቅ የሚሸተውን "ቆሻሻ፥ ግም" ማለቴ መሳደቤ ሳይሆን እውነቱን መናገሬ ነው። ሰዎች እውነቱ ሲነገራቸው ለይወዱም"* በማለት ይከራከራሉ። ከርከራቸው ተቀባይነት እንዲያ ገኝ ምሳሌ የሚሰጡት ኢየሱስ ፈሪሳውያንን *"የአባብ ልጆች፥ የተለ ሰናችሁ መቃብሮች፥ ግብዞች... ብሎ ይለይባቸው ነበር"* የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው። ኢየሱስ ግን እነዚህን ቃሎች የተጠቀ

መበት ምክንያት የተለየ ነው። በመስቀል ላይ ሲሰቅሉት፣ በምስማ
ሲጠረቅቁት፣ ሲሰድቡት፣ በጥፊ ሲመቱት፣ ምራቃቸውን ሲተፉበት
የሾህ አክሊል ሲደፉበት፣ የለበሰውን ገፍፈው በመውሰድ በልብ
ቁማር ሲጫወቱበት፣ ጦር ወርውረው ጎኑን ሲወጉት አልተሳደበም፣
በመሳደብ ፈንታ "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው
ብሎ ነው የጸለየው።

እነርሱ የሚሳደቡት፣ ከአፋቸው እንደ ጦር የሚወጋ ቃል የ
ወረውሩት ስለ ጽድቅ ሲሉ ሳይሆን፣ "ለምን አልቀደምኩም፣ ለም
የእኔ ፍላጎት አልተሟላም፣ ለምን የተመኘሁትን አላገኘሁም" ብለ
እንደሆነ ግልጽ ነው። ታሪኩ ተረት ይሁን እውነተኛ የተፈጸ
እንደ ሆነ አላውቅም። አንድ ጊዜ አንድ ሰው አንዱን "ሰደበኝ
ብሎ ከሶ ፍርድ ቤት አቀረበው። ሰዳቢው "አልሰደብኩትም" ብለ
ተከራከረ። ዳኛው ተሰደብኩ ያለውን ሰው "ለመሆኑ ምን ብሎ ሰ
በህ?" ብለው ጠየቁት። "ምንአባክ! ብሎ ሰደበኝ" ሲል መለሰላቸው፣
ዳኛውም "ይሄማ ስድብ አይደለም" በማለት ተከሳሹን በነጻ ለቀቁት፣
ከላሽ የዳኛውን ፍርድ ከሰማ በኋላ በጣም ተናዶ "ምንአባክ ግለ
ስድብ ካልሆነማ፣ ከቡርነቶ! እርሰም ምናባትህን!" ብሏቸው ፍርደ
ቤቱን ለቆ ወጣ ይባላል።

ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችም የስድብ ቃል ከአፋ
ቸው ሲወጣ ይሰማል። መጠኑ ይለያይ እንጂ፣ ሳናውቀው ከሁላች
ንም አፍ አልፎ አልፎ ክፉ ቃል ይወጣል። በአፍ ከመተላለፍ ነጻ
ብንሆንም፣ አልፎ አልፎ ከሰዎች አፍ በሚወጣ ክፉ ቃል፣ ተጎድ
ተን ስለምናውቅ፣ በክፉ ምላስ፣ አጥንት ሰብሮ በሚገባ ስድብ ስሜ
ታቸው የተጎዳ፣ የቆሰሉና የደሙ ሰዎች ጉዳታቸው ይገባናል። ተሳ
ዳቢው በመሳደቡ ጉዳት ስላልደረሰበት ይርሳው እንጂ፣ የተሰደበው
ሰው ግን በቀላሉ አይረሳውም። የሚያሳዝነው፣ የተጎዳው ሰው "ተጎ
ዳኹ" ብሎ ስሜቱን ሲገልጹ፣ "አዝናለሁ! ይህን የተናገርኩት ሳላውቅ
ነው። ይቅርታ" በማለት ፈንታ "እንዴት በዚህ ዓይነት በቀላሉ ትጎ
ዳለህ" ብለው የሚከራከሩ ሰዎች መኖራቸው ነው። በሌላ በኩል
ደግሞ የሚያስደንቀው፣ ተሰዳቢዎቹ የሰደቧቸውን ሰዎች "ስድብህ
ጎዳኝ ብለው ቅር ይለዋል፣ ያዝናል" ብለው መጎዳታቸው የማይገልጹ
መሆናቸው ነው።

ሁላችንም አልፎ አልፎ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ራሳችንን
መቆጣጠር የምንቸገርበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። መሀንዲስ፣ ሀኪም፣
ነርስ፣ አስተማሪ ወዘተ. ለመሆን ብዙ ዓመት ትምህርት ቤት ገብቶ
መማርን ይጠይቃል። ትምህርት ቤት ሳይገቡና ሳይማሩ ከላይ
በዘረዘርናቸው የሥራ ሙያዎች ላይ መሰለፍ አይቻልም። ወላጅ
መሆን ከባድ ኃላፊነትና ትልቅ እውቀትና ጥበብ የሚያስፈልገው
ቢሆንም፣ ወላጅ ከመሆኑ በፊት ትምህርት ቤት ገብቶ የተማረ
ማንም የለም። ስለሆነም፣ ልምምድ የሌላቸው አንዳንድ አዳዲስ
ወላጆች ልጆቻቸውን በማሳደግ ሥራ ላይ ተሰልፈው ብዙ ስህተቶ
ችን በልጆቻቸው ላይ ይፈጽማሉ። በተለይ እናት (ጥሩ እናት ከሆ
ነች) ስለ ልጆቿ ከጥቂት እስከ ማታ ድረስ እንደምትደክም የታወቀ
ነው። ለእናት ቀኑ ረጅም፣ ሌሊቱ አጭር ነው። ቀኑን ሙሉ ታግላ
መሸት ሲል ያላት ትዕግሥትና ኃይል ስለሚያልቅ በቀላሉ ትበሳጫ
ለች። ጥቂት ሲነጫነጩ፣ ምንም ያህል ብትወዳቸውም ብድግ አድ
ርጋ ከግድግዳ ጋር ማጋጨት የሚቃጣት ጊዜ እንደሚኖር ግልጽ
ነው። በጣም ከመድከሟ የተነሳ አስፈላጊ የሆነ እንኳን ጥያቄ
ልጆቿ ቢጠይቋት "ኡ! ኡ!" ብላ መጮኽ የሚቃጣት ጊዜ አለ።
በአፏ የመጣላትን ስድብ፣ ይጎዳል፣ አይጎዳም ብላ ሳታስብ ክፉ
ቃል ትወረውርባቸዋለች። ክርስቲያን ከሆነች፣ ክርስትያንነቷ የሚ
ፈተነው በዚህ ዓይነት ጊዜ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነው
"ትዕግሥት" ይታይባታል? ወይስ የስድብ መዓት ከአፏ ይወጣል?
አንዳንድ ሰዎች በንዴት ገንፍለው የመጣላቸውን የስድብ ቃል
በሰው ላይ ሲወረውሩ፣ ራሳቸውን ለመከላከል፣ አላጠፋሁም ለማ
ለት፣ እንዲሁም ከህሊና ክስ ለመዳን "የሚሰማኝን፣ የልቤን፣ እውነ
ቱን መናገሬ፣ ግልጽ መሆኔ ነው" ይላሉ። እውነቱን መናገር፣ ግልጽ
መሆን፣ የሚሰማቸውን ስሜት መግለጽ ይችላሉ። ይሁን እንጂ
በፍቅር፣ በርህራሄና እንዲሁም ራስን በመቆጣጠር መሆን እንዳለበት
መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ጸብ ጫሪነት ከሕይወታችን ክፍል አንደኛው መሆን የለበትም።
ጸብ ጫሪነት ከቁጣ መንፈስ የመነጨ ሲሆን፣ "እኔ ያልኩት ብቻ
ይሁን፣ የእኔ ፍላጎት ከሌሎች ሁሉ ቅድሚያ ይሰጠው፣ ወይም
የእኔ ብቻ ፍላጎት ይሟላ" ባይነት ነው። እውነተኛ ክርስቲያኖች

ከሆንን፥ ጨዋ፥ ርጋታ የሚታይብን እንጂ ጸብ የምንፈጥር፥ ተሳዳቢዎች፥ ጭቅጭቆች መሆን የለብንም። በአንዳንድ ምክንያት ልባችን በንዴት ሲሞላ፥ ከአስቆጣን ሰው አካባቢ ለጊዜው ገለል ብለን እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጠን፥ መንፈሳችንን ጸጥ እንዲያደርግልን መጸለይ አለብን። ራሳችንን መቆጣጠር አቅቶን ከፉ፥ ወይም የስድብ ቃል ከውስጣችን ወጥቶ እንደሆነ፥ እግዚአብሔርንም ሆነ ከፉ የተናገርነውንም ሰው ከልባችን ይቅርታ መጠየቅ አለብን። "ሁልጊዜ እየተሳደብኩ ይቅርታ መጠየቁ ሰለቸኝ" የምንል ከሆነ፥ በእርግጥ መዳናችንን እንመርምር። ምክንያቱም፥ ክርስቲያን ተንሸራትቶ ሊወድቅ ይችላል እንጂ፥ እውነተኛ የዳነ ክርስቲያን ሆኖ በኃጢአት ውስጥ ሁልጊዜ አይኖርም። *"የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ኃጢአት አይሠራም፥ ሊሠራም አይችልም ምክንያቱም የእግዚአብሔር ባሕርይ በውስጡ ስለሚኖርና ከእግዚአብሔርም ስለተወለደ ነው"* ይላል (1 ዮሐ. 3፥9)። እዚህ ላይ "ኃጢአት አይሠራም" ሲል፥ በኃጢአት ፈጽሞ አይወድቅም ማለቱ ሳይሆን፥ ሁልጊዜ ኃጢአት እየሠራ ወይም እየተለማመደ አይኖርም ማለቱ ነው።

8. <u>መሳደብ ኃጢአት ይሆን?</u>

መሳደብ ኃጢአት የማይመስላቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች እንዳሉ የታወቀ ነው። "መጋጨት" በሰዎች መካከል ሁልጊዜ ይኖራል። በሀሳብ፥ በምርጫ እስከተለያየን ድረስ መጋጨታችን አይቀርም። በወደቀው ዓለም ውስጥ፥ ከወደቀው ሰው ጋር እስከኖርን ድረስ መጋጨት ይኖራል። ይሁን እንጂ፥ ግጭት በጎ ነገርም ሊወጣበት ይችላል። ብረት ብረትን እንደሚስለው፥ በግጭታችንም አንዳችን ከአንዳችን እንግራለን። *"ብረት ብረትን እንደሚስል፥ ሰውም አርሰ በእርሱ አንዱ ከሌላው ይማራል"* (ምሳሌ 27፥17) ይላል። ስለዚህ መጋጨት ሁልጊዜ ክፉ አይደለም። ግጭት ፈርቶ ዝም ከማለት እውነቱን በፍቅር መናገር የተሻለ ነው። *"ምናልባት እግዚአብሔር ንስሐ የመግባትና እውነትንም የማወቅ ዕድል ስለሚሰጣቸው፥ ተታዋሚዎችንም በገርነት የሚያርም መሆን አለበት"* ይላል (2 ጢሞ. 2፥25)። አንዳንድ ሰዎች ከውስጥ የሚሰማቸውን ቁጣ ሁኔታው እስኪበርድ ድረስ ብለው ከውስጣቸው ቀብረው ለማስቀመጥ

ይሞክራሉ። ይሁን እንጂ፥ የሚያስቆጣቸው ነገር በላይ በላዩ ሲጨመርባቸው ሳያውቁት ፍቅርን ከውስጣቸው እየገደለ ይመጣል። በመጨረሻም ያ በውስጣቸው የተጠራቀመው ነገር በዝቶ ሲገንፍል ወይም ሲፈነዳ ንዴታቸውን ለመወጣት፥ ከአፋቸው የሚወጣው ቃል እጅግ አስከፊ ይሆናል። ያንን ሰው ይህን የመሰለ ስድብ የሰደብነው ይህን ያህል ከፍተኛ ጉዳት አድርሶብን ሳይሆን፥ በልዩ ልዩ ምክንያት ከውስጣችን የተጠራቀመ ንዴት ስላለብን ብቻ ነው።

ቁጣ በውስጣችን ሞልቶ በፈነዳ ጊዜ፥ ያስቆጣንና ከፍ ዝቅ አድርገን የሰደብነው ሰው ጥፋቱ ምን ይሆን ብለን ረጋ ብለን ብንጠይቅና ምክንያቱን ብንረዳ በራሳችን እናፍራለን። ሚስት የዕለት ሥራዋን ከመጀመሯ በፊት ገና አልጋዋ ላይ እያለች "ዛሬ ባሌ የሚወደውን ዓይነት ጥሩ ምግብ ሠርቼ ደስ አሰኘዋለሁ" ብላ ታስባለች። ፍላጎቷን በተግባር ለማዋል በሥራ ትንበስ ቀና ማለት ጀመረች። የምትፈልጋቸውን የምግብ ዓይነቶች በደንብ ሠራች። ጠረጴዛውን ከዚህ በፊት ባሏ አይቶት በማያውቀው የጠረጴዛ ልብስ አሰጌጠች። ለበዓል ጊዜ ብቻ የሚጠቀሙበትን ሳህኖች ደረደረች። ብርጭቆውን ሹካውን ማንኪያውን ቢላዋው ተደረደረ። ባሏ ሁልጊዜ ከሥራው ወጥቶ ቤት የሚደርሰው 12 ሰዓት ላይ ነው። ዕራት መብላት የሚጀምሩት ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ነው። ባሏ ከመምጣቱ በፊት ሁሉን ሠርታ ጨርሳ ስለ ነበረ፥ ምግቡን በሚያምር መልክ ደረደረች። የሚያማምሩ ሻማዎች በሚያማምሩ ሻማ ማስቀመጫዎች አድርጋ የባሏን መምጣት መጠባበቅ ጀመረች።

ባሏ በዚያን ቀን በተለመደው ሰዓት አልመጣም። 12 ሰዓት ተኩል ሆነ...ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆነ... ሁለት ሰዓት ሆነ። ያቀረበችው ምግብ ቀዘቀዘ። "የሚዘገይ ከሆነ ለምን ስልክ አይደውልልኝም?" ብላ ማዘን፥ መበሳጨት ጀመረች። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ መጣ። በዚህ ሰዓት ሁለት ምርጫ ነበራት። አንደኛው፥ ረጋ ብላ ምክንያቱን ጠይቃ መረዳት ሲሆን፥ ሁለተኛው፥ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳትጠይቅ በንዴት ገንፍላ ማናገር ነበር። ይህቺኛዋ ሴት ግን የመረጠችው ሁለተኛውን ነበር። ልክ እሳሩን ሲያስገባ አንበሳ ሆና የጠበቀችው ሚስቱ የስድብ መአቱን ማውረድ ጀመረች። *"ምን ዓይነት የማትረባ፥ ደደብ ሰው ነህ! ቢሮህ ስልክ የሌለ*

በት ሜካ ውስጥ አይደለም። ደውለህ በሰዓቱ አልደርስም ለምን ለኝም? ጥዋት ከእንቅልፌ ከተነሳሁበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ጊ አላረፍኩም። ውስጥ እግሬ ተቃጠለ። ምን አለ አንተማ ው ትውላለህ እኔማ እንደ ሌሎች ሴቶች ባሎች መስለሽኝ ነው። አ ወግና ማዕረግ የምትፈልግ ሰው አይደለህም። እስቲ እከሌን እየ በሰዓት ገብቶ በሰዓት የሚወጣ፥ ሚስቱን የሚያከብር፥ ለሚ የሚሸቆጠቆጥ ሰው ነው። አንተ ብቻ ነህ በእኔ ላይ የምትጫወተው ግድ የለም ጥፋቱ ያንተ አይደለም... ጥፋቱ የእኔ ነው... ንቄ ነ ውህ ናሮ ትሸር ነበር..." በማለት አፏ ላይ የመጣላትን ሁሉ ወረ ረችበት።

ከሌሎች ወንዶች ጋር እያወዳደረች የምትፈልገውን ዓይ ስድብ አውርዳ ስትጨርስ፥ "ጨረስሽ?" ብሎ ጠየቃት። እርሷ "ምን ልትል ነው? አንተ እንደሆንክ ምክንያት አታጣ!" አለችው እርሱም "በጣም አዝናለሁ! ቀኑን ሙሉ የደከምሽበት ነገር በ ሁኔታ ግለቁ ያሳዝናል። ይህን ሁሉ የስድብ መአት ሳታወርጂ ምክንያቴ ምን እንደሆነ ብትጠይቂኝ ናሮ ጥሩ ነበር። መጽሐ ቅዱስ 'ሰው በልቡ የተረፈውን በአፉ ይናገራል ስለሚል፥' ሁኔታ የልብሽን አቋም ያሳያል። ይህን ሁሉ ምግብ ያዘጋጀሽው ወ ኝና ለክብረሽኝ ነው? ወይስ 'ይህን ሰራሁ ብለሽ ራስሽን እንዲል ሽ ነው? ወደሽኝ ቢሆን ናሮ፥ የተዘጋጀው ለእኔ ከሆ 'እወደዋለሁ የምትይውን ሰው እንዴት ከፍ ዝቅ አድርገሽ ትሰደ ዋለሽ? እንዴት ከሌሎች ወንዶች ጋር እያወዳደርሽ፥ እያጥላላ እያሳነስሽ ትናገሪዋለሽ? ለጥጋቢ ምክንያት ባይኖረኝ እንኳን በሰ ለእራት ባለመምጣቴ ምክንያት ብቻ ይህን ያህል ከፍ ዝቅ አደ ገሽ ልትሰድቢኝ ይገባል ወይ? መጽሐፍ ቅዱስ 'ሚስቶች ሆ ባሎቻችሁን አክብሩ' ይላል እንጂ፥ 'ሚስቶች ሆይ! አራት አዘጋ ታችሁ ስትጠብቋቸው በሰዓቱ ያልመጡ እንደሆነ ስደቧቸው' ነ ያለው? ለመሆኑ ከፉ ቃል፥ ስድብ ኃጢአት አይደለም? ክርስትና እዚህ ላይ የት ነው ያለው?" ሲል ጠየቃት። ንግግሩን አቋር "ስብከትህን እዚያው ለራስህ አድርገውና፥ ምክንያትህን ንገረ አለችው። "ምክንያቴ ይሄ ነው። ከሥራ ወጥቼ ወደ ቤት ስመጣ የትራፊክ መብራት ቀዩ አልር አረንጓዴው ሲበራ ገና መሄ

ሰጀምር አንድ ትንሽ ልጅ ከየት እንደመጣ ሳላውቅ በርሮ በመ ኪናዬ ተመቶ ወደቀ። አንቡላንስ ተጠርቶ ልጁ በአስቸኳይ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ። ፖሊሶ መንጃ ፈቃዴን፥ የመኪናዋን የባለቤት ነት ካርድና የኢንሹራንስ ወረቀት ተቀብሎ፥ መኪናዋ የእኔ መሆ ኗን፥ ወንጀል ያለብኝ መሆን አለመሆኔን ሲመረምር ቆየን። ፖሊሱ እንደጨረሰ፥ የተገጨው ልጅ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማየትና ለመጠየቅ ሆስፒታል ሄድኩ። ሁሉን እንደ ጨረስኩ ወደ ቤት መጣሁ። በአደጋ ምክንያት ደነገጥኩ። አሁን ደግሞ ጨካኝ በሆ ነች ሚስት ምላስ ተገረፍኩ። ምክንያቴ ገባሽ?" በማለት መልስ ሰጣት። "ጥፋተኛ ነኝ! አዝናለሁ" በማለትና ሁኔታውን በማስተካከል ፋንታ "ብላ፥ አትብላ" ሳትል ሁሉንም ነገር ጠረጴዛው ላይ እንዳለ ትታ መኝታ ቤቷ ገብታ ተኛች።

ይህቺ ሴት ራሷን መቆጣጠር ብትችል ኖሮ፥ ብዙ ጥፋት አት ሠራም ነበር። "ክርስቲያን ብዬ ራሴን ከጠራሁ፥ ባሌንም ሆነ ሌላ ሰው መሳደብ፥ ከፉ ቃል ከአፌ ማውጣት ይገባኛል ወይ?" ብላ ብታስብ ኖሮ ራሷን መቆጣጠር ትችል ነበር። እንዲሁም ትዕግሥት ኖሯት ምክንያቱን ብታዳምጥ ኖሮ፥ ከላይ የሰማነውን ዓይነት ከፉ ቃል ከአፏ አይወጣም ነበር። አንዳንድ ክርስቲያኖች ኃጢአት ምን እንደሆነ የገባቸው አይመስሉም። ለነርሱ ኃጢአት ማለት "መስረቅ፥ ዝሙት ማድረግ፥ መግደል..." ብቻ ነው። በአሁኑ ጊዜ መሳደብ ፈጽሞ ኃጢአት የማይመስላቸው ብዙ ናቸው። በየክርስቲ ያን ቤቱ የሚደረገውን ይቃል ልውውጥ የሚቀዳ መቅረፀ ድምጽ (tape recorder) በስውር ለአንድ ወር ያህል ቢቀመጥ ምን ዓይነት የሚያሳፍር፥ "እነዚህ ክርስቲያኖች ናቸው ወይ?" በማለት የሚያስ ጠይቅ የስድብ ቃል ይሰማ ነበር። ሚስቶቻቸውን በመስደብ የሚያ ዋርዱ፥ በጥርጣሬ ተሞልተው "የት ሄድሽ? ...የት ገባሽ? ...ማን አየሽ?" እያሉ መከራ የሚያሳዩ ወንዶች አሉ፥ እንዲሁም፥ ባላቸ ውን የማያከብሩ፥ "...አንተም ወንድ ተብለህ ትጠራለህ?... የወንድ አልጫ..." ብለው የሚሳደቡ ሴቶች አሉ። የሚያሳዝነው በዚህ ከፉ በተናገሩበት፥ በተሳደቡበት ምላሳቸው ቤተ ክርስቲያን ሄደው የሚ ዘምሩ፥ የሚሰብኩ መሆናቸው ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ለማሳ የት ነው ሐዋርያው ያዕቆብ "ከአንድ አፍ ምስጋናና እርግማን ይወ ጣሉ፥ ወንድሞቼ ሆይ! ይህ ሊሆን አይገባም። ከአንድ ምንጭ

ጣፋጭ ውሃና መራራ ውሃ ሊወጣ ይችላልን? ወንድሞቼ ሆይ! የበለስ ዛፍ የወይራ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን? ወይስ የወይን ተክል የበለስ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን? እንዲሁም ከመራራ ውሃ ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ ይችላልን?" ያለው (ያዕ. 3፥10-11)።

9. ክፉ ቃል ከአፋችን እንዳይወጣ መውሰድ የሚገባን ጥንቃቄና እርምጃ

9.1. የተቆጣንበት ምክንያት አጥጋቢ መሆኑን እንመርምር

አልፎ አልፎ በማይረባ ምክንያት ክፉ ቃል ከአፋችን የሚወጣበት ጊዜ አለ። ተቆጥተን ክፉ ቃል በመናገር ሌላውን ከመጉዳታችን በፊት የተናደድንበትን ወይም የተቆጣንበትን ምክንያት እንወቅ። አንዳንድ ጊዜ ሰው ሲደክመው በቀላሉ ስለሚበሳጭ የተቆጣነው ደክሞን ይሆን? ከሆነ፥ አሰፈላጊውን ዕረፍት እንውሰድ። ሴቶች ደግሞ፥ የወር አበባቸው መምጫ አካባቢ በቀላሉ የማዘን፥ የመከፋት ስሜት ስለሚኖራቸው፥ የቁጣ ስሜት የተሰማቸው በዚያ ምክንያት እንደሆነ ራሳቸውን ይጠይቁ። የወር አበባቸው የሚመጣበትን ጊዜ አስቀድሞ ማወቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ይረዳቸዋል። "ፍላጎቴ ለምን አልተሟላም፥ እኔ ያልኩት ብቻ ለምን አልሆነም?" ብለን እንደሆነ፥ እንዲህ ዓይነቱ መንፈስ ኃጢአት መሆኑን አውቀን ጌታን ይቅርታ እንጠይቀው። በዚህ ዓይነት ራሳችንን መመርመር ከቻልን፥ በሌላው ሰው ላይ ከመቆጣትና ክፉ ቃል ከመናገር እንቆጠባለን። *"የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር፥ ለማስተማርም የሚበቃ፥ ለትዕግሥትም የሚጸና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም"* ሲል ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በሰጠው ምክር እንጠቀምበት (2 ጢሞ. 2፥24)።

9.2. የተጋጨንበትን ምክንያት እንወቅ

ብዙዎቻችን ያከራከረን፥ ወይም ያጋጨን ምክንያት ምን እንደ ሆነ የማናውቅበት ጊዜ አለ። አንዳንድ ሴቶች፥ *"ባሌ ምን እንደሚሰማኝ ባልነግረውም ሰሚቴን ማወቅ አለበት"* ይላሉ። የሰው ልብ የማንበብ ችሎታ እንደሌለው ይረሳሉ። ስሜታቸውን፥ ፍላጎታቸውን ለባሎቻቸው በመግለጽ ፈንታ፥ ባሎቻቸው እንዲህ ማወቅ ያለባቸው መስሎ ስለሚሰማቸው "ይሄን እንዴት አያውቅም?" በማለት በባሎቻቸው ላይ የሚበሳጩ ሚስቶች እንዳሉ የታወቀ ነው። የሚሰማንን ስሜት፥ የምንፈልገውን ነገር "በፍቅር መናገር" ብንችል፥ ግጭቶቻችን በጣም ይቀንሱ እንደነበር ምሁርን ይናገራሉ። ባልና ሚስት በተጋጩ ቁጥር፥ "ይሄ ጎደለ... ይሄ ሆነ... ያ አልሆነም..." በማለት ብዙ ያልሆነላቸውን ነገር ሲዘረዝሩ በሁለቱም አቅጣጫ ይሰማል። *"... አንተ ለቤተሰብህ ጊዜ የለህም... ሁልጊዜ ሥራ አለብኝ... ስትል መስማቱ ሰልችቶኛል..."* ይላሉ። የግጭታቸው ምክንያት ምናልባት ባል ከቤተሰቡ ጋር የሚያሳልፍበት ጊዜ ማጣት ይሆናል። ከሆነ፥ ባል *"ሌላ ነገር ማሟላ የማይገባበት የቤተሰብ ጊዜ በላምንት አንድ ቀን ይኑረን ማለትሽ ነው?"* ብሎ ሚስቱን በመጠየቅ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት። በዚህ ዓይነት ሁልጊዜ የሚያጋጫቸውን ምክንያት ለይተው ለማወቅ ቢሞክሩ፥ ወደ ፊት የሚያጋጥማቸው ግጭት በጣም ይቀንሳል።

9.3. ንግግራችን "ገጭዎነት" (Gentleness) የተሞላ ይሁን

ጴጥሮስ ሚስቶችን ሲመክር *"ውበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት የጋው እጅግ የከበረ በሆነና በማይጠፋው ጌጥ በገርነትና በጭምትነት ውስጣዊ ሰውነት ይሁን"* ይላል (1 ጴጥ. 3፥4)። "ጨዋነት" ብዙ ነገርን ያጠቃልላል። --ርህራሄ፥ ደግነት፥ ረጋ ያለ መንፈስ፥ ታጋሽነት፥ አላጊነት ወዘተ. ያጠቃልላል። ንግግራችን በጨዋነት የተሞላ መሆን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ስፍራ ላይ ተጠቅሷል። *"ልዝብ አንጋገር ቁጣን ያስታግሳል፥ ግልፍታ የተሞላበት አንጋገር ግን ቁጣን ያባብሳል"* ይላል (ምሳሌ 15፥1)። እንዲሁም ምሳሌ 16፥24 ላይ *"መልካም ንግግር እንደ ማር ወለላ ጣፋጭ ነው፥ ለሰውነትም ፈውስ የሚሰጥ ነው"* ይላል። "ጨዋነት" ምን ዓይነት ነው?

(ሀ) በጨዋነት የሚናገር ሰው፥ በሌላው ሰው ላይ አይጮኽም። ንግግሩ በእርጋታ የተሞላ ነው። ሀሳቡን ለመግለጽ መጮኽ አያስፈልገውም። "ልዝብ አንጋገር ቁጣን ያስታግሳል" ያለው ንግግራችን በመጪዉ አይሁን ማለቱ ነው። አንዳንድ

ጊዜ ያለንበት ሁኔታ እጅግ ትዕግስትን የሚፈትን ከመሆኑ የተነሳ ረጋ ብለን ለመናገር ያስቸግር ይሆናል። ሆኖም እግዚአብሔር ጸጋውን እንዲያበዛልን በመጸለይ ትዕግሥትና ዕርጋታ የተሞላበት ንግግር ለማድረግ በየጊዜው ጥረት ልና ደርግ ያስፈልጋል።

(ለ) በጨዋነት የሚናገር ሰው በፊቱ ገጽታ ላይ የሚታየው ሁኔታ የሚስብ እንጂ የሚገፋተር አይደለም። አንዳንዶቻችን ብዙ ጊዜ አሳባችንን የምንገልጸው በቁጣ ምክንያት ስሮቻችን ተግተርትረው፥ ዓይኖቻችን ፈጥጠው፥ ከንፈሮቻችን እየተን ቀጠቀጡ፥ ቁና ቁና እየተነፈስን ነው። እነዚህ ሁሉ የጨዋነት ምልክት አይደሉም።

(ሐ) ጨዋን ሰው "ጨዋ" የሚያሰኘው አንደኛ ከአፉ በጎ እንጂ ክፉ ቃል ስለማይወጣ ነው። እርግጥ ነው ጨዋነት በራሳችን ጥረት አይመጣም። ጨዋነት ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል አንዱ ነው። *ሰደብ፣ ወቀሳ፣ ማጉረምረም፣ በደል ቆጠራ፣ የፍርድ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አንዳልሆነ ግልጸ ነው።* ጨዋ የሆነውን ኢየሱስን በሕይወታችን ስናስገባ፥ መንፈስ ቅዱስ ውስጣችንን እንዲለውጥ ስንፈቅድለት፥ የክርስቶስ ጨዋ የሆነ መንፈስ በእኛ ሕይወት ውስጥ በግልጽ መታየት ይጀምራል። ጨዋነታችንም የሚታወቀው ከአፋችን በሚወጣው ቃል ነው። ጨዋነታችንን የሚያሳይ ነገር ከአፋችን የማይወጣ ከሆነ፥ የፈለግነውን ዓይነት የሃይማኖት ሥርዓት ብንፈጽምም፥ ከጌታ ጋር ቅርበት እንደሌለን በግልጽ ይታወቃል።

ምዕራፍ ፯

ውሸተኛ ምላስ

"እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ ምክንያቱም አሮጌውን ሰው ከነሥራው አውልቃችሁ ጥላችሁታል። አዲሱንም ሰው ለብሳችሁታል፥ ይህም አዲስ ሰውነት እርሱን በመሳት ወደግወቅ ያደርሳችሁ ዘንድ ፈጣሪው እግዚአብሔር በራሱ መልክ ምሳሌ ዘወትር እንዲታደስ የሚያደርገው ነው።"
(ቆላስይስ 3፥9)

ዓለማችን የመልካም ሥነ ምግባር ሥርዓተ ሕግ የሚጣስበት፥ ውሸት ጎልቶ የሚታይበት ዓለም ነው። ውሸት በዓለማችን ውስጥ ምን ያህል እንደ ሰለጠነ ለማየት በምሁራን ተጠንተው የቀረቡትን አንዳንድ እስታትስቲክስ መመልከቱ ይጠቅማል። ለምሳሌ፥ ከአሜሪካ ሕብረተሰብ ውስጥ፥

- *ታክስ ከሚከፍለው ሕዝብ ሰላሳ አምስት ከመቶ (35%) እውነቱን ሪፖርት አያደርግም፥*
- *የበላይ ባለሥልጣናት በዓመት 40 ቢሊየን ዶላር ከመሥሪያ ቤታቸው እየዋሹ ይሠርቃሉ፥*